# የኢዴፓ የፖለቲካ ፕሮግራም ትንታኔ

## ክፍል አምስት (Volume - 5)

## በልዩ ልዩ ማኅበራዊ ጉዳዮች ኢዴፓ
## የሚያራምደው አቋም

(ረቂቅ - ፩)

ሰኔ 1995 ዓ.ም

## ብርቱ ማሳሰቢያ፣

ይህ ሰነድ ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ይፋ የተደረገው በሰኔ ወር 1995 ዓ.ም ነው። ፖለቲካ በባህሪው የተለዋዋጭ ሂደቶች (Political Dynamism) ውጤት ነው። በዚህም ምክንያት ሰነዱ ከተዘጋጀ ወዲህ ባሉት ጊዜአት በሀገሪቱ በርካታ ሁኔታዎች ተስተውለዋል። እንደ ፖለቲካ ኃይል፤ ኢዴፓም የዚሁ ዳይናሚዝም ውጤት ነው። ስለሆነም፣ ፓርቲው ይህንን ሰነድ አሁን ካለው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የመጨረሻውን Version እስከሚያወጣ ድረስ፤ ይህንን ሰነድ የሚያነቡ ሁሉ የተጻፈበትን ወቅት የቋንቋ አጠቃቀምና ስነልቡና ከግምት ውስጥ እንዲያስገቡ በአክብሮት እናሳስባለን።

**(የኢዴፓ የውጭ ጉዳይ ዘርፍ)**

# ክፍል - 5

## በልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች ኢዴፓ የሚያራምደው አቋም

## 1. ማህበራዊ ደህንነት (ዋስትና)

*ጠንካራ ማህበራዊ ዋስትና የጠንካራ ኢኮኖሚ እድገት ውጤት ነው፡፡ በሀገራችን እንዲመሰረት የሚፈለገው መልካም አስተዳደር የሁሉንም ዜጎች ጥቅም የማቻቻልና ደህንነታቸውን የማረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መፈፀሙንም የማረጋገጥ ግዴታ አለበት፡፡ መንግስት ለዜጎች የጤና ችግር፣ በጤና መታወክ ከስራ ለሚሰናበቱ፣ ለጡረታ፣ ለሕፃናት እንክብካቤ፣ ለድሖች የቤት ኪራይ መደጎሚያ፣ ለስራ አጥነት ችግር ማቃለያ፣ ለአካል ጉዳተኞች፣ ለጦር ጉዳተኞች ድጋፍ ወዘተ. የሚሰጡ አገልግሎቶችን ስራ ላይ ለማዋል የሚያስችሉ ሕጋዊ ስርዓቶችን ተግባራዊ በማድረግ ይኽንኑ ግዴታውን ሊወጣ ይገባል፡፡*

*በሀገራችን በአሁኑ ጊዜ ጠንካራ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም ለመዘርጋት የሚያስችል የኢኮኖሚ እድገት ባይፈጠርም አስፈላጊነቱ ሊታመንበትና አቅም የሚፈቅደውን ያህል ተግባራዊ በማድረግ ሊጀመር ይገባዋል፡፡ ከኢኮኖሚው እድገት ጋር አብሮ ሊያድግ የሚችል የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም በአቅም መጠን ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ ለመጪው ጊዜ የዜጎች ደህንነት ማረጋገጫ የሚሆን መሰረት ለመጣል ያገለግላል፡፡ ዜጎች በተለያየ መንገድ ሀገራቸውን ካገለገሉ በኋላ አቅማቸው በሚደክምበት ጊዜ የትም ሊጣሉ አይገባቸውም፡፡ በማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም የሚደገፉበትን ሁኔታ በማመቻቸት በቂ መተዳደሪያ እንዲያገኙና ተመጣጠኝ የኑሮ ደረጃ እንዲኖራቸው ማድረግ ይገባል፡፡*

*በየትኛውም የስራ መስክ የተሰማሩ ዜጎች እስከተወሰነ የገቢ ደረጃ ከገቢያቸው የተወሰነውን መጠን እንዲያዋጡ በሕግ በመደንገግ የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራምን መደገፍ ይገባል፡፡ በመንግስት የልማት ድርጅቶችና ሲቪል ሰርቪስ ተቋም ውስጥ የሚገኙትን ብቻ ሳይሆን በግላቸው ስራ ፈጥረው የሚተዳደሩትንም በፈቃዳቸው የፕሮግራሙ አካል እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል፡፡ በግል ባለሀብቶች ተቀጥረው የሚሰሩትንም እንደዚሁ በፕሮግራሙ ውስጥ ማቀፍ ይገባል፡፡ ነጋዴዎች፣ የእደ ጥበብ ሞያተኞችና ገበሬዎች ጭምር በፕሮግራም እንዲታቀፉ የሚያስችል አቅጣጫ መዘርጋት ይኖርበታል፡፡ አሰሪና ሰራተኛ ለማህበራዊ ዋስትና የሚያስፈልገውን መዋጮ እኩል በእኩል እየተካፈሉ እንዲያዋጡ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በግዴታ እስካልሆነና የሁሉንም ፈቃደኝነት በሚያረጋግጥ መንገድ እሰከተፈፀመ ድረስ በማህበራዊ ዋስትና መዋጮ ተሳትፎ የሚደርጉ አባላት ቁጥር ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ እንደሚሄድ የታወቀ ነው፡፡ የጡረታ ዋስትና ፕሮግራም አባል የሆነ ሰው ከሞተ በኋላ በእሱ እርዳታና ኃላፊነት ስር ለነበሩ ቤተሰቦቹ የተወሰነ የክፍያ መጠን እያገኙ እንዲቆዩ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ የማህበራዊ ዋስትና አባልነት አነስተኛ የቆይታ ጊዜ በሕግ የተደነገገና በግልፅ የሚታወቅ መሆን አለበት፡፡ የጡረታ መውጪያ እድሜ የሀገሪቱን ኤኮኖሚ ማደግና የዜጎችን የጤና ሁኔታ መሻሻል እየተከተለ መለወጥ የሚገባው ሲሆን በተወሰነ ሁኔታ በሕግ ከታወቀው የጡረታ እድሜ በፊት ለሚወጡ ዜጎች የጡረታ ዋስትና ማረጋገጥ የሚያስችል አሰራር መኖር አለበት፡፡ ከፊል ጡረታና ከፊል ስራ የሚኖረበት እድልም መፈጠር ይገባዋል፡፡*

*የማህበራዊ ዋስትና ሽፋንና መጠን መወሰን የሚገባው በፕሮግራሙ የታቀፉ ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ውስጥ ባዋጡት የማህበራዊ ዋስትና መዋጮ ላይ ተመስርቶ ነው፡፡ ከዚህ ሌላ የሕዝብ ቁጥር እድገትን በተለይም ሞትንና ልደትን እንዲሁም የኢኮኖሚ ሁኔታን በማገናዘብ የፋይናንስ መሰረቱን በየጊዜው ለማስፋት ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ ዞሮ ዞሮ የማህበራዊ ዋስትና ሽፋን ዋና ዓላማ ከዜጎች ገቢና የማህበራዊ ዋስትና መዋጮ ጋር በተጣጣመ መንገድ የፕሮግራም*

ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ፣ ደረጃውን የጠበቀ የኑሮ ሁኔታ እንዲኖራቸው ማስቻል፣ ከሀገሪቱ የኢኮኖሚ እርምጃ ተጠቃሚዎች እንዲሆኑ ማስቻል ነው:: በሀገራችን ውስጥ አብዛኞዎቹ ሰራተኞች ቋሚ የማህበራዊ ዋስትና የሚያገኙት በጡረታ እድሜ ላይ ሲደርሱ ነው:: ስለሆነም የሚሰጣቸው የጡረታ የዋስትና መዋጮ ይከፍሉ በነበረበት ጊዜ የለመዱትን የኑሮ ሁኔታ የጠበቀ የኑሮ ደረጃ እንደሚያስገኝላቸው እርግጠኛ መሆን ያስፈልጋል:: በተለይ በስራ ላይ የነበራቸው የቆይታ ጊዜ ሲጨምር የጡረታ ክፍያ ምጣኔውም መጨመር አለበት:: በየጊዜው ከሚከሰቱት አዳዲስ ለውጦች ጋር የጡረታ ክፍያ መጠን የሚሻሻልበት ሁኔታ መኖር አለበት:: የጡረታም ሆነ የሌላ ማህበራዊ ዋስትና ሽፋን ዝም ብሎ የሚሰጥ ብቻ መሆን አይገባውም:: የሚሰጠው የማህበራዊ ዋስትና የዜጎችን የመስራት አቅም የሚያሻሽልና መልሶ የሚገነባ መሆን አለበት:: ይህ ዋስትና ለአዲስ ስራ የሚደረግ መልሶ ስልጠናን፣ የጤና ሁኔታን ለማሻሻልና ወደሌላ የስራ መስክ ለመሰማራት የሚያስችል ዓላማን የሚደግፍ እንዲሆን ማድረግ ይገባል:: አሁን በስራ ላይ ያለው የጡረታ ዋስትና አገልግሎት ለዜጎች የኑሮ ደረጃ መጠበቅም ሆነ መሻሻል ትርጉም ያለው አስተዋፅኦ ስለሌለው መቀየር አለበት::

ኩባንያዎችም ለሰራተኞች የጡረታ አበል የሚከፍሉበትን ሕጋዊ ሰርዓት መዘርጋት በማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራም ውስጥ ተጨማሪ ጉልበት የሚያስገኝ እጅግ ከፍተኛ ዋጋ ያለው ጉዳይ ነው:: ለዚህ ተግባር የሚያገለግል ፈንድ በመመስረት ሰራተኛው በኩባንያው ውስጥ የተወሰኑ ዓመታት አገልግሎት ከሰጡና የተወሰነ የእድሜ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ የጡረታ ዋስትና የሚያገኙበትን ቋሚ ስርዓት ማበጀት ይቻላል:: ይኸንን ማድረግ ከተቻለ ሌላው ቀርቶ አሰሪው ለመክፈል ሳይችል ሲቀር እንኳ የዋስትና ሽፋኑ አይቋረጥም::

በመንግስት ቋሚ የጤና ዋስትና ፕሮግራም በመዘርጋት ወይም በግል የዋስትና ተቋሞች አማካይነት በሕግ በተቀመጠ ግዴታ ወይም በፈቃደኝነት የጤና ዋስትና አስተዋፅኦ ያደረጉ ዜጎች ሁሉ የዚህ አገልግሎት ተጠቃሚ መሆን አለባቸው::

በመንግስት በሚዘረጋ ሰፊና የተቀናጀ ፕሮግራም ስር ለሁሉም ሰራተኞች፣ ደመወዝ ለሚከፈላቸውና ሌሎች በርካታ የሕብረተሰብ ክፍሎች እስከተወሰነ የገቢ መጠን ለጤና ዋስትና የሚከፈል የግዴታ አስተዋፅኦ መኖር አለበት:: በዚህ ፕሮግራም ውስጥ በተወሰነ ደረጃ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የዋስትና መዋጮ እንዲኖር ማድረግ ይቻላል:: የመንግስት የጤና ዋስትና ፕሮግራም ጡረተኞችን፣ ስራ አጦችን፣ ስልጠና ላይ የሚገኙትንና ተማሪዎችን እንዲያጠቃልል መደረግ ይገባዋል:: ሰራተኞች የጤና ዋስትና አስተዋፅኦ የሚያደርጉት ለዚሁ ተግባር ለተመሰረተው የራሳቸው የዋስትና ፈንድ ነው:: የዚህ ዋስትና መብት የተረጋገጠለት ማንኛውም ሰው የራሱን ሐኪም የመምረጥ ነፃ እድል ይኖረዋል:: ለጤና ዋስትና ፈንድ የሚሰጠውን ክፍያ ሰራተኞች ግማሹን ሲከፍሉ ግማሹን ደግሞ አሰሪዎች የሚከፍሉበት አሰራር መኖር አለበት:: የጤና ዋስትና ፈንዱ የሕክምና ምርመራ ዋጋን፣ የመድሃኒትና የመስተንግዶ ወዘተ. ዋጋዎችን እንዲከፍል ያስፈልጋል:: የማንኛውንም የማገገሚያ እንክብካቤና ሕክምና ዋጋ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ መክፈል አለበት:: የወሊድ፣ የቤተሰብና የቤት እንክብካቤ ዋስትና ሽፋን እንዲኖር ያስፈልጋል:: በሕመም ጊዜ እስከ 4 ሳምንታት ሙሉ ደመወዝ የሚያገኙበትና በአንዳንድ ሁኔታ ከዚያም ለበለጠ ጊዜ እንዲከፈላቸው የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ይገባል:: ከዚያ ጊዜ በኋላ በቋሚ ፈንዱ የሕመም ክፍያ ከመደበኛው ደመወዝ 50% የሚሆነውን ለአንድ ዓመት ተከታታይ የሚከፍልበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል:: በእርግጥ የጤና ዋስትና ዋጋ በየጊዜው እየጨመረ መሄዱ ስለማይቀር የተወሰኑ የአገልግሎት ዓይነቶችን በመገደብ ተጠቃሚዎቹ ራሳቸው አብዛኛውን ዋጋ እንዲሸፍኑ ማድረግ የሚያስችል አሰራር መከተልም ይገባል::

በስራ ላይ የሚደርስ አደጋን ለመከላከል፣ ከደረሰ በኋላም ለመደገፍና በስራ ምክንያት የጤና ችግር ሲያጋጥም ለመርዳት ቋሚ የአደጋ ዋስትና ፕሮግራም በሕግ መመስረት ተገቢ ነው:: ሠራተኞችና ገበሬዎች (ዘመናዊ እርሻ መስፋፋት በሚችልበት ጊዜ አደጋዎች ስለሚኖሩ) የዚህ ፕሮግራም ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን ሕጋዊ ግዴታ ማውጣት ይገባል:: ሌሎች የራሳቸውን ስራ ፈጥረው የሚንቀሳቀሱ ዜጎችም በፈቃደኝነት የዚህ ዋስትና ፕሮግራም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማድረግ ይቻላል::

በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ተማሪዎችና በመዋዕለ ሕጻናት ውስጥ የተመዘገቡ ሕፃናትም እንዲሸፈኑ ማድረግ ይገባል፡፡ ዋናዎቹ የአደጋ ዋስትና አገልግሎት ሰጪዎች የሞያና የንግድ ማህበራት ሊሆኑ ይገባል፡፡ እነዚህ አካላት በተወሰነ ሞያ ወይም ንግድ የተሰማሩና በተወሰነ አካባቢ የሚገኙ አባሎች ያሏቸው ስለሆነ በእነሱ መሰጠት አለበት፡፡ የዋስትናው ፈንድ የሚገኘው አሰሪዎች እንዲከፍሉ በሕግ ከተጣለባቸው ግዴታ ብቻ እንዲሆን ሕግ ማውጣት ያስፈልጋል፡፡ የክፍያ ጥያቄ የሚነሳው በስራ ወቅት የአካል ጉዳት ከደረሰባቸውና የሞት አደጋ ካጋጠማቸው ወገን ወይም በዋስትና ፕሮግራሙ ውስጥ ከሚገኙት መካከል በስራ ምክንያት ሕመም ወይም ሞት ካጋጠማቸው በኩል ነው፡፡ ወደ ስራ በሚደረግ ጉዞ ወይም ከስራ መልስ አደጋ ሲያጋጥም በስራ ላይ እንደደረሰ አደጋ የሚቆጠርበትን ስርዓት መከተል ይገባል፡፡

በዋስትናው የታቀፈ ሰው በአደጋ ምክንያት ስቃይ ሲያጋጥመው የሕክምናውን ሙሉ ወጪ የአደጋ ዋስትና ፈንዱ እንዲሸፍን ማድረግ ይገባል፡፡ ጉዳት የደረሰበት ሰው ለመስራት የማይችል ከሆነ የጉዳት ገንዘብ ሊከፈለው ይገባል፡፡ በአደጋው ምክንያት ለሕይወቱ ገቢ መፍጠር የማይችል ወይም ሞት የሚያጋጥመው ከሆነ የዋስትና ፈንዱ የጡረታ ወይም የሕይወት ዋጋ መክፈልና በሰውየው ኃላፊነትና ድጋፍ ስር ለነበሩ ቤተሰቦች ጡረታ መክፈል እንዲችል የሚያደርግ ስርዓት ያስፈልጋል፡፡ እንደሌሎቹ የዋስትና ሽፋኖች አጠቃላይ ገቢ ሲጨምር አብረው ማደግና መሻሻል የሚችሉ አሰራሮች መኖር አለባቸው፡፡ በዚህ ዋስትና ፕሮግራም ውስጥ የሞያ ማሻሻያ ስልጠና መስጠትና የስራ እድል የማፈላለግ ድጋፍ ማድረግ ሊካተቱ ይገባል፡፡ የሞያና የንግድ ማህበራት የአደጋ መከላከያና ከስራ ጋር የሚፈጠሩ በሽታዎች መቆጣጠሪያ ሕግ እንዲወጣ፣ ተፈፃሚነቱንም የሚያረጋግጥ የቁጥጥር ስርዓት በተለያዩ የስራ ተቋሞች እንዲዘረጋ በተቀናጀ ሁኔታ መንቀሳቀስና ግፊት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ሕፃናትን ማሳደግና ማስተማር ለቤተሰብ ከፍተኛ የፋይናንስ ጫና የሚፈጥር ነው፡፡ ይኸንን ጫና ለመቀነስ ሕፃናት የተወሰነ እድሜ ገደብ እስኪደርሱ ለማንኛውም ወላጅና አሳዳጊ የሕፃናት ማሳደጊያ ድጋፍ የሚያገኙበት ስርዓት በመንግስት መመቻቸት አለበት፡፡ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ወላጆች የሚያገኙት የሕፃናት ማሳደጊያ ድጋፍ አነስተኛ ሆኖ ዝቅተኛ ገቢ ወይንም ምንም ገቢ ለሌላቸው ወላጆች የሚሰጠው የድጋፍ መጠን ከፍ ያለ መሆን አለበት፡፡ ድጋፉን ከታክስ ነፃ ማድረግን ጨምሮ በተለያየ መንገድ ሊሰጥ የሚችል መሆን ይኖርበታል፡፡ የሕፃናት ማሳደጊያ አበል በየወሩ ለመጀመሪያዎቹ ጥቂት ወራት ሊሰጥ የሚችልበትን አሰራር መከተል ይገባል፡፡ መጠኑ እንደሀገሪቱ ኢኮኖሚ አቅም እየታየ የሚወሰንና ኢኮኖሚው ሲያድግ ሊሻሽል በሚችልበት ሁኔታ የሚሻሻል እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ ወይንም እንደወላጆች የገቢ መጠን የተለያየ ክፍያ እንዲሆን ማድረግ ይቻላል፡፡ ከተወሰነ ጊዜ በኋላ የሚቋረጥ እንደሚሆንና ወደሌሎች የዋስትና ሽፋኖች ሽግግር የሚደረግበት ሁኔታ እንደሚኖር አድርጎ ማቀድ ይቻላል፡፡

የጦር ጉዳተኞች እርዳታ ዋና ተግባር የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው፣ ወላጆቻቸውን ላጡና አሳዳጊ ለሌላቸው፣ የትዳር ጓደኞቻቸውን ለተነጠቁ፣ ጧሪ ቀባሪ ላጡና ሀዘን ላጋጠማቸው ቤተሰቦች ቢያንስ በገንዘብ የሚካሱበትን ሁኔታ መፍጠር ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በጦርነት የአካል ጉዳት ላጋጠማቸው የማገገሚያ ሕክምና፣ ስራ ማስጀመሪያና የመሳሰሉትን ድጋፎችም ማድረግ ይገባል፡፡ በእነዚህ ወገኖች ኃላፊነትና እንክብካቤ ስር ለነበሩ ቤተሰቦችም እንክብካቤና ድጋፍ ማድረግን የሚጨምር መሆን አለበት፡፡

ማንኛውም የሀገሪቱ ዜጋ በከባድ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ ምክንያት ለአስከፊ ችግር በሚጋለጥበት ጊዜ የማቋቋሚያ እርዳታ ማድረግ የሚያስችል የማህበራዊ ርዳታ ፕሮግራም መዘርጋት ይገባል፡፡ የዚህ ዓይነቱ እርዳታ አብዛኛው መጠን በክልልና የአካባቢ የመንግስት አካላት ደረጃ መሸፈን ያለበት ሲሆን የሕዝብም ተሳትፎ እንዲጨመርበት አድርጎ መቀየስ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህ ዓይነቱ እርዳታ የሚያገለግል ሕግ በፌዴራልና በክልል መንግስታት እንዲወጣና ስራ ላይ እንዲወል ማድረግ ይገባል፡፡

የማህበራዊ ዋስትና ፕሮግራሞች ጥቅም በሌሎችም በርካታ መስኮች የሚገለፅበትን አቅጣጫ መከተል ይገባል፡፡ ለምሳሌ አቅመ ደካሞችን ለማቋቋምና በስራ የተሰማሩ እናቶችን ለመጠበቅ የሚረዳ የሕግ ሰርዓት በመዘርጋት ሊገለፅ ይችላል፡፡

# 2. ትምህርትና ሥልጠና

## 2.1 የትምህርትና ሥልጠና አስፈላጊነት

ትምህርት የአንድ ኅብረተሰብ አባላት በልማት ሂደት ውስጥ በብቃት መሳተፍ ይችሉ ዘንድ እውቀት፣ ክሂልና አቅም የሚሰጥ መሣሪያ በመሆኑ ከሰብአዊ ልማት አመልካቾች አንዱና ዋነኛው ነው። ከአንድ አገር ሕዝብ የብዙዎች መማርና ከፍተኛ ሥልጠና ማግኜት ከከፍተኛ የገቢ መጠንና ላቅ ካለ የኑሮ ደረጃ ይዞታ ጋር ይዛመዳል። በአገራችን በስፋት የተንሰራፋውን ድህንትን ለመቀነስ ከተፈለገ ትኩረት ማግኘት ካለባቸው ዋና ዋና ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የትምህርትና የሥልጠና አገልግሎት ነው። ትምህርትና ሥልጠና የሰዎችን ችሎታ ለማሻሻል፣ ብሎም ኑሮን መልክ ለማስያዝ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው። ሰዎች ከተማሩ የተሻለ ገቢ ማግኘት ከመቻላቸውም በላይ የአሁኑንና የወደፊቱን ትውልድ ኑሮ እንዲሻሻል ማድረግ ይችላሉ። ሰዎች መብታቸውን አውቀው እንዲያስከብሩ፣ ከአካባቢያዊ ለውጥ ጋር እንዲላመዱና አካባቢን እነዲንከባከቡ ትምህርት ወሳኝ ነው።

የትምህርትና ሥልጠና አገልግሎት እኩል ዕድል ማግኘት መሠረታዊ ሰብአዊ መብት ነው። ትምህርትና የሥልጠና አገልግሎትን በተመለከተ ለዜጎች ሁሉ እኩል ዕድል መስጠት ይቻላል፣ ይገባልም። ሰዎች ከተማም ይኑሩ ገጠር፣ ዳር አገርም ይኑሩ መሃል፣ ደጋም ይኑሩ ቆላ፣ በዘር፣ በሀብት፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ፣ አድልዎ ሳይደረግባቸው የትምህርትና የጤና አገልግሎት እኩል ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፣ አለባቸውም። በመሆኑም ትምህርትና የሥልጠና አገልግሎትን በስፋትና በጥራት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ማሰራጨት ድህነትን ለመቀነስ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው።

## 2.2 የሀገራችን ትምህርት አንፃራዊ ሁኔታ

በ1992 ዓ.ም የነበረውን የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪቃና የእስያ አገሮችን ሁኔታዎች በንጽጽር ማየት በትምህርቱ ዘርፍ ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል። በአገራችን ዕድሜአቸው ለትምህርት ከደረሱ ሕፃናት መካከል የመማር እድል ያገኙት ጥቂቶች ናቸው፤ በአንደኛ ደረጃ 43 ከመቶ፤ በሁለተኛ ደረጃ 12 ከመቶና በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ደግሞ 1 ከመቶ ብቻ ናቸው። በሌሎች አፍሪካ አገሮች የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎችን ብቻ ብንመለከት ኬኒያ 85 ከመቶ፣ ሱዳን 51 ከመቶና፣ ግብፅ 101 ከመቶ ሲሆን እንዲሁም የአፍሪካ አማካይ ደግሞ 80 ከመቶ ነው። እንደዚሁም ከ35 ዓመታት በፊት የአንደኛ ደረጃ ተማሪዎች ብዛት በሲንጋፖር 85 በመቶ፣ በሆንግ ኮንግ 78 ከመቶ፣ በኮሪያ 80 ከመቶ፣ በፊሊፒንስ 113 በመቶ፣ በማሌዥያ 90 በመቶ፣ በታይላንድ 78 ከመቶና በኢንዶኔዢያ 72 በመቶ ነበር።

በአገራችን እድሜአቸው ከ15 ዓመት በላይ የሆኑ ማንበብና መፃፍ የማይችሉ ዜጎች ከወንዶቹ 57 ከመቶና ከሴቶቹ 68 ከመቶ ሲሆኑ ከጠቅላላው ደግሞ 63 በመቶ ናቸው። በኬንያ ደግሞ ከወንዶቹ 12 ከመቶና ከሴቶቹ 25 ከመቶ ሲሆኑ ከጠቅላላው ደግሞ 19 በመቶ ብቻ ናቸው። በሱዳን ደግሞ ከወንዶቹ 31 ከመቶና ከሴቶቹ 55 ከመቶ ሲሆኑ ከጠቅላላው ደግሞ 43 በመቶ ናቸው። እንደዚሁም በግብፅ ከወንዶቹ 34 ከመቶና ከሴቶቹ 57 ከመቶ ሲሆኑ ከጠቅላላው ደግሞ 45 በመቶ ናቸው። በጠቅለላው በአፍሪቃ ደግሞ ከወንዶቹ 31 ከመቶና ከሴቶቹ 49 ከመቶ ሲሆኑ ከጠቅላላው ደግሞ 40 በመቶ ናቸው።

## 2.3 በትምህርቱ ዘርፍ የታዩ ችግሮች

በኢትዮጵያ የትምህርት ሁኔታ በሁሉም መመዘኛዎች ሲገመገም ተማሪዎች ተገቢውን ትምህርት ቀስመው የችግር ፈቺነት ባሕሪይንና ችሎታን እንዲያጎለብት አስችሏል ለማለት አያስደፍርም። የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል፣ በልማት እድገት ላይ ቁልፍ ሚና ለመጫወት፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን በማዳበር ሀገሪቷን ወደተሻለ የእድገት ደረጃ ለሚሸጋገር በሚያስችል አቅጣጫ ላይ የሚገኝ አይደለም።

በሥርጭቱም ረገድ ዕድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱት መካከል በአንደኛ ደረጃ የሚሳተፉት ጥቂቶቹ ናቸው:: ከነዚህም ከዝቅተኛ ክፍል አቋርጠው ወደ ማይምነት የሚመለሱት በርካታ ናቸው:: በክልሎች መካከል ያለው ተሳትፎ ሲታይም ሥርጭቱ ፍትሃዊ አይደለም:: በአጠቃላይ ሰፊ የማህይምነት ችግር መኖሩ በግልጽ ይታያል:: የሁለተኛ ደረጃና የከፍተኛ ትምህርት ችግሮችም እንደዚሁ የጎሉ መሆናቸው ይታወቃል:: በተለይ በእነዚህ ደረጃዎች የትምህርት ተገቢነትና ጥራት እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ላይ ይገኛል:: በከፍተኛ ትምህርት በሳል ችግር ፈቺ ምሁራንን በማፍራትም ሆነ ለሕዝብ ጥቅምና ለአገር እድገት የሚጠበቀውን ያህል የጥናትም ሆነ የምርምር ውጤት ጎልቶ አልታየም::

የትምህርት ዕድል ማግኘትን በተመለከተ በከተሞችና በገጠሩ መካከል ሠፊ ልዩነት አለ:: በአዲስ አበባና በሌሎች ከተሞች አብዛኞቹ ሕፃናት ማለት ይቻላል የትምህርት ዕድል ያገኛሉ:: በሌላ በኩል ግን በገጠር አካባቢ ከሚኖሩት ዕድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱ ሕፃናት ውስጥ 10 በመቶ ያህሉ ብቻ ናቸው የመማር ዕድል ያገኙት:: የትምህርት ዕድል በማግኘት ረገድ በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው ልዩነትም ሠፊ ነው:: በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከተመዘገቡ ተማሪዎች ውስጥ 60 ከመቶ ወንዶች ሲሆኑ ሴቶች ደግሞ 40 ከመቶ ብቻ ናቸው::

የትምህርት ቤቶች ብቃት በቁጥርም ይሁን በጥራት ገና በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ይገኛል:: ተመዝግበው ትምህርት ከጀመሩ ተማሪዎች መካከል 22 በመቶ የሚሆኑት ሦስተኛ ክፍልን ሳያጠናቅቁ ትምህርታቸውን ያቋርጣሉ:: የመምህርናንና የተማሪ ምጥነት አንድ መምህር ለሃምሳ ተማሪዎች አካባቢ ነው:: በርካታ መምህራን በቂ ሙያዊ ሥልጠና ስለሌላቸው የትምህርቱ ጥራት አደጋ ላይ ነው::

የብዙ ትምህርት ቤቶች መማሪያና ቁሳቁስ የተሟሉ አይደሉም:: የመማሪያ ክፍሎች በቁጥርም ሆነ በጥራት በቂ አይደሉም:: ለተማሪዎችና ለመምህራን መቀመጫና ጠረጴዛ (ደስክ)፣ ጥቁር ሰሌዳ፣ መስኮትና በር ተሟልተው የሚገኙባቸው ትምህርት ቤቶች እጅግ በጣም ጥቂት ከመሆናቸው የተነሳ እንደ ብርቅ እየታዩ ነው:: የውሃ አቅርቦት፣ መፀዳጃ ቤቶች፣ የስፖርት ሜዳዎች የመሳሰሉት በብቃት የሉም:: ቤተ መጻሕፍት፣ ላቦራቶሪ፣ የትምህርት መረጃዎች ማዘጋጃ፣ ወርክሾፖች፣ የመሳሰሉት ጨርሶ የማይታወቁባቸው ትምህርት ቤቶች በርካታ ናቸው:: በመሆኑም የትምህርት ጥራት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አሳድሯል::

በአገራችን የተከሰተው ፈጣን የሕዝብ ቁጥር እድገት ዕድሜያቸው ለትምህርት ለደረሱ ልጆች ትምህርትን ለማዳረስ ፈታኝ ሁኔታ ነው:: ከዚሁ ጋር ተያይዞም መምህራንን በብዛት፣ በጥራትና በብቃት ማሠልጠን ወሳኝ ጉዳይ ነው:: በሁለተኛ ደረጃና በከፍተኛ ትምህርት የሚማሩ ወጣቶች መጠን ዝቅተኛ በመሆኑም በልዩ ልዩ የሥራ መስኮች በተሠማሩት ሠራተኞች ብቃትና ጥራት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ አሳድሯል::

ወጣቶችና ጎልማሶች ትምህርት ቤት ገብተው አስፈላጊውን እውቀት እስካላገኙ ድረስ በኢትዮጵያ የሰብአዊ ልማት እርምጃ ሊፋጠን አይችልም:: ድህነት፣ ሥራ አጥነትና ፈጣን የሕዝብ ብዛት እድገት ባለበትና ትምህርት ባልተስፋፋበት አገር የመሃይምነት መጠን እየሠፋ ይሄዳል:: ይህ ከሆነ ደግሞ የሕዝቡ ምርታማነት በከፍተኛ መጠን ያሽቆለቁላል:: ቀስ በቀስም እየሠፋና ሥር እየሰደደ ይሄድና ለማስተካከል እጅግ አዳጋች ከሚሆንበት ደረጃ እንዳይደርስ ያሰጋል::

በአሁኑ ጊዜ በአገራችን በሥራ ላይ የተሰማራው የሰው ኃይል ያልሠለጠነና ዝቅተኛ ምርታማነት ያለው ነው:: አብዛኛዎቹ ዕድሜያቸው ለትምህርት የደረሱ ልጆች እውቀት ለመቅሰም ወደ ትምህርት ቤት አይሄዱም:: ትምህርት ቤት ገብተው እስከተወሰነ ደረጃ ተምረው የሚመረቁ ተማሪዎችም ቢሆኑ የአገራችንን ፍላጎት የሚያሟላ ተግባራዊ ዕውቀት ወይም ሙያ ይዘው አይወጡም:: ይህም ክስተት የአገራችንን የትምህርት ተቋማት ሥራ አጥና ለሥራ ብቃት የሌላቸው ዜጎች ማምረቻ አድርጓቸዋል:: ይህ ሁኔታም፣ ሥርዓተ ትምህርቱን በአስቸኳይ እንደገና የመገምገምን አስፈላጊነት በግልጽ ያመለክታል:: በሁሉም ደረጃዎች የሚሰጠው ትምህርት በሕብረተሰቡ ችግሮችና ፍላጎቶች ላይ የተመሠረተ ፈጣን እድገት ማምጣት የሚችል መሆን ይኖርበታል::

በትምህርት በኩል የታዩ ችግሮችን ለመፍታትና ለመለወጥ ተስማሚ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ ማስፈለጉ አያጠያይቅም:: ፖሊሲው ከሕፃናት አስተዳደግ ጀምሮ እስከ ከፍተኛ ትምህርት

ድረስ ልዩ ትምህርትን ጨምሮ ያለውን መደበኛና መደበኛ ያልሆነ ትምህርት አጠቃላይና ዝርዝር ዓላማዎችን እንዲሁም ሥልቶችንና ተግባሮችን አጠቃልሎ በሚያሳይ መልኩ መቀረፅ አለበት፡፡ ስለሆነም የአገርና የሕዝብ ችግሮችን ለመፍታት የተዘጋጀና ሰብአዊና አገራዊ ኃላፊነት የሚሰማው፣ ዴሞክራሲዊና ሰብአዊ አመለካከቱ የተስተካከለ፣ የማምረትና የመመራመር አቅሙ የዳበረና ብሔራዊ ስሜት ያለው ዜጋ ለማዘጋጀት የሚያስችል አጠቃላይ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መዘጋጀት አለበት፡፡

ትምህርትን በተመለከተ ችግሩ ግንዛቤ አግኝቶ አዲስ ፖሊሲ ለማዘጋጀት ተሞክሯል፡፡ የፖሊሲ ቀረጻው አካሄድ ግን በጎ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ ይችሉ የነበሩ ወገኖችን በብቃት አላሳተፈም፡፡ ይህም ባለመሆኑ አዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ከመጀመሪያው ጀምሮ ችግር ሊያመጣ እንደሚችል የተለያዩ ወገኖች በተለይም መምህራን ጠቁመው ነበር፡፡ ግን አዳማጭ አላገኙም፡፡ ጠቃሚና ደካማ ጎኑ በተግባር ሳይፈተሸ፣ በቂ ውይይትና ዝግጅት ሳይደረግ፣ አላስፈላጊ የሆነ የማደናገሪያ ፕሮፓጋንዳ በመንዛት ፖሊሲውን በህዝብ ላይ ለመጫን የሚደረገው ሩጫ ውጤት አላስገኘም፣ አያስገኝምም፡፡

አሁንም ብዙ ቀውስ ከማስከተሉ በፊት ምሁራንን፣ መምህራንን፣ ወላጆችንና ሌሎች የሚመለከታቸውን አካሎች ያሳተፈ ግልጽና ነፃ ውይይት ተደርጎ አስፈላጊው ክለሳ መደረግ ይኖርበታል፡፡ የትምህርት ፖሊሲ ከገዢው ፓርቲ ዕድሜ አልፎ የብዙ ትውልዶችን የወደፊት ዕድል የሚወስን ብሔራዊ ጉዳይ መሆኑ መዘንጋት የለበትም፡፡ ችግሩ አሁኑኑ ካልተቀለበሰ መዘዙ የከፋ ይሆናል፡፡

## 2.4 ትምህርት ለኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋጽኦ

ካፒታል፣ ጉልበትና መሬት ዋና ዋናዎቹ የልማትና የእድገት ግብዓቶች ናቸው፡፡ ከሦስቱም ግን በማምረት ሂደት ውስጥ ከፍተኛ ወሳኝነት ያለው ግብአት ጉልበት ነው፡፡ በዚህ ባለንብት በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ጉልበትን እንደ አንድ ዋነኛ የምርት ሂደት ግብአት በመመልከት አስፈላጊውን ትኩረት መስጠት ከመቸውም ጊዜ ይበልጥ አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን ባለንበት ዘመን የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ በእውቀት የሚመራ በመሆኑ የተማረ የሰው ኃይል እጅግ ወሳኝ እና ምትክ የሌለው ነው፡፡

ቀደም ብሎ አንድ አገር ርካሽና ያልሰለጠነ የሰው ኃይል ስላላት እነዚህ ነገሮች ከሌሏቸው አገሮች የተሻለ ትጠቀማለች ተብሎ ይታሰብ ነበር፡፡ እውነታው ግን እንዲህ ዓይነቱ ያልተማረና ያልሰለጠነ የሰው ኃይል ለአንድ አገር ሸክም መሆኑን ያሳያል፡፡ የሰው ኃይልና ካፒታል ለልማት እጅግ ጠቃሚና ቁልፍ ጉዳይ መሆኑን፣ በተወሳሰበው የልማት ጎዳና ተጉዘው ከነበሩበት ኋላቀርነት በመውጣት የበለፀጉና ከቴክኖሎጂ አምባ የደረሱ አገሮች የኢኮኖሚ ታሪክ ያስረዳል፡፡ መሣሪያዎችን የሚያንቀሳቅሱ፣ ሲበላሹ የሚጠግኑ እንዲሁም ከአካባቢ ሁኔታዎች ጋር የሚስማሙና ተመጣጣኝ አማራጭ ቴክኖሎጂዎችን የሚያዳብሩና የሚፈጥሩ በደንብ የሰለጠኑ ሰዎች ያስፈልጋሉ፡፡ በእርግጥ ከነዚህ ተግባራት አንዳንዶችን በሥራ ሂደት ለመማር ይቻላል የሚሉ ወገኖች ይኖሩ ይሆናል፡፡ ዳሩ ግን የዚህ ዓይነት ባሕሪይ ያለው ክሂል አገራችንን ጠመዝማዛ በሆነው የልማት ጎዳና ተጉዛ ራሷን ችላና ተደላድላ ለመቆም የሚያስችላትን ተስማሚና ተመጣጣኝ የቴክኖሎጂ መሠረት ለማጎናፀፍ የሚያስችል ኃይል የለውም፡፡

ትምህርትን የምርት መሣሪያ በማድረግ እንዲሁም ምርትን የትምህርት መሣሪያ በማድረግ ሀብትን መንከባከብና በተገቢው መንገድ መጠቀም የሚያስችል የሰው ኃይል አስፈላጊ ነው፡፡ የዜጎችን የማመዛዘን፣ የመፍጠርና የመመራመር ችሎታን በማዳበር፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት፣ መስረጽና ማደግ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችል የሰው ኃይል ማግኘት ለምንመኘው እድገት ቁልፍና ወሳኝ ነው፡፡ አካባቢውን የማወቅ፣ የመገንዘብ፣ የመመዘን፣ የመገምገምና የመተንተን ብሎም የመለወጥ ችሎታ ያለው የተማረና የሰለጠነ የሰው ኃይል ለሀገራችን ኢኮኖሚም እጅግ አስፈላጊ ሆነ ለሁለንተናዊ እድገታችን እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡

## 2.5 የኢዴፓ የሥርዓተ ትምህርት ሀሳቦች

*የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ችግሮች ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ አንደኛ በትምህርቱ ስራ ቀጥተኛ ተሳትፎ ያላቸው መምህራን፣ የልጆቻቸው የሰደፊት እጣ ፈንታ የሚመለከታቸው ወላጆችና የጉዳዩ ባለቤት የሆኑት ተማሪዎች አስተያየት እንዲሰጥበት ተደርጎ በሕዝብ ተሳትፎና ፍላጎት ላይ በተመሰረተ ጥናትና ግምገማ የተዘጋጀ አለመሆኑ ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ የሀገሪቱን ችግር ሊገታ በሚችልበት መንገድ ሳይሆን የአንድ ፖለቲካ ቡድን አስተሳሰብ ማስፋፊያ ሆኖ በሚያገለግልበት መንገድ የተዘጋጀ መሆኑ ነው፡፡ ሶስተኛው ቀደም ሲል የነበሩ የትምህርት ጥራት ችግሮች እንዲወገዱ ሳይሆን እንዲባባሱ በሚደርግ መንገድ መዘጋጀቱ ነው፡፡ አራተኛ ሰርጭቱን ሚዛናዊና ፍትሐዊ ለማድረግ በሚያስችል መንገድ አለመዘጋጀቱ ነው፡፡ በዚህም ምክንያት በመንግስት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መሆን ከመጀረበት ጊዜ አንስቶ እስካሁን ድረስ በከፋ ቀውስ ውስጥ ገብቶ የሀገሪቱን ወጣቶች የወደፊት እጣ ፋንታ እያበላሸ ነው፡፡ በስራ ላይ ሲውል ጉዳቱን አደገኛነቱ ጎልቶ ቢወጣም ሁኔታን ለማረም በመንግስት በኩል ዝግጁነት የለም፡፡ ለምሳሌ ፖሊሲውን ለማስፈፀም ይረዳሉ ተብለው እየተሞከሩ ባሉት የመማሪያ ክፍል መኔጅሜንትና የትምህርት መስጫ ቋንቋ ስርዓቶች ከባድ ተቃውሞ ከየአቅጣጫው እየተነሳ ቢሆንም የአፈፃፀም እንጂ የፖሊሲ ችግሮች አይደሉም የሚል መልስ እየቀረበ ሁነኛ መፍትሔ ሊገኝ አልቻለም፡፡ የመማሪያ ክፍል ማኔጅሜንትን አስመልክቶ ከሚነሱ ተቃውሞች መካከል ሰልፍ ኮንቴይንድ የሚለው አሰራር አንዱ ነው፡፡ ይህ አሰራር በትምህረት ጥራት ላይ ጉዳት እያስከተለ መሆኑ በተግባር የተረጋገጠ መሆንም መንግስት መፍትሔ ለመስጠት አልፈለገም፡፡ ከዚህ አሰራር ሌላ በስነ ትምህርት የተደገፉ በርካታ አማራጮች ማለትም በዲፓርትሜንት ላይ የተመሰረተ የትምህርት አሰጣጥ፣ ብዙ የክፍል ደረጃዎችን ባጣመረ አሰራር ላይ የተመሰረተና የመሳሰሉ የክፍል ማኔጅሜንት ዘዴዎች ቢኖሩም መንግስት እኔ ያልኩት ካልሆነ ብሎ ድርቅ እንዳለ ነው፡፡*

*በትምህርት መስጫ ቋንቋ ደግሞ የአፍ መፍቻ ቋንቋ እስከየትኛው የክፍል ደረጃ ይሰጥ፣ የክልል ቋንቋ ከየት ተጀምሮ የት ድረስ ይቀጥላል፣ ብሔራዊ የስራ ቋንቋ ከየት ጀምሮ የት ድረስ ይዝለቅ፣ የትኛው የማስታሪያ ቋንቋ በየትኛው የክፍል ደረጃ የጀምር፣ የትኛው እንደ አንድ ትምህርት ይሁን ወዘተ. የሚሉት ጉዳዮች ከሕዝቡ ፍላጎትና ከጥናት ውጭ በመንግስት በኩል የፖለቲካ ውሳኔ የተሰጠባቸው በመሆኑ የሀገሪቱ የትምህረት ጥራት ችግር እየተባባሰ ቀጥሏል፡፡ ከዚህ ሌላ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ልቀቂያ ፈተና በየትኛው ክፍል ደረጃ ይሰጥ፣ ለዚህ የሚያስፈልገው ዝግጅትና ቅድመ ሁኔታ እስኪሟላ የሚሰደው የሽግግር ጊዘ ምን ያህል ይሁን ወዘተ. የሚሉት ችግሮች እንደ ሆነው በመንግስት ትዕዛዝ ብቻ ነገሮች እንዲራመዱ በመወሰኑ የሀገሪቱ ትምህርት ከባድ ቀውስ ውስጥ ገብቷል፡፡ በትምህርቱ ስራ ዋነኛ ተዋናይ የሆኑት መምህራን በሞያቸው ነፃ ማህበር እንዳያቋቁሙና ለትምህርቱ ጥራት ተገቢ ሚና እንዳይጫወቱ ከፍተኛ ፖለቲከዊ ጫና ሰለሚደርስባቸው ለሀገራችን ማበርከት የሚገባቸውን የሞያና የዜግነት አስተዋፅኦ በሚገባ ሲያበረክቱ አልቻሉም፡፡ በዚህም የተነሳ ትምህርት ቤቶች ነፃ የአካዳሚክ ስፍራዎች የትውልድ አስተሳሰብ የሚቀረፅባቸው ተቋሞች መሆናቸው ቀርቶ የአንድ ፖለቲካ ቡድን ርዕዮተ አለም ማስፋፊያ መዋቅሮች የትርምስ ቦታዎች ሆነዋል፡፡*

*ኢዴፓ እነዚህን ችግሮች ከመሰረቱ አስወግዶ የሀገሪቱ ወጣቶች መልካም ዜጋ ሆነው እንዲታነፁ የሚያደርግ አማራጭ ስርዓተ ትምህርት መዘጋጀት አለበት ብሎ ያምናል፡፡ ለሀገሪቱ የሚያስፈልጋት ስርዓተ ትምህርት አላማ የሞያ ብቃትና ችሎታ ያለው፣ ነፃ አስተሳሰብና በራስ የመተማመን መንፈስ ያለው፣ የስራ ፍቅርና የመፍጠር ችሎታ ያለው፣ ሀገሩን የሚወድና ለሰው ልጅ ከበሬታ ያለው ብቁ ዜጋ ማፍራት መሆን አለበት ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡*

*አሁን ያለው ስርዓተ ትምህርት ነፃ አስተሳሰብ ያለውና በራሱ ምርጫ የሚፈልገውን አምነት ለመከተል ሆነ የማይፈልገውን ለመተው የሚችል ዜጋ የሚያፈራ ሳይሆን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የሚለውን የአንድ ፓርቲ ርዕዮተ አለማዊ እምነት በግድ እየተጋተ እንዲወጣ የሚያደርግ ስለሆነ መቀየር አለበት እንላለን፡፡*

*ለትምህርቱ ጥራት መጠበቅ የመጀመሪያው እርምጃ መወሰድ ያለበት በፖሊሲ ቀረፃ ላይ በመሆኑ የትምህርት ፖሊሲውን በመቅረፅና ይዘቱን በማሟላት ረገድ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ ወላጆችና መላ ዜጎች ሙሉ ተሳትፎ ሊያደርጉ ይገባል ብለን እናምናለን፡፡ የትምህርት አስተዳደሩም ከፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነፃ ሆኖ በሕዝብና በባለሞያዎች፣ በመምህራና በተማሪዎች ተሳትፎ ላይ*

*መመስረት አለበት እያለልን ከዚህ እምነት በመነሳት ዝርዝር የሥርዓት ትምህርት አማራጭ ሀሳቦችን በሚከተለው ሁኔታ አቅርበናል፡፡*

*ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የራሱን ስብዕና ለማዳበርና የሚማርበትን ስፍራ፣ የሚማረውን ሞያና የሚሰማራበትን የስራ መስክ በነፃነት ለመምረጥ የሚያስችል መብት ሊኖርው ይገባል፡፡ ይህ መብት የሰው ልጅ መሰረታዊ መብት ነው፡፡ በመሆኑም መንግስት ከዜጎች ችሎታና ፍላጎት ጋር የተጣጣመ ትምህርት ለማቅረብ የሚያስችል እድል እንዲኖር የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ የዚህ ዓይነቱ የትምህርት እድል መገኘት ያለበት ለሳምንታት፣ ለወራትና ለዓመታት ብቻ ሳይሆን ዜጎች መማር እስከፈለጉና እስከቻሉ ጊዜ ድረስ በመላ ሕይወት ዘመናቸው ነው፡፡ እንዲህ ዓይነት የትምህርት እድል የሚያገኙ ዜጎች በሀገሪቱ የዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታና እድገት ሂደት ውስጥ የበኩላቸውን ድርሻ በብቃት ሊወጡ ይችላሉ፡፡*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው የትምህርት እድል ያላገኘ በመሆኑ ለብዙ ዓይነት ችግርና ኋላቀርነት የተጋለጠ ነው፡፡ በመሆኑም ሕዝቡን ከዚህ አጠቃላይ ኋላቀርነት ለማውጣት የሚቻለው የዜጎችን የመማር እድል በማስፋት እንደመሆኑ ለትምህርት የተለየ ትኩረት መስጠትና ከፍተኛ ጥረት ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ለአጠቃላይ የሀገር ልማት ከሚመደበው ገንዘብ፣ የሰው ኃይልና ጊዜ ውስጥ የትምህርት ድርሻ በየጊዜው እየጨመረ እንዲሄድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡*

*የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው በአስከፊ ድህነት ውስጥ የወደቀ በመሆኑ ለትምህርት የሚያስፈልገውን ወጪ ለመሸፈን አቅም የለውም፡፡ በመሆኑም አሁን ባው ተጨባጭ ሁኔታ ትምህርትን ለዜጎች የማዳረስ ኃላፊነት በዋናነት የፌዴራልና የክልል መንግስታት መሆኑ የግድ ነው፡፡ አቅም ያላቸው የግል ባለሀብቶችም በዚህ መስክ ተሳትፎ የሚያደርጉበት እድል ክፍት እንዲሆን ያስፈልጋል፡፡ ሕዝቡ ደግሞ በትምህርት ቤቶች ሕንፃ ግንባታ፣ በትምህርት ቤቶች አስተዳደርና እንክብካቤ ተግባር እንደ አቅሙ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ ተሳትፎ ማድረግ የሚችልበት ስርዓት መኖር አለበት፡፡ መንግስት በአንድ በኩል የግሉ ሴክተር ትምህርትን በማስፋፋት ጉልህ ሚና እንዲጫወት ምቹ ሁኔታ እየፈጠረ በሌላ በኩል የግሉ ሴክተር ለጊዜው ሊገባባቸው በማይፈልግ የትምህርት ዘርፎችና ሊደርስባቸው በማይችል አካባቢዎች ትምህርትን የማስፋፋት ተኩረት ሊሰጥ ይገባል፡፡*

*እድሜአቸው 6 ዓመት የሆኑ ዜጎች ቢያንስ እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ እንዲማሩ የሚያስችል ሕጋዊ ግዴታ መደንገግ በሀገሪቱ ውስጥ ትምህርት እንዲስፋፋ መወሰድ ካለባቸው እርምጃዎች መካከል አንዱና የመጀሪያው ነው፡፡ በመንግስት ትምህርት ቤቶች ለሚማሩ ዜጎች ትምህርት በነፃ እንዲሰጣቸው የሚያስችል ሕጋዊ ሥርዓት መፍጠር ይገባል፡፡ ይህ አቋም እስከ 8ኛ ክፍል ድረስ እንዲማሩ ለሚጣልባቸው ግዴታ ማካካሻ ሆኖ የሚታይ ሳይሆን ከዜጎች በሚሰበሰብ ግብር ተገንብቶ ስራውን በሚያካሂድ የመንግስት ትምህርት ቤት ውስጥ በነፃ መማር መብታቸው ከመሆኑ አንፃር በመነሳት የሚፈፀም ነው፡፡ ለትምህርት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ማለትም እስክርቢቶ፣ እርሳስ፣ ደብተርና የመሳሰሉት በተማሪው የሚሸፈኑ ሆነው የመማሪያ መፃሕፍት ደግሞ አቅም ያላቸው በግዥና በኪራይ፣ አቅም የሌላቸው ደግሞ በትውስት የሚያገኙበትን አሰራር መከተል ያስፈልጋል፡፡*

*ጥራት ያለው ትምህርት ለመስጠትና መልካም ዜጎች ቀርፆ በማውጣት ረገድ የመምህራን ድርሻ ከፍተኛና ምትክ የሌለው መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ መምህራን ተማሪዎችን በአግባቡ ለመቅረፅ የሚስችል በቂ የሞያ ስልጠና እንዲያገኙ ማደረግ፣ ከወቅቱ የኑሮ ደረጃ ጋር የሚመጣጠን በቂ ወርሃዊ ደመወዝና ልዩ ልዩ ማበረታቻ የሚያገኙበትን ሁኔታ ማመቻቸት፣ የሞያ ስነምግባራቸውን ለማዳበርና መብታቸውን ለማስከበር የሚስችል ነፃ የሞያ ማህበር እንዲኖራቸው ማድረግ ስለትምህርት ጥራት ሲታሰብ ቅድሚያ ትኩረት ማግኘት የሚገባው ነው፡፡*

*በመንግስት፣ በግልና በሕብረተሰቡ ተገንብተው አገልግሎት በሚሰጡ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚሰጠው ትምህርት በኃይማኖት መርህ ላይ የተመሰረተ ሊሆን አይገባውም፡፡ የተለያዩ ኃይማኖቶችና ፆታዎች፣ ቋንቋዎችና ባህሎች ያሏቸው ሰዎች በአንድ ክፍል ውስጥ ተደባልቀው ለመማር የሚከለክል ሕግ መኖር አይገባውም፡፡ የኃይማኖት ድርጅቶች፣ የውጭ ሀገር ኮሚኒቲዎች፣ የበጎ አድራጎት ተቋሞችና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በባለቤትነት*

ወይም በኃላፊነት በሚያንቀሳቅሷቸው ትምህርት ቤቶች የሚሰጥ መደበኛ ትምህርት የሀገሪቱን የትምህርት ስርዓትና የጥራት ደረጃ የጠበቀ እንዲሆን ማድረግ ይገባል፡፡ በእርግጥ የኃይማኖት ድርጅቶች ለኃይማኖት ትምህርት መስጫ ባቋቋሙት የማስተማሪያ ተቋም ኃይማኖታቸው በሚፈቅደውና ራሳቸው በመረጡት መንገድ የማስተማር ነፃነታቸው አይደፈርም፡፡ በመደበኛው ትምህርት ለሚማሩ ተማሪዎች እድሜያቸው 18 ዓመት እስኪሞላ ድረስ ለሁሉም ኃይማኖቶችና ባህሎች በሚስማማ መንገድ የሚሰጥ የሥነምግባር ትምህርት እንዲያገኙ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

## 2.5.1 የህፃናት መዋያና አንደኛ ደረጃ ትምህርት

የሀገሪቱ ዜጎች እድሜያቸው 6 ዓመት እስኪሞላና የ1ኛ ደረጃ ትምህርት እስኪጀምሩ ድረስ በሕፃናት መዋያዎች ተመዝግበው የተወሰነ ችሎታ እንዲያዳብሩ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ የሕፃናት መዋያ ዋና ዓላማ ሕፃናት ስብዕና እንዲያዳብሩ፣ ራሳቸውን በአግባቡ እንዲገልጹ፣ ጠቃሚ የሕብረተሰቡ አባላት እንዲሆኑ የሚያስችል መሰረታዊ ነገር እንዲጨብጡ ማድረግ ነው፡፡ የሕፃናት መዋያ የመንግስት ትምህርት ቤት ስርዓት አካል ሳይሆኑ በፈቃደኝነት የሚከናወኑና በአብዛኛው ወጪያቸውም በወላጆችና በአሳዳጊዎች የሚሸፈን ሊሆን ይገባዋል፡፡ ሁኔታው እስከፈቀደ የአካባቢ መንግስታትም ይኸንን አገልግሎት ቢሰጡ የሚከለክል ገደብ ሊጣልባቸው አይገባም፡፡ ብዙውን ጊዜ የግል ባለሀብቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራት፣ የኃይማኖት ተቋሞችና የመሳሰሉት በዚህ መስክ ሰፊ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ እንደሁኔታው ከሶስትና አራት ዓመታት ጀምሮ 6 ዓመት እስኪሞላቸውና የ1ኛ ደረጃ መደበኛ ትምህርት እስኪጀምሩ ድረስ ሕፃናት በእነዚህ መዋያዎች አገልግሎት ማግኘት ይችላሉ፡፡ በእነዚህ ተቋሞች ሕፃናት የግማሽ ቀን ወይም የሙሉ ቀን አገልግሎት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡ የእነዚህ አገልግሎቶች መኖር በተለይም ስራ ላላቸው እናቶችና አባቶች ወይም አሳዳጊዎች ስራቸውን ለማቋረጥ እንዳይገደዱ ጠቃሚ ነው፡፡

የመደበኛው ትምህርት ስርዓት መጀመር ያለበት ሕፃናት 6 ዓመት እድሜ ሲደርሱ ሆኖ ለ6 ተከታታይ ዓመታት የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ይከታተላሉ፡፡ የመጀመሪያዎቹ 4 ዓመታት ትምህርቶች የግማሽ ሴሚስተር፣ የሴሚስተርና የዓመት ፈተና የሚዘጋጅላቸውና ደረጃ የሚወጣላቸው ሳይሆኑ በአነስተኛ የፈተና ሙከራዎችና በተከታታይ የመምህራን ግምገማ ተማሪዎች ከክፍል ወደክፍል ዝውውር የሚያደረጉባቸው ወይም ደግመው እንዲማሩ የሚደረጉባቸው ይሆናሉ፡፡ ተከታዮቹ ሁለት ዓመታት ደግሞ አስቀድሞ በታቀደ የጊዜ ሰሌዳና ፕሮግራም መሰረት ፈተና የሚዘጋጅላቸውና ደረጃ የሚወጣላቸው ሆነው አላፊና ደጋሚ ተማሪዎች በሚለዩበት ስርዓት የሚማሩ ይሆናሉ፡፡ በተለይ የ1ኛ ደረጃ ትምህርት ማጠቃለያ የሆነው 6ኛ ክፍል ተማሪዎች በክልል ደረጃ በሚዘጋጅ ፈተና ተመዝነው ወደመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ የሚያልፉበት ይሆናል፡፡

ከ5ኛ እስከ 6ኛ ክፍል የሚሰጠው ትምህርት የኦሬንቴሽን (የማስተዋወቂያ) ምዕራፍ ተደርጎ የሚታይና ተማሪዎችና ወላጆች የሚስማማቸውን ትምህርት ቤት ምርጫ ለማስተካከል እድል እንዲኖራቸው የሚያስችል ነው፡፡ የ1ኛ ደረጃ የመጀመሪያዎቹ 6 ዓመታት ሕፃናት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው እንዲማሩ ይደረጋል፡፡ ከሕፃናት መዋያ ጀምሮ እስከ 6ኛ ክፍል ማጠናቀቂያ ድረስ እንግሊዘኛ ቋንቋ፣ የፌዴራሉ መንግስት የስራ ቋንቋ፣ የክልሉ የስራ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣሉ፡፡

## 2.5.2 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት

ከ1ኛ እስከ 4ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን በአንድ መምህር በአሃዳዊ ስርዓት ማስተማር በሌሎች በአደጉ አገሮች የሚሰራና ውጤትም ያስገኘ ሲሆን ይህ ሁኔታ አሁን ሀገራችን ካለችበት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ አንፃር ግን ስራ ላይ ሊውል የሚችል አይደለም፡፡ በተለይም በሀገሪቱ ያሉት የ1ኛ ደረጃ መምህርት አንድን ተማሪ በብቸኛ አስተማሪነት ቀርፆ ለማውጣት በሚያስችል ብቃት ላይ የሚገኙ ስላልሆኑ፣ የተማሪ ቤተሰቦችም በእኩል ደረጃ የልጆቻቸውን የትምህርት ደረጃ በብቃት የመከታተል ልምድና ችሎታ የሌላቸው በመሆኑ አሃዳዊ የትምህርት

ስርዓትን በአጭር ጊዜ ተግባራዊ ማድረግ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ተማሪዎች ከአንድ በላይ በሆኑ መምህራን እንዲማሩ ያለንበት ተጨባጭ ሁኔታ ያስገድዳል፡፡

የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ከ7ኛ ክፍል እስከ 12ኛ ክፍል ሆኖ የ7ኛና 8ኛ ክፍል ትምህርቶች የመለስተኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት (Junior secondary education) የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ 9ኛና 10ኛ የመካከለኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት (Intermediate secondary education) የሚሰጥባቸው ሲሆኑ 11ኛና 12ኛ ክፍል ደግሞ በሁለት ዘርፎች የተከፈለ ሆኖ አንደኛው ለኮሌጅና ለዩኒቨርስቲ ትምህርት (preparatory secondary education) መዳረሻ የሚሆን የመዘጋጃ ትምህርት ሁለተኛው ደግሞ የሥራ ማዘጋጃ የሞያ ሰልጠና (Vocational preparation for the job) የሚሰጥባቸው ናቸው፡፡ ከ7ኛ እስከ 12ኛ ክፍል የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንግሊዝኛ ሆኖ የክልልና የፌዴራሉ የስራ ቋንቋ እንደ አንድ የትምህርት ዓይነት ይሰጣል፡፡ የ7ኛና 8ኛ ክፍል ትምህርቶች በቀለም ትምህርት ላይ ያተኮሩ ሆነው የ9ኛና የ10ኛ ክፍል ትምህርቶች ደግሞ የቀለም ትምህርትና የሞያ ሥልጠና ጎን ለጎን የሚሰጥባቸው ይሆናሉ፡፡ የ7ኛና 8ኛ ክፍል ትምህርት የሚከታተሉ ተማሪዎች ችሎታ መመዘኛ ፈተናዎች የሚዘጋጁላቸውና ደረጃ የሚወጣላቸው ሆነው ከክፍል ወደክፍል የሚሸጋገሩትና የሚደግሙት ተማሪዎች ይለያሉ፡፡ በተለይ 8ኛ ክፍል ሲያጠናቅቁ በብሔራዊ ደረጃ በሚዘጋጅ ፈተና ተመዝነው ወደ መካከለኛ 2ኛ ደረጃ የሚያልፉት ተማሪዎች ይታወቃሉ፡፡

የመካከለኛ 2ኛ ደረጃ ትምህርት በ9ኛና 10ኛ ክፍል የሚሰጠው ሲሆን በመለስተኛ 2ኛ ደረጃና በኮሌጅና ዩኒቨርስቲ መዘጋጃ 2ኛ ደረጃ መካከል የሚገኘው የትምህርት ደረጃ ማለት ነው፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለፀው በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት የቀለም ትምህርትና የሞያ ስልጠናን ጎን ለጎን ያቀፈ ነው፡፡ በተቻለ መጠን በተማሪውና በአስተማሪው ላይ ከፍተኛ ጫና በማይፈጥርና በጥንቃቄ ተጠንቶ በሚዘጋጅ ትምህርት የተመረጡ የቀለምና የሞያ ትምህርቶች ይሰጣሉ፡፡ በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ትምህርት ወደማዘጋጃ ምዕራፍ መሸጋገሪያ የሚሆን ነው፡፡ የተማሪዎች የችሎታ መመዘኛ ፈተናዎች እየተዘጋጁ አላፊዎችና ደጋሚዎች ይታወቃሉ፡፡ በተለይም 10ኛ ክፍል በብሔራዊ ደረጃ በሚዘጋጅ ፈተና ወደ ኮሌጅና ዩኒቨርስቲ መዘጋጃ ትምህርት ወይም ወደ ስራ መዘጋጃ የሞያ ሥልጠና የሚሄዱትና የሚወድቁት ተማሪዎች የሚለዩበት ነው፡፡ ወደሁለቱም አቅጣጫ የሚሄዱት የማለፊያውን ነጥብ ያገኙ ሆነው ይኸንን ያላገኙት የሚወድቁበትን አሰራር መከተል የተሻለው አማራጭ ነው፡፡ ነገር ግን ወደኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ማዘጋጃና ወደስራ ማዘጋጃ የሞያ ስልጠና የሚገቡትን መለያው መንገድ ካለፉት መካከል ከተወሰነ ነጥብ በላይ ያገኙት ወደ ኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ማዘጋጃ፣ ከተወሰነ ነጥብ በታች ያገኙት ደግሞ ወደስራ ማዘጋጃ ሞያ ስልጠና የሚገቡበትን አሰራር መከተል ይገባዋል፡፡ መለያው ነጥብ የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ ማዘጋጃዎችም ሆኑ የሥራ ማዘጋጃ ሞያ ስልጠና ማዕከላቱ በሚኖራቸው የመቀበል አቅም ላይ ተመስርቶ የሚወሰንና እንደሁኔታው የሚለዋወጥ እንጂ ቋሚ መሆን የለበትም፡፡ ረዘም ላለ ጊዜ በቋሚነት ሊቀጥል የሚችለው ወደ ሁሉም የማዘጋጃ ክፍሎች ለማለፍ የሚያበቃው ዝቅተኛ ውጤት 2 ነጥብ ቢሆን ተገቢ ነው፡፡ 10ኛ ክፍል ላይ የሚሰጠውን ብሔራዊ ፈተና የወደቁ ተማሪዎች ትመህርት የመቀጠል እድላቸው ምንጊዜም ክፍት መሆን አለበት፡፡ 10ኛ ክፍል ላይ ብሔራዊ ፈተናውን የወደቁ ተማሪዎች በለጋ አድሜ ላይ የሚገኙ ስለሆነ ቢያንስ አንድ ጊዜ ሙሉ አመት ደግመው የመማር እድል እንዲያገኙ ማድረግና ከአንድ ጊዜ በላይ የወደቁት ምንጊዜም በግላቸው ፈተናውን ደግሞ የመውሰድ እድላቸው ክፍት እንዲሆን ማደረግ ተገቢነው፡፡ ፈተናውን በሚያልፉበት ጊዜ በሚያገኙት ውጤት መሰረት ወደኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ማዘጋጃ ወይንም ወደ ስራ ማዘጋጃ የሞያ ስልጠና የሚገቡበትን ቋሚ አሰራር መከተል ይገባል፡፡ በግል ለሚያደርጉት ጥረት ውጤታማ መሆን ለዚሁ ተግባር በግል ባለሀብቶች በሚዘጋጅ መደበኛ ትምህርት ቤቶችና የተልዕኮ ትምህርት ፕሮግራሞች እየተመዘገቡ በድጋሚ ሊማሩ እንዲችሉ ወይንም በግል ጥረታቸው ተዘጋጅተው ለድጋሚ ፈተና እንዲበቁ እድሉን ክፍት ማድረግ ይገባል፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች በመጀመሪያው ጊዜ ወይም በ2ኛው ጊዜ ያልተሳካላቸው ተማሪዎች በሌላ ጊዜ ሊሳካላቸው የማይችልበት ምክንያት የለም፡፡ ዋናው ነገር 10ኛ ክፍል ብሔራዊ መልቀቂያ ፈተና አንድ ጊዜ ሞክሮ ያልተሳካለት ሰው እስከህይወቱ ፍፃሜ ድረስ የመማር እድሉ የተዘጋ አለመሆኑን ማረጋገጥ ነው፡፡ ሌላው ትልቅ ሊሰጠው የሚገባው ቁምነገር ይህን አይነቱን የትምህርት ስርዓት ለማስፈፀም በቅድሚያ የስራ ማዘጋጃ የሞያ ማሰልጠኛ ማዕከላትም ሆኑ የኮሌጅና ዩኒቨርስቲ ማዘጋጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በቅርበት በሚያገኟቸው አካባቢዎቹ በጥራትና በብዛት መደራጀት አለባቸው፡፡ ለሁለቱም ተቋማት በቂ የሆኑ መምህራን በቅድሚ በበቂ ሁኔታ ሰልጥነው መዘጋጀት አለባቸው፡፡

የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ ማዘጋጃ (በ11ኛ እና በ12ኛ ክፍል) የሚሰጠውን ትምህርት ያጠናቀቁ ተማሪዎች የመግቢያ ፈተና እየወሰዱ ባመጡት ውጤት መሰረት የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ ትምህርት በተለያየ የሞያ መስክ እንዲያገኙ ይደረጋል። የመግቢያ ፈተና የሚሰጠው በማዘጋጃው ወቅት መርጠው በተዘጋጁበት የማህበራዊ ወይም የተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ ላይ ተመስርቶ መሆን ይገባዋል። ከዚያ በኋላ በወሰዱት የመግቢያ ፈተና ውጤት መሰረት በተፈጥሮ ሳይንስ ለኮሌጅና ለዩኒቨርስቲ ወይም ለዲፕሎማና ለዲግሪ ትምህርት በመንግስት ተቋሞች ዘርፍ ይደለደላሉ።

በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ በዲፕሎማና በዲግሪ ትምህርት የሚሰጥባቸውን የተለያዩ የትምህርት ዓይነቶች ለመምረጥ ያላቸው እድል የሚወሰነው በውጤታቸውና በፍላጎታቸው ላይ ይሆናል። በማህበራዊ ሳይንስ ዘርፍም ይኸንኑ አሰራር መከተል ይገባል። በዚህ የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ ማዘጋጃ ፕሮግራም ከቆዩት መካከል በመግቢያ ፈተና ወዳቂ ሆነው ከትምህርት ዓለም እስከመጨረሻው የሚነጠሉበትን አሰራር ማስወገድ ይገባል። ከዚህ ይልቅ የመንግስት ኮሌጆችና ዩኒርሰቲዎች ገብቶ ለመቀጠል ያለውን እድል ሁልጊዜም ክፍት ማድረግ ይገባል። ወይንም በሌሎች የኮሌጅና የዩኒቨርስቲ ትምህርት በሚሰጡ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የትምህርት ተቋሞች ውስጥ ገብተው ለመቀጠል፣ ወይንም የውጭ ስኮላርሽፕ ትምህርት አግኝተው ለመማር የሚችሉበትን እድል ሁልጊዜም ክፍት ማድረግ አስፈላጊ ነው። ይኸንን የማዘጋጃ ትምህርት ተከታትለው የመግቢያ ፈተና ለወሰዱ ተማሪዎች ማረጋገጫ ሰርተፊኬት መስጠት ይገባል። በቀድሞው ስርዓተ ትምህርትም 12 ክፍል ማትሪክ ተፈትነው የወደቁ ተማሪዎች ድጋሚ ፈተና መውሰድ የሚችሉበት እድል መመቻቸት አለበት።

በስራ ማዘጋጃ የሞያ ስልጠና በ11ኛና 12ኛ ክፍል የሚሰጠውን ትምህርት የተከታተሉ የሞያ ስልጠና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት ይሰጣቸዋል። በዚህ ደረጃ የሚሰጠው ስልጠና በተማሪዎቹ ምርጫና በሞያ ስልጠና ተቋሞቹ የመቀበል አቅም ላይ የተመሰረተ ሆኖ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ የስራ መስኮች በከፍተኛ ደረጃ በሚፈልጓቸው ሞያዎች ላይ የሚያተኩሩ መሆን አለባቸው። በእርግጥ ኢኮኖሚው እያደገና ማህበራዊ የስራ ክፍፍል እየሰፋ በሄዱ ቁጥር የሚፈለገው የሞያ ዓይነትና ብዛት እየጨመረ ስለሚሄድ በሞያ ማሰልጠኛዎቹ ስልጠና የሚሰጥባቸው ሞያዎችም በዓይነትና በቁጥር እድገት ማሳየታቸው የማይቀር ነው። በመሆኑም አሁን ያለውን የስልጠናና የሞያተኛ ፍላጎት እንደመነሻ በመውሰድና የመጪውን ሁኔታም አሻግሮ በማየት በተወሰኑ የሞያ መስኮች መጀመርና እንደሁኔታው በየጊዜው ተገቢ ለውጦችንና ማሻሻያዎችን ማድረግ ይቻላል። ስለሆነም በግብርና ሞያዎች፣ በኤሌክትሪክ፣ በአውቶ ሜካኒክ፣ በአናፂነት፣ በግንበኝነት፣ በቢሮ ፀሐፊነት፣ በረዳት ሕክምና፣ በፀጉር ስራ፣ በቀለም ቀቢነት፣ በመገናኛ ኦፐሬተርነት፣ በረዳት ሂሳብ መዝገብ ያዥነት፣ በሽያጭ ረዳትነት፣ በእንጨት ስራ፣ በብረታ ብረት ስራና በሌሎችም የሞያ መስኮች እንዲሰለጥኑ ማድረግ ይቻላል። በዚህ መስክ የሰለጠኑ ተማሪዎች ከትምህርት ወደስራ ሕይወት ለመሸጋገር ያለው ሁኔታ ቀላል ይሆንላቸዋል። ፍላጎታቸው ወደስራ መሰማራት ከሆነ መደበኛ ስልጠና የወሰደ ሰው በሚጠይቁ ስራዎች ተወዳድረው ለመቀጠር እድል ያገኛሉ። የራሳቸውንም ስራ ለመስራት ከፈለጉ ይኸንኑ ለማድረግ የሚያስችል መሰረታዊ ችሎታ ያስጨብጣቸዋል። ተጨማሪ ስልጠና የሚፈልጉት ደግሞ የሞያ ስልጠና በሚሰጡ የትምህርት ተቋሞች ገብተው መማር ይችላሉ። የመካከለኛ 2ኛ ደረጃ ወይም የስራ ማዘጋጃ ሞያ ስልጠና የጨረሱ ተማሪዎች ተጨማሪ ስልጠና በፈለጉ ጊዜ ይኸንኑ ለማድረግ የሚችሉባቸው የሞያ ትምህርት ተቋሞች በመንግስት፣ በግልና መንግስታዊ ባልሆኑ ሌሎች አካላት የሚስፋፉበትን እድል መፍጠር ያስፈልጋል።

በእነዚህ የሞያ ትምህርት ተቋሞች የሚሰጠው ትምህርት ንድፈ ሀሳብንና ተግባርን ያቀናጀ እንዲሆን በማድረግ ንድፈ ሀሳባዊውን በትምህርት ቤቱ ውስጥ፣ የተግባር ስልጠናውን ደግሞ በመንግስትና መንግስታዊ ባልሆኑ ተቋሞች የሚሰጥበትን ስርዓት መዘርጋት ይገባል። የስልጠና ሕጉን የማውጣት ኃላፊነት የፌዴራሉ መንግስት ሆኖ የሞያ ትምህርት ተቋሞቹን የማስተዳደርና የመምራት ኃላፊነት የክልል መንግስታትና የግል ባለሀብቶች እንዲሆኑ በማድረግ የስራ ክፍፍል መፍጠር ያስፈልጋል። ለሞያ ትምህርት ተቋሞቹ የሚያስፈልጉ ፋሲሊቲዎችን በማሟላቱ ጥረት የፌዴራል መንግስትም ሊሳተፍበት ይገባል። እነዚህ የሞያ ስልጠና የሚሰጡ የትምህርት ተቋሞች እድሜያቸው ከ18 ዓመት በታች ሆነው ሌላ የትምህርት ዓይነት ያልተከታተሉ ወጣቶችንም እንዲያሰለጥኑና ለሥራ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ይገባል።

ከዚህ በተጨማሪ የስራ ላይ ስልጠና የሚካሄድበትን አሰራር መዘርጋት ያስፈልጋል፡፡ እንደስራው ባህርይና እንደሚፈለገው የስልጠና ዓይነት የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎች የሚሰጡበትን አቅጣጫ መከተል ይገባል፡፡ ለሚሰጠው ሥልጠና የሚያስፈልገው ወጪ ለኪስ ወይም ለሻይና ለትራንስፖርት የሚያግዝ መጠነኛ ብቻ እንዲሆን አድርጎ የመለማመጃ ስልጠና ማካሄድ፣ እንዲሁም ምን አይነት ትምህርት መሰጠት እንደሚገባውና ይኸም እንዴት ሊመዘን እንደሚችል በስልጠና ሕጉ መወሰን ያስፈልጋል፡፡ ይኸንን የሚወስነው የሚመለከተው የፌዴራል መስሪያ ቤት ሆኖ ለውሳኔው የመነሻ ሀሳብ ከንግድ ማህበራት፣ ከአሰሪዎችና ከሰራተኞች ማህበራት ማግኘት ይኖርበታል፡፡ የስራ ላይ ስልጠናው የኢንዱስትሪ፣ የእደጥበብና የንግድ ምክር ቤቶችን የመሳሰሉ የግል ቢዝነስ ተቋሞች በሚሰጡት የመመዘኛ ፈተና እንዲጠናቀቅ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በፈተና ቦርዱ ውስጥ ከአሰሪዎች፣ ከሰራተኞች፣ ከሞያ ትምህርት ቤቶችና ከመምህራን ተወካዮች እንዲካተቱ ማድረግ የምዘናውን ትክክለኛነት ለማረጋገጥ አንድ ጠቃሚ መንገድ ነው፡፡

በተቻለ መጠን ሁሉም የስራ ተቋሞች የሞያ ስልጠና አገልግሎት ለሠራተኞቻቸው የሚሟላበትን ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት ማድረግ ይገባቸዋል፡፡ በተለይ ትላልቅ ተቋሞች የራሳቸው የስልጠና ወርክሾፕ ማደራጀት የሚችሉበትን አሰራር ማስፈን ይገባል፡፡

በሌላ መልክ የሚሰጥ የሞያ ስልጠናም ሊኖር ይችላል፡፡ በአነስተኛ የወጪ ድጋፍ ከሚሰጡ የመለማመጃ ስልጠናዎች ከሞያ ትምህርት ቤቶች የተለዩ የሞያ ማሰልጠኛ ስርዓቶችን ዘርግቶ ጥቅም ላይ ማዋል ይገባል፡፡ ሙሉ ቀን ልዩ የሞያ ትምህርት የሚሰጡ ተቋሞች በመንግስትና በግል እንዲከፈቱ በማድረግ ለ1 ዓመትና እንደሁኔታው ከዚያም ለሚበልጥ ጊዜ እንዲያሰለጥኑ ማድረግ ይቻላል፡፡

ልዩ የ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን በመንግስትና በግል እያቋቋሙና የመካከለኛ 2ኛ ደረጃ ያጠናቀቁትን ተማሪዎች በመቀበል ለሁለት ዓመታት እያስተማሩ ብቁ በማድረግ በኮሌጅ ደረጃ የሚሰጥ ከፍተኛ ትምህርት የሚከታተሉበትን መንገድ መከተል ይቻላል፡፡ በዚህም አለ በዚያ ዋናው ነገር የሀገሪቱ ወጣቶች የመማር እድል እንዲሰፋ ማድረግ፣ ሁሉም ወጣቶች የተወሰነ የሞያ ስልጠና ሊያገኙ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ማስቻልና ለተግባር ብቁ ዝግጅትና ችሎታ ያሟሉ ዜጎችን ማፍራት ነው፡፡ ይህ ዓላማ በሁሉም መስክ ኋላቀርነት ተብትቦ በያዛት ድሃ ሀገር በቀላሉ የሚሳካ እንዳልሆነ ይታወቃል፡፡ በመንግስት ጥረት ብቻም የሚሟላ ሊሆን አይችልም፡፡ መንግስትን ጨምሮ የግል ባለሀብቶችንና ሁሉንም የትምህርትና የሰለጠነ የሰው ኃይል ጉዳዩ የሚያገባቸውን ወገኖች ሰፊ ጥረት የሚጠይቅ ነው፡፡ የአሁኑን ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን የሀገሪቱን እድል የሚወስነው አንዱ ትልቅ ጉዳይ በትምህርትና በሞያ ስልጠና የሚደረገው ጥረት እንደመሆኑ ለዚህ ቁልፍ የመውደቅና የመነሳት ጉዳይ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ መረባረብ ይገባል፡፡

## 2.5.3 **የከፍተኛ ትምህርት**

በሀገራችን የከፍተኛ ትምህርት ልምድ ከግማሽ ምዕት ዓመት ብዙም የራቀ አይደለም፡፡ ስርጭቱም ከአዲስ አበባ ሌላ በጥቂት የክፍለ ሀገር ከተሞች አካባቢ ብቻ የተወሰነና የመቀበል አቅማቸውም እጅግ አነስተኛ ነው፡፡ በእነዚህ ዩኒቨርስቲዎች የሚሰጠው ትምህርት በአብዛኛው ሞያተኞችን የሚያፈራ ሳይሆን የንድፈ ሀሳብ እውቀት በማስጨበጥ ላይ ያተኮረ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ሰፊ የምርምር ስራ የማይካሄድባቸውና የሚካሄዱ ጥቂት ምርምሮች ካሉም በሕዝቡ መሰረታዊ ችግሮች ላይ የሚያተኩሩ አይደሉም፡፡ ስለዚህ ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ቁጥራቸው እንዲጨምር፣ ስርጭታቸው ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲሰፋ፣ የመቀበል አቅማቸው እያደገ እንዲሄድ፣ ሀገሪቱ በምትፈልገው መስክ ሞያተኛን ማፍራት እንዲችሉና በሀገሪቱ መሰረታዊ ፍላጎቶች ላይ የተመሰረቱ ችግር ፈቺ ምርምሮችን እንዲያካሂዱ በሚያስችል አቅጣጫ መገንባት ያስፈልጋል፡፡ እስካሁን ድረስ የተወሰኑ የኃይማኖት ተቋሞችና የግል ባለሀብቶች ከሚያስተዳድሯቸው ጥቂት የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች በስተቀር ዋና ዋናዎቹ ኮሎጆችና ዩኒቨርስቲዎች የመንግስት ናቸው፡፡ በዚህም ምክንያት መንግስት በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ላይ ያለው ተፅዕኖ ገደብ የለሽ ነው፡፡ በበጀት ተፅዕኖ ያደርግባቸዋል፡፡ የራሱን የፖለቲካ ካድሬዎችና ደጋፊዎች በከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች አመራር ላይ እየሾመ ያስቀምጣል፡፡ ፖሊሲውን የማይከተሉ ናቸው ብሎ ያሰባቸውን መምህራንና ሰራተኞች በፈለገው ጊዜ ከስራ ያሰናብታቸዋል፡፡ ነፃ የሞያ ማህበር እንዳያደራጁ የተለያዩ መሰናክሎችን

እየፈጠረ የመደራጀት መብታቸውን ይገድባል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ተማሪዎች በነፃነት እንዳይደራጁ፣ ሀሳባቸውን እንዳይገልፁ፣ የአካዳሚክና የመብት ጥያቄዎችን እንዳያነሱ በመሳሪያ ኃይል ያፍናል። በጥበቃና በልዩ ልዩ ሰበብ የመንግስት ሰላዮችንና የገዥው ፓርቲ አባላትን እየመደበ በከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማህበረሰቡ ላይ ከፍተኛ ክትትል ያደርጋል። በአጭሩ የአስተዳደርና የአካዳሚክ ነፃነት አሳጥቷቸዋል።

ስለዚህ እስካሁን የነበረውን አመቺ ያልሆነ የስራ ሁኔታና የመንግስትን ጣልቃ ገብነት ማስቀረት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ረገድ መወሰድ ከሚገባቸው ተግባሮች መካከል የመጀመሪያው መሆን ይኖርበታል። የፌዴራል መንግስት የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የሚመሩባቸውን አጠቃላይ መርሆዎችና ሕጋዊ ስርዓቶች ተፈፃሚነት ከመከታተል በስተቀር በእለት ከዕለት አስተዳደራዊና የመማር ማስተማር ጉዳያቸው ውስጥ ጣልቃ የሚገባበት ሁኔታ መቅረት አለበት። ለምርምር፣ ለግንባታና ማስፋፊያ ስራ የሚውል ፋይናንስ በመመደብ ከፍተኛ ሚና መጫወት የሚገባው ቢሆንም ይኸንን ሽፋን በማድረግ የአሰራር ነፃነታቸውን ጨርሶ እስከመቀማት የሚደርስ ተፅዕኖ የሚያደርግበት ሁኔታ መለወጥ አለበት። የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ራሳቸውን የማስተዳደር ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። በየትኛውም የዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ እንደሚገኙ ነፃ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች የሀገራችን ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች የራሳቸውን ቻርተር በራሳቸው ውሳኔ አዘጋጅተው መመራት አለባቸው። ቻርተሩ የሀገሪቱን ሕገመንግስት መሰረት አድርጎ መዘጋጀት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የተቋሞቹን አስተዳደራዊና አካዳሚዊ ነፃነት የሚያረጋግጥ መሆን ይገባዋል። የራሳቸውን መሪዎች ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድና የብቃት መመዘኛዎችን መሰረት ባደረገ ሁኔታ የመምረጥ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። ተማሪዎችም የመደራጀት፣ ሀሳባቸውን የመግለጽ፣ የአካዳሚክና የመብት ጥያቄዎችን የማቅረብ ነፃነታቸውን በሚያረጋግጥ መንገድ የራሳቸውን ደንብ ማውጣትና መሪዎቻቸውን በዴሞክራሲያዊ አግባብ የመምረጥ ሙሉ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል። የመፅሔት፣ የሬዲዮና የጋዜጣ ስርጭት ስራ በነጻነት ማካሄድ የሚያስችል መብት ሊከበርላቸው ይገባል። የአካዳሚክ ስታፍ አባላት ብቻ ሳይሆኑ በተቋሞቹ ውስጥ የተመደቡ ሌሎች ሰራተኞችም መብታቸው እንዲጠበቅላቸውና በአንድ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ውስጥ የሚሰራ ሰራተኛ የሚጠበቅበትን ከፍተኛ ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠርላቸው ያስፈልጋል። በአጠቃላይ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ማህበረሰቦች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው እንዲሰሩ የሚያስችል አስተዳደራዊና አካዳሚያዊ ነፃነት ሊኖራቸው ይገባል።

የሀገሪቱ ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች በገበያው ውስጥ ባለው የሰው ኃይል ፍላጎትና በመጪው ጊዜ ትንበያ ላይ የተመሰረተ ስልጠና መስጠት በሚያስችል መንገድ የስራ ክፍፍል ሊኖራቸው ይገባል። የተወሰኑት በምርምርና በድህረ ምረቃ ፕሮግራም ቢያተኩሩ ሌሎቹ በዲፕሎማና በመጀመሪያ ደረጃ የሚመረቁ ተማሪዎችን በማውጣት ላይ የበለጠ ሊያተኩሩ ይችላሉ። የተወሰኑት በማህበራዊ ዘርፍ ብቁ ሞያተኞችን ለማፍራት ከፍተኛ ትኩረት ቢሰጡ ሌሎች ደግሞ በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ ሞያተኞችን በብቃት የማፍራት ስራ ላይ ይበልጥ ሊረባረቡ ይችላሉ። የተወሰኑት በእርሻ ሞያ ቢያተኩሩ ሌሎቹ በቴክኒክና በኢንጅነሪንግ ዘርፍ ይበልጥ ትኩረት ሊያደርጉ ይችላሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ የተለያዩ የከፍተኛ ትምህርት ሞያዎችን አንድ ላይ በማቀናጀት አጠቃላይ በሆነ መንገድ ብቁ ሞያተኞችን ለማፍራት ይችላሉ። ሌሎች የርቀት፣ የተልዕኮና የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራሞችን ከመደበኛ ስራቸው ጎን ለጎን ሊያካሂዱ ይችላሉ። የከፍተኛ ትምህርት በእንግሊዝኛ ቋንቋ መሰጠት የሚገባው ሲሆን የሀገሪቱን ቋንቋዎች እንደ አንድ የሞያ መስክ ማጥናት ለሚፈልጉ ዜጎች በከፍተኛ ትምህርት ደረጃ እንዲማሩት ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባል።

ተማሪዎች ማጥናት የሚፈልጉትን የሞያ መስክ ራሳቸው እንዲመርጡ መብት ሊኖራቸው ይገባል። አንዳንዶቹ የሞያ መስኮች የመግቢያ ፈተና የሚጠይቁ ቢሆኑም እንኳ የተማሪዎቹን ምርጫ በጠበቀ መንገድ ሊካሄዱ ይገባል። ተማሪዎች የሚፈልጉትን ሞያ ብቻ ሳይሆን መውሰድ የሚፈልጉትን ሌክቸር እስከመምረጥ መብት ሊኖራቸው ይገባል። የሀገሪቱ ዜጎች በከፍተኛ ድህነት ውስጥ ለረጅም ጊዜ የቆዩና አሁንም ከዚህ አሳዛኝ ሁኔታ ያልወጡ በመሆናቸው አብዛኞቹ ወላጆች ለልጆቻቸው የከፍተኛ ትምህርት ወጪ የሚሆን ገንዘብ የመክፈል አቅም የላቸውም። በመርህ ደረጃ የከፍተኛ ትምህርት ወጪን ተማሪዎች እንዲጋሩ ማድረግ ተገቢ ቢሆንም የሀገሪቱ የኢኮኖሚ ሁኔታና የዜጎች ድህነት እጅግ አሳዛኝ በሆነ ደረጃ በሚገኝበት በአሁኑ ጊዜ ይኸንን

ተግባራዊ ማድረግ ፍትሃዊ ሊሆን አይችልም፡፡ እየተበደሩ እንዲከፍሉ በሀገሪቱ ውስጥ የማበደር አቅም ያላቸው ተቋሞች በበቂ ሁኔታ የተገነቡበት ደረጃ ላይ አልተደረሰም፡፡ መንግስት የማበደሩን ኃላፊነት ብቻውን ይውሰድ እንዳይባል ራሱ በብድር ጫና የጎበጠና ወለዱን እንኳ ከፍሎ ለመጨረስ የሚችልበት እድል በአጠራጣሪ ሁኔታ ላይ የሚገኝ በመሆኑ የሀገሪቱን ችግር ከማብዛት በስተቀር ሌላ ትርፍ የማያስገኝ ነው፡፡ ምንአልባት የሕወሓት/ኢህአዴግ የንግድ ተቋሞች በአበዳሪነት እንሰራለን የሚል አቋም ሊይዙ ይችሉ ይሆናል፡፡ የገዥው ፓርቲ የንግድ ተቋሞች ለከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ወጪ የአበዳሪነት ሚና እንዲኖራቸው ከተደረገ የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞቹ ከእነሰራተኞቻቸውና ከሚያፈሩት የተማረ የሰው ኃይል ጋር ለአንድ ፖለቲካ ፓርቲ በሽያጭ እንደተዛወሩ የሚቆጠር ይሆናል፡፡ ይህ ከሆነ በሀገሪቱ ውስጥ ነፃ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም የመኖሩ ተስፋና ብቁ ሞያተኛ የማፍራቱ ሀሳብ ሁሉ ያበቃለታል ማለት ነው፡፡ ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ወደ ፖለቲካ ትምህርት ቤትነት፣ ሁሉም የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ወደ ፓርቲ ካድሬነት ይወርዳሉ ማለት ነው፡፡ ስለዚህ የወጪ መጋራት ጉዳይ አሁን ሊጀመር የማይችልና የማይገባው መሆኑ ሊታመንበት ያስፈልጋል፡፡

የወጪ መጋራቱ አሰራር ተፈፃሚ መሆን የሚገባው የሀገሪቱ ኢኮኖሚ የማያቋርጥና አስተማማኝ የእድገት መስመር መያዙ ሲረጋገጥ፣ የሕዝቡም ድህነት ሲሻሻልና አስተማማኝ የኑሮ ዋስትና መፈጠር ሲጀምር ብቻ ነው፡፡ ይህ እስከሚሆን ጊዜ ድረስ መንግስት ከድሃው ሕብረተሰብ የሚሰበስበውን ቀረጥና ግብር ከሙስናና ከብክነት በፀዳ መልኩ በቁጠባ እየተጠቀመ፣ ከውጭ የሚገኘውን ብድርና እርዳታም እንደዚሁ በአግባቡ በስራ ላይ እያዋለ ለትምህርት ዘርፍ የሚመደበውን በጀት መሸፈን ይኖርበታል፡፡ ያለውን የፋይናንስ ሪሶርስ በቁጠባና በተገቢው መንገድ መጠቀም አንዱ ነገር ሆኖ የግብርና የታክስ መሰረቱን ማስፋትና የማሰባሰብ ብቃትን የማሳደግ ጉዳይ የመንግስትን ገቢ የሚጨምር በመሆኑ ሊተኮርበት ያስፈልጋል፡፡ በዚህም መሰረት አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ የወጪ መጋራት አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ መሞከር ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝነ ነው፡፡ ከሁሉም በላይ የሀገሪቱን ዜጎች የመማር መብት የሚገድብ ውጤት ማስከተሉ የማይቀር ነው፡፡ የድሃ ልጆች ለመማር ያላቸውን ፍላጎት ተስፋ የሚገድል ነው፡፡ የከፍተኛ ትምህርት የጨረሱ ሰዎች ከትምህርት በኋላ የስራ እድል እንደሚያገኙ እርግጠኛ መሆን የሚያስችል የኢንቨስትሜንት ፍሰትና የስራ እድል በሌለበት ሁኔታ ተማሪዎች ተበድረው ለመማር ድፍረቱ አይኖራቸውም፡፡ ስራ አግኝተው እንደሚከፍሉት እርግጠኛ የማይሆኑበትን የብድር እዳ እያሰላሰሉ የከፍተኛ ትምህርትን ጫና ለመቋቋም የሚያስችል ስነልቦናዊ መረጋጋት ያገኛሉ ተብሎ አይታሰብም፡፡ እንደዚህ ባለ ውጥረትና ጭንቀት በሰፈነበት መንገድ ብቁ ሞያተኞችን አፍርቶ ማውጣት ቀላል ነገር አይደለም፡፡

ስለዚህ የወጪ መጋራትን በአሁኑ ጊዜ መጀመር ከፈረሱ ጋሪውን እንደማስቀደም የሚቆጠር ነው፡፡ በቅድሚያ ድህነትን በመቀነሱ ትግል አንድ ዓይነት ተስፋ የሚጣልበት ውጤት ለማስመዝገብ መረባረብ ይገባል፡፡ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ሁኔታ አስተማመኝ በሆነ የእድገት መስመር ውስጥ እንዲገባ ለማድረግ መረባረብ ያስፈልጋል፡፡ ለኢቨስትመንትና ለስራ እድል መስፋፋት የሚያመቹ የፖሊሲ እርምጃዎችን መውሰድና የሚጨበጥ ውጤት ለማስመዝገብ መስራት ይገባል፡፡ የሕዝቡ የኑሮ ሁኔታ መሻሻል እንዲያሳይ የሚረዱ መሰረታዊ ለውጦች በየዘርፉ መታየት አለባቸው፡፡ ይኸንን በብቃት አከናውኖ ወደወጪ መጋራት አሰራር መግባት አሳማኝና ተገቢ ነው፡፡ ወደፊት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ለሚጠበቅባቸው የወጪ መጋራት ኃላፊነት የፋይናንስ ድጋፍ የሚሰጥ በሕግ የተቋቋመ ፈንድ ፈጥሮ ተግባራዊ ለማድረግ ከአሁኑ ጥናቶችና ቅድመ ዝግጅቶች ሊጀመሩ ይገባል፡፡ በዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ውስጥ የተማሪዎች ማህበራዊ ደህንነት ተቋሞች እንዲፈጠሩና ለተማሪዎች መኝታና ቀለብ ወጪ መሸፈኛ ድጋፍ የሚያደርጉበትን ሁኔታ በቅድሚያ መመስረት ያስፈልጋል፡፡ ተማሪዎች በትምህርት ቆይታ ጊዜያቸው ለሚደርስባቸው አደጋና የጤና ችግር ሽፋን የሚሰጡ የመድህን ዋስትና ፕሮግራሞችን በቅድሚያ ማዘጋጀት ይገባል፡፡

ብዙ ዜጎች ከፍተኛ ትምህርት የመማር ፍላጎት እያሳዩ ነው፡፡ በስራ ውስጥ ያሉ አብዛኞቹ ዜጎች ከፍተኛ ትምህርት ተከታትለው ስራቸውን ማሻሻል ይፈልጋሉ፡፡ ስራ የሌላቸውም ስራ የማግኘት እድላቸውን ለማስፋት የከፍተኛ ትምህርት መከታተል ይፈልጋሉ፡፡ ጥቂቶች ደግሞ ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ ከማሳለፍ የከፍተኛ ትምህርት መከታተል ይፈልጋሉ፡፡ በእነዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የከፍተኛ ትምህርት መከታተል የሚፈልጉ ዜጎችን ጥያቄ የሚያስተናግድ አደልት

ኢጁኬሽን ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል። ኮሌጆችና ዩኒቨርስቲዎች ለዚህ ዓላማ መሳካት የተጠናከረ የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ዘርግተው በስራ ላይ ማዋል ይገባቸዋል። ኮሌጆችና የዩኒቨርሲቲ ተቋሞች ባልተከፈቱባቸው የሀገሪቱ ክልሎች ንዑስ ማዕከላት እንዲቋቋሙና የተከታታይ ትምህርት ፕሮግራም ዘርግተው በስራ ላይ ማዋል ይገባቸዋል። ኮሌጆችና የዩኒቨርስቲ ተቋሞች ባልተከፈቱባቸው የሀገሪቱ ክልሎች ንዑስ ማዕከላት ከፖለቲካና ከሃይማኖት ገለልተኛ በሆነ መንገድ ተደራጅተው እንዲሰሩ በማድረግ የአጭርና የረጅም ጊዜ ስልጠናዎችን ሊሰጡ ይገባል። እንደሁኔታው የሙሉ ጊዜ ወይም የትርፍ ጊዜ አስተማሪዎችን እየመደቡ በማሰራት በቋንቋ፣ በሕግ፣ በሂሳብ መዝገብ አያያዝ፣ በኮምፒዩተርና በሌሎችም የተፈጥሮና ማህበራዊ ዘርፎች የሰርተፊኬት፣ የዲፕሎማና የዲግሪ ፕሮግራሞችን ማካሄድ ይገባል። የሞያ ስልጣን የሚሰጡ ተቋሞችም በተመሳሳይ መንገድ እየሰሩ አገልግሎት የሚያቀርቡበትን ስርዓት መከተል ያስፈልጋል።

የምርምር ስራዎች የሚያካሂድ ልዩ ልዩ የምርምር ተቋሞችና ኢንዱስትሪዎች ሊኖሩ ቢችሉም ዩኒቨርስቲዎች ከፍተኛውን ኃላፊነት መሸከም እንዳለባቸው የታወቀ ነው። የሀገሪቱ ከፍተኛ ትምህርት ከምርምር ጋር የተሳሰረ እንዲሆን ማድረግ መሰረታዊ ጉዳይ ነው። አንዳንዶቹ የምርምር ስራዎች በተለይ በተፈጥሮ ሳይንስ መስክ የሚካሄዱ በሚሆኑበት ጊዜ ትልቅ ፋሲሊቲና የቡድን ምርምርን ይጠይቃሉ። የፋይናንስ ፍላጎታቸውም ግዙፍ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ዓይነቶቹን ትላልቅ የምርምር ስራዎች የመንግስት ፈንድ በሚያገኙ ሌሎች ተቋሞች ማድረግ ይመረጣል። ዩኒቨርስቲዎች በመሰረታዊ ምርምር ላይ ሰፋ ያለ ትኩረት እንዲሰጡ በማድረግ ከተግባርና ከልማት ጋር የተያያዙ ምርምሮችን ለሚሰሩ ተቋሞችና ለኢንዱስትሪ ላቦራቶሪዎች እንደ አጋዥ ሆነው የሚሰለፉበትን አሰራር መከተል ተመራማሪዎችንና ለምርምር የሚወጣውን ሪሶርስና የምርምሩን ግኝት በተቀናጀ መንገድ ለመጠቀም ያስችላል። ለምሳሌ ኢንሳይክሎፒዲያ ማዘጋጀት በዩኒቨርስቲ ተመራማሪዎች የሚካሄድ ቢሆን አካባቢን የሚመለከት ምርምር ደግሞ በአካባቢ ጥበቃ ምርምር ማዕከል ሊካሄድ ይችላል። ነገር ግን በሁለቱም ስራዎች የሚካሄዱ ምርምሮች የሁለቱንም ወገን ትብብርና ግንኙነት የሚጠይቅ ነው። ስለሆነም በዩኒቨርስቲና በሌሎች ተቋሞች መካከል ጠንካራ ቅንጅታዊ ስራ እንዲኖር ከተደረገ በሀገሪቱ ውስጥ በሁሉም የምርምር ተቋሞች የሚካሄዱ ስራዎች ችግር ፈቺና የሀገሪቱን ፍላጎት የሚያሟሉ እንዲሆኑ ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል። ብዙዎቹ በመንግስትና በግል ተቋሞች የሚካሄዱ ስራዎች በቅድሚያ ሳይንሳዊ ምርምር እንዲካሄድባቸውና የተመራማሪዎችን ምክር በማግኘት እንዲሰሩ የሚያስፈልግበት ደረጃ ላይ ተደርሷል። ስለዚህ በምርምር ተቋሞች መካከል ብቻ ሳይሆን በምርምር ተቋሞች፣ በመንግስትና በልማት ድርጅቶች መካከልም ጠንካራ ትስስር እንዲኖር በማድረግ መስራት ይገባል።

በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄደው ምርምር ችግር ፈቺ እንዲሆን ከተፈለገ ግልፅ የምርምር ፖሊሲ መኖር አለበት። ይህ ፖሊሲ የምርምር ነፃነትን የሚያረጋግጥ እንዲሆን ያስፈልጋል። በሀገሪቱ ፌዴራላዊ አወቃቀር መሰረት በምርምር ተቋሞች መካከል የስራ ክፍፍል በሚኖርበት አቅጣጫ የተቃኘ ፖሊሲ መሆን አለበት። በመጀመሪያ ደረጃ መሰረታዊ በሆነ የምርምር ስራ ረገድ ምን ዓይነት ምርምር መካሄድ እንዳለበት የመወሰንና ውጤቱንም የመገምገም ኃላፊነት ለምርምር ተቋሞቹ መተው ያለበት ነው። በተግባራዊና የልማት ምርምር መስኮች ደግሞ የምርምር ፕሮጀክቶችን በመምረጥና ውጤታቸውንም በመገምገም ረገድ መንግስት፣ የግል ኩባንያዎች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ማህበራትና ድርጅቶች ሰፊ ተሳትፎ ሊኖራቸው ይገባል። በተለይም መንግስት በግል ኩባንያ ለማሰራት ወጪያቸው ከባድ የሆኑ የምርምር ፕሮጀክቶችን በፋይናንስ መደገፍ ይገባዋል። ምርምሩን ለሚሰሩ ተቋሞች ደግሞ የታክስ ቅናሽ በማድረግ ወይም እርዳታና ድጋፍ በማድረግ ማበረታቻ ሊሰጥ ይችላል።

## 2.5.4 ስኮላርሽፕና የተልዕኮ ትምህርት

የስኮላርሽፕ አገልግሎት መኖር ለከፍተኛ ትምህርት አንድ ጠቃሚ ቁምነገር ነው። ከሌሎች የውጭ ሀገር ከፍተኛ ትምህርት ተቋሞች ጋር ወዳጅነት መመስረትና ኢትዮጵያዊያን የስኮላርሽፕ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ይገባል። የስኮላርሽፑ ዓላማ ለሀገሪቱ የሚያስፈልጉትን ብቁ ሞያተኞች ማስገኘት እንደመሆኑ አሰራሩ ይሽንኑ ዓላማ ለማሳካት በሚያስችል ግልፅነት መመራት

ይገባዋል:: የስኮላርሽፕ እድል ዜጎች በእኩልነት የሚያገኙት እንጂ የመንግስት ስልጣን የያዙ ፓርቲዎች ለአባሎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው ውለታ መክፈያ መሆን አይገባውም:: በአሁኑ ጊዜ የስኮላርሽፕ እድል ለማግኘት የገዥው ፓርቲ አባል መሆን እንደቅድመ ሁኔታ የሚታይበት አሰራር በሚገባ ሰፍኗል:: የአጭርና የረጅም ጊዜ የውጭ ስልጠና የሚያገኙ ሰዎች መመዘኛ አካዳሚያዊ መሆኑ እየቀረ በፖለቲካ ወገንተኝነት እየተተካ ነው:: አውሮፓ፣ አሜሪካ፣ ኤዥያ፣ አውስትራሊያ ወዘተ. ሄደው የሚማሩት የገዥው ፓርቲ ታማኞች ብቻ የሆኑበት ሁኔታ በግልፅ ይታያል::

ሌላው ቀርቶ ከውጭ ሀገር በእርዳታና በብድር የሚገኝ የተልዕኮ ትምህርት ለመከታተል የሚችሉት የገዥው ፓርቲ መሪ ካድሬዎች ብቻ ናቸው:: ከኦፕን ዩኒቨርስቲ ጋር መንግስት በፈጠረው የተልዕኮ ትምህርት ግንኙነት ዋነኞቹ ተጠቃሚዎች የገዥው ፓርቲ ግንባር ቀደም ካድሬዎችና አባላት ናቸው:: 10ኛ ክፍል እንኳ በወጉ ያላጠናቀቁ ካድሬዎች የማስትሬት ፕሮግራም እንዲከታተሉና ማስረጃ እያገኙ ትላልቅ ሹመት እንደሚሰጣቸው የሚታወቅ ነው:: ከኦፕን ዩኒቨርስቲ ጋር የተደረገው ስምምነትም ሆነ ከሌሎች ጋር የሚካሄደው የስኮላርሽፕ ግንኙነት በኢትዮጵያ ስም በተገኘ ብድርና እርዳታ ላይ የተመሰረተ ነው:: በሀገር ስም በሚገኝ እርዳታና ብድር የአንድን ፓርቲ ካድሬዎች ብቸኛ ተጠቃሚ ማድረግ ፍትሃዊነት የጎደለው ብቻ ሳይሆን የለየለት ወንጀል ነው::

ስለዚህ የስኮላርሽፕና የተልዕኮ ትምህርት እድሎች ለሁሉም ዜጎች በእኩል ደረጃ መሰጠት ይገባቸዋል:: መመዘኛውም አካዳሚያዊ ብቃትና የሀገሪቱ የሞያተኛ ፍላጎት ሆኖ አሰራሩ ደግሞ ግልጽነትና ተጠያቂነትን መሰረት ያደረገ ሕጋዊ ስርዓት መዘርጋት አለበት:: ይሽንን ተግባር በኃላፊነት የሚመራ፣ ነፃ አደረጃጀትና አሰራር ያለው ተጠሪነቱም ለፌዴራል ፓርላማ የሆነ አንድ የውጭ ሀገር ስኮላርሽፕና ተልዕኮ ትምህርት ኤጀንሲ መቋቋም ይኖርበታል::

## 2.5.5 ማጠቃለያ

ከማንኛውም ፖሊሲ ሊቀረፅለት ከሚያስፈልግ ሀገራዊ ጉዳይ በላይ ትምህርት ከፍተኛ ጥንቃቄ የሚጠይቅ ነው:: የትምህርት ፖሊሲ ጉዳይ በበቂ ጥናትና ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ መቀረፅ ያለበት ስለሆነ በፖሊሲ አወጣጥ እረገድ ከፖለቲከኞች ይልቅ የባለሙያዎች ድርሻ ከፍተኛ መሆን አለበት:: በተለይም ጉዳዩን በዋናነት ሊያስፈፅሙ የሚችሉትና የሚገባቸው መምህራን በትምህርት ፖሊሲ አወጣጥ ላይ የሚኖራቸው ተሳትፎ ከፍተኛ መሆን ብቻ ሳይሆን በፖሊሲው ላይ አንፃራዊ የሆነ የተሟላ እምነት እንዲኖራቸው ያስፈልጋል::

ሌላው በትምህርት ፖሊሲ አወጣጥ ላይ ትልቅ ግምት ሊሰጠው የሚገባው ቁምነገር ለሀገሪቱ ወቅታዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ ትኩረት የመስጠት ጉዳይ ነው:: በአውሮፓና በአሜሪካ ተሞክሮ ውጤት ያመጣን አንድ ፖሊሲ ለመኮረጅ ሲፈለግ በቅድሚያ ሀገሪቱ ከሌሎቹ አገሮች ጋር በንፅፅር ያለችበት ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ ግምት ውስጥ ገብቶ በበቂ ሁኔታ መጠናት አለበት:: ፖሊሲው በወረቀት ላይ ሊቀመጥ መቻሉ ብቻ ሳይሆን የአፈፃፀሙና የአገማገሙ ሂደት በቅድሚያ ከነባራዊ ሁኔታ ጋር የሚጣጣም መሆኑ መረጋገጥ አለበት:: ከዚህ በተጨማሪ ትምህርት ከብሔራዊ ደረጃ አልፎ ዜጎችን በአለም አቀፉ ደረጃ ለማግባባትና ለማስተሳሰር የሚያስችል ባህሪ ያለው በመሆኑ በተቻለ መጠን የትምህርት ስርዓት በብሔራዊ ደረጃ (Uniformity) የተማከለ አሰራርን እንዲከተልና ተመሳሳይነት ያለው እንዲሆን ማድረግ ጠቃሚ ይሆናል::

# 3. ጤና

## 3.1 አጠቃላይ ሁኔታ

በአገራችን የጤና ይዞታ እጅግ ደካማ ነው:: ኢትዮጵያ በሽታ የተንሰራፋባት አገር ናት:: የበርካታ ሕፃናት መሞትና ሰዎች በሕይወት የሚቆዩበት የዕድሜ መጠን ማነስ አገራዊ የጤና ይዞታ ዝቅተኛነትን ያመለክታሉ:: የሕክምና መስጫ ተቋማትና የሕክምና አገልግሎት የሚገኙት እጅግ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ ነው:: ሕዝቡም ስለ ጤና እንክብካቤና ጥንቃቄ ያለው ግንዛቤ ዝቅተኛ ነው::

በኢትዮጵያ ካሉት የጤና ችግሮች ብዙዎቹ ለመከላከል የሚቻሉ ተላላፊ በሽታዎችና ከአመጋገብ ጉድለት ጋር የተያያዙ በሽታዎች ናቸው:: የሕዝቡ ኢኮኖሚያዊ አቅም ዝቅተኛነት፣ ንጽሕና የሌላቸው አካባቢያዊ ሁኔታዎች፣ የጤና አገልግሎት ሽፋን ዝቅተኛነት እና የሌሎች ማኅበራዊ አገልግሎቶች አለመሟላት የአገራችንን የጤና ገጽታ የሞት ጥላ ያንዣበበት አድርጎታል::

በበሽታ ከሚሞቱ ሰዎች መካከል ሦስት አራተኛ የሚሆኑት በ10 በሽታዎች በአንዱ ወይም በጥምር በመያዝ ነው:: እነዚህም፣ 17 በመቶዎቹ በወሊድ ምክኒያት የሚሞቱ እናቶች፣ 14 በመቶዎቹ በሳምባና በመተንፈሻ አካላት መመረዝ፣ 14 በመቶዎቹ በወባ በሽታ፣ 8 በመቶዎቹ በተመጣጠነ የምግብ እጥረት የሚሞቱ ዕድሜያቸው ከአምስት ዓመት በታች የሚሆናቸው ሕፃናት፣ 8 በመቶዎቹ በተቅማጥ በሽታ፣ 7 በመቶዎቹ በኤድስ፣ እንዲሁም 5 በመቶዎቹ በሳምባ ነቀርሳ እንደሆነ ይገመታል:: በአገራችን ውስጥ ያለው የጤና ችግር በከፊል ከሥርዓተ ምግብ (ኑውትሪሽን) ይዞታ ዝቅተኝነት ጋር የተያያዘ ነው::

ልዩ ልዩ ጥናቶች እንደሚመለክቱት ኢትዮጵያ በዓለም ካሉ ከፍተኛ የአመጋገብ ጉድለት ከሚታይባቸው አገሮች አንዷ ናት:: የንጥረ ምግብ እጥረት በከፍተኛ ደረጃ ተንሰራፍቷል:: ከአምስት ዓመት በታች እድሜ ካላቸው ሕፃናት መካከል ግማሾቹ የተመጣጠነ ምግብ አያገኙም:: ሁለት ሦስተኛ የሚሆኑት ሕፃናት ደግሞ እድገታቸው ስንኩል ነው:: አሥር በመቶ ሚሆኑት ደግሞ የከሱና የቀጨጩ ናቸው:: በተመጣጠነ ምግብ እጥረትና በሌሎች የጤና ችግሮች የተጐዱ ሕፃናትን በአካል አቅመ ደካማና ምርታማነታቸውም ዝቅተኛ ነው:: በአእምሮ ፈዛዛና ዝቅተኛ የማሰብ ችሎታ ያላቸው በማድረግ ለእድሜ ልክ ችግርም ይዳርጋቸዋል::

በኢትዮጵያ ውስጥ አብዛኛው ሕዝብ የመጠጥ ውሃ የሚያገኘው ከወንዞችና ከሐይቆች ነው:: በገጠር የሚኖረው አብዛኛው ለመጠጥ፣ ለማብሰያና ለንፅሕና የሚጠቀምበትን ውሃ የሚያገኘው ከነዚህ የውሃ አካሎች ነው:: ከወንዞችና ከሐይቆች የሚገኘው ውሃ አብዛኛውን ጊዜ የሚያስተማምን ባለመሆኑ ለሰዎች የጤና መታወክ ዋና ምክንያት ነው:: ስለዚህም ወባን፣ ተቅማጥን የመሳሰሉት ውሃ-ወለድ በሽታዎች ዋና ዋና የጤና ችግሮች ሆነዋል::

ጤናን ለሕዝብ ለማዳረስ ትኩረት የሚያስፈልገው ጉዳይ በሽታን መከላከል ነው:: በኢንፎርሜሽን ልውውጥና በትምህርት አማካኝነት ሕዝቡ ስለ ጤና ያለውን ግንዛቤ ማሳደግ አስፈላጊ ነው:: ትኩረት መሰጠት ከሚገባቸው ነገሮችም ውስጥ ተላላፊ በሽታዎችንና ወረርሽኝን፣ ከተመጣጠነ ምግብ እጥረትና ንፅሕና ከጎደለው አኗኗር የሚመጡ በሽታዎችን መቆጣጠር ነው::

እስከአሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ በሀገራችን ውስጥ ዋነኛው የጤና አገልግሎት ሰጪ አካል መንግሥት ነው:: ይሁን እንጂ በጤናው ዘርፍ በቂ በጀት ባለመመደቡ የጤና አገልግሎት ተሽመድምዷል:: የጤና አገልግሎት መስጫ ተቋማት ብዛት፣ መልክዓ ምድራዊ ሥርጭትና የሚሰጡት አገልግሎት ስብጥር ብቃት የለውም:: በዘርፉ የተሠማሩት ባለሙያዎች ቁጥራቸው ጥቂት ናቸው:: በኢትዮጵያ ያለው የጤና አገልግሎት ስብጥር ከጠቅላላው ሕዝብ ከግማሽ ያነሱትን ብቻ ነው ሊያገለግል የሚችለው:: የጤና ማዕከሎችና የጤና ጣቢያዎች ቁጥር አንድ ላይ ሆኖና የሕዝብ ብዛት ምጥነት፣ አንድ የጤና አገልግሎት ድርጅት ለ22 ሺህ ሕዝብ ገደማ ነው::

# 3.2 አንፃራዊ ሁኔታ

በሕፃናትና የእናቶች ሞት፣ በተላላፊ በሽታዎችና በምግብ እጥረት አማካይነት በሕይወት የመኖር እድሜ በመሳሰሉት ተቀባይነት ባገኙ የጤና መለኪያዎች መሠረት ኢትዮጵያ በዓለም ዝቅተኛ ሥፍራ ላይ ከሚገኙት አገሮች መካከል ትመደባለች:: በ1992 ዓ.ም የነበረውን የኢትዮጵያንና የተመረጡ የአፍሪቃና የእስያ አገሮችን ሁኔታዎች በንጽጽር ማየት በጤናው ዘርፍ ከምን ደረጃ ላይ እንደምንገኝ ለመገንዘብ ይረዳል::

በጤና አገልግሎት በኩል ያለውን ሁኔታ ብንመለከት፤ በአገራችን አንድ ሐኪም ለ35 ሺህ ሰዎች እንዲሁም አንድ የሆስፒታል አልጋ ለ4140 ሰዎች ይደርሳል:: የሐኪሞች ስርጭት ከጠቀላላው የሐኪሞች ቁጥር ከ50 ከመቶ በላይ የሚሆኑት ተመደበው የሚሰሩት በአዲስ አበባ ከተማ ነው:: በአንፃሩ ግን በኬኒያ አንድ ሐኪም ለ27 ሺህ ሰዎች እንዲሁም አንድ የሆስፒታል አልጋ ለ602

ሰዎች ይደርሳል:: በሱዳን ደግሞ አንድ ሐኪም ለ9540 ሰዎችና አንድ የሆስፒታል አልጋ ለ919 ሰዎች ይደርሳል:: እንዲሁም በግብጽ አንድ ሐኪም ለ1573 ሰዎች እንዲሁም አንድ የሆስፒታል አልጋ ለ476 ሰዎች ይደርሳል::

የንፁሕ ውሃ አቅርቦትን ብንመለከት፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 22 ከመቶው ብቻ ንፁህ የመጠጥ ውሃ የሚያገኝ ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 77 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 13 በመቶው ብቻ ነው:: በአንፃሩ ደግሞ ከኬንያ ሕዝብ ንፁሕ የመጠጥ ውሃ የሚያገኘው ሕዝብ 40 ከመቶው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 89 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 25 በመቶው ነው:: በሱዳን ደግሞ ከጠቅላላው ሕዝብ 67 ከመቶው ንፁሕ ውሃ ሲያገኝ ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 86 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 60 በመቶው ነው:: እንዲሁም በግብፅ ከጠቅላላው ሕዝብ 94 ከመቶው ንፁሕ ውሃ ሲያገኝ ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 97 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 91 በመቶው ነው:: ከጠቅላላው የአፍሪቃ ሕዝብ 56 ከመቶው ንፁሕ ውሃ ሲያገኝ ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 86 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 43 በመቶው ነው::

በሌላ በኩል ደግሞ የመፀዳጃ አገልግሎትን ብንመለከት፤ ከኢትዮጵያ ሕዝብ 15 ከመቶው ብቻ የመፀዳጃ አገልግሎት ያለው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 58 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 6 በመቶው ብቻ ነው:: በአንፃሩ ደግሞ ከኬንያ ሕዝብ የመፀዳጃ አገልግሎት ያለው ሕዝብ 86 ከመቶው ሲሆን ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 96 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 81 በመቶው ነው:: በሱዳን ደግሞ ከጠቅላላው ሕዝብ 62 ከመቶው የመፀዳጃ አገልግሎት ሲኖረው ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 87 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 48 በመቶው ነው:: እንዲሁም በግብፅ ከጠቅላላው ሕዝብ 94 ከመቶው የመፀዳጃ አገልግሎት ሲኖረው ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 98 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 91 በመቶው ነው:: ከጠቅላላው የአፍሪቃ ሕዝብ 60 ከመቶው የመፀዳጃ አገልግሎት ሲኖረው ከዚህ ውስጥ ከከተማው ሕዝብ 85 ከመቶው ከገጠሩ ሕዝብ ደግሞ 45 በመቶው ነው::

በአገራችን ከሚወለዱት ሕፃናት ውስጥ 11 ከመቶዎቹ አንድ ዓመት ሳይሞላቸው ይሞታሉ:: በዚሁ ወቅት የነበረው የሕፃናት ሞት ኬንያ 7 ከመቶ፣ ሱዳን 7 ከመቶና፣ ግብፅ 5 ከመቶ ነው:: እንደዚሁም ከ35 ዓመታት በፊት የሕፃናት ሞት በሲንጋፖር 6 በመቶ፣ በሆንግ ሆንግ 3 በመቶ፣ በኮሪያ 6 በመቶ፣ በፊሊፒንስ 7 በመቶ፣ በማሌዥያ 6 በመቶ፣ በታይላንድ 9 በመቶና በኢንዶኔዢያ 13 በመቶ ነበር::

በኢትዮጵያ የአንድ ሰው አማካይ እድሜም 43 ዓመት ብቻ ሲሆን በኬንያ 51 ዓመት፣ በሱዳን 55 ዓመት፣ በግብፅ 67 ዓመት ሲሆን፣ የአፍሪቃ አማካይ ደግሞ 54 ዓመት ነው:: እንደዚሁም ከ35 ዓመታት በፊት አማካይ እድሜ በሲንጋፖር 66 ዓመት፣ በሆንግ ኮንግ 68 ዓመት፣ በኮሪያ 57 ዓመት፣ በፊሊፒንስ 56 ዓመት፣ በማሌዥያ 58 ዓመት፣ በታይላንድ 56 ዓመትና በኢንዶኔዢያ 44 ዓመት ነበር::

## 3.3 የግሉ ዘርፍ

በጤናው ዘርፍ የግል ባለሀብቶች ተሳትፎ በተለይም በአድስ አበባ ከተማና በአንዳንድ ሌሎች ከተሞች እያደገ መጥቷል:: የግሉ ዘርፍ እንቅስቃሴ በክሊኒኮችና በሆስፒታሎች አማካኝነት ሕክምና በመስጠትና መድኃነቶች ከማቅረብ ጋር የተያያዘ ነው:: በጤናው ዘርፍ ካሉት ልዩ ልዩ አገልግሎቶች ውስጥ የግል ዘርፍ ተሳትፎ ጎልቶ የሚታየው የመድኃኒት አገልግሎት ዘርፍ ነው:: ይኸውም መድኃኒት ማምረትን፣ ማስመጣትንና ማከፋፈልን ያካትታል::

በአገራችን ካሉት ፋርማሲዎች ሁለት ሦስተኛዎቹና ከመድኃኒት መደብሮችና መድኃኒት ቤቶች 90 በመቶዎቹ የግል ባለሀብቶች ንብረቶችና በእነርሱም የሚተዳደሩ ናቸው:: በተጨማሪም በአዲስ አበባ ውስጥ ወደ 30 የሚጠጉ መድኃኒት አስመጪዎች ወይም ጅምላ ሻጭዎች ይገኛሉ::

በግል ይዞታነቱ በግልጽ የሚታወቀው ባሕላዊ መድኃኒት በጤናው ዘርፍ ከፍተኛ ሚና ይጫወታል:: ባሕላዊ ሕክምና፣ የባሕል ወጌሾችን እንዲሁም ሕዝቡ ራሱ ከልዩ ልዩ እፅዋት የሚቀመመውን መድኃኒት፤ ሃይማኖታዊ ተቋማትና ሥነ ሥርዓቶችን ጨምሮ በአገራችን የጤና አገልግሎት ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው::

## 3.4 ጤናና እድገት

ጤንነት ማለትም የአካል፣ የአእምሮና የማኅበራዊ ደህንነት፣ ደስተኛ ኑሮ ለመኖርና ከፍተኛ ምርታማነትን ለመቀዳጀት አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ ተጨባጭ ግቦች ሊተለሙ ይገባል:: ከእነዚህ ግቦች ለመድረስ የአገር ውስጥና የውጭ ድጋፎችን በሠፊው ለመጠቀም አግባብ ያላቸው ዘዴዎችና አቅጣጫዎች መከተል ይገባል:: በተለይም የሕዝብ ንቁ ተሳትፎና የራስ አቅምን ማጎልበት ቁልፍ ሚና ስለሚጫወቱ እነዚህ ባህሎች እንዲስፋፉና እንዲዳብሩ የማኅበራዊና ፖለቲካዊ ሁኔታዎችን ማመቻቸት አስፈላጊ ነው::

ተገቢ የጤና ፖሊሲ የሕዝብ እድገትን፣ የምግብ አቅርቦትን፣ ተስማሚ የኑሮ ሁኔታዎችንና ሌሎችም ለጤና መሻሻል በጣም አስፈላጊ የሆኑ ጉዳዮችን ከሚመለከቱ ፖሊሲዎች ተነጥሎ የሚታይ አይደለም:: በአጠቃላይ የጤና አገልግሎት ዕድገት ለሰብአዊነት ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚና ማኅበራዊ ልማት አስፈላጊ ከሆኑ ጥቅል ግብዓቶች አንዱ አካል ሆኖ መታየት አለበት:: እንዲሁም ለሕዝብ ፍትሕና እኩልነት መጠበቂያ መሣሪያ ሊሆን ይችላል::

ከጤና አገልግሎት በተጨማሪ፣ በጤና ይዞታ ላይ ተፅእኖ የሚያሳድሩ ሌሎች ችግሮች አሉ:: ጤናን በተመለከተ የአንደኛ ደረጃ ትምህርት አሰጣጥ አሳሳቢ ሲሆን፣ የንፁሕ ውሃ አቅርቦት አለመኖር ሌላው ነው:: የትምህርቱ ዘርፍ መጠናከር በረጅም ጊዜ ውስጥ የጤንነት ይዞታን በማሳደግ ረገድ የጤና እንክብካቤን ያህል አስፈላጊ ነው:: በትራንስፖርትና በጤና መካከልም ግንኙነት አለ:: የመንገዶች መገንባት የጤና አገልግሎት አሰጣጥን ቀላልና ቀልጣፋ ያደርገዋል:: በልላ በኩል ደግሞ የበሽታዎችን መዛመትና ሥርጭት ይጨምራል:: በአጠቃላይ የአገራችንን የጤና ሁኔታ ለማሻሻል ከተናጠልና በአንድ ዘርፍ ከሚደረጉ ጥረቶች ይልቅ የተቀናጁ ጥረቶችን ማድረግ አስፈላጊ ነው::

ድህነትን ለመቀነስ ትኩረት ማግኘት ካለባቸው ጉዳዮች ውስጥ የጤና አገልግሎት አንዱ ነው:: የተሟላ ጤንነት የሰዎችን ችሎታ ለማሻሻል፣ ብሎም ኑሮን መልክ ለማሲያዝ ከፍተኛ ጠቀሜታ አላቸው:: የጤና አገልግሎት እኩል ዕድል ማግኘት መሠረታዊ ሰብአዊ መብት ነው:: የጤና አገልግሎትን በተመለከተ ለዜጎች ሁሉ እኩል ዕድል መስጠት ይቻላል፣ ይገባልም:: ሰዎች ከተማም ይኑሩ ገጠር፣ ዳር አገርም ይኑሩ መሃል፣ ደጋም ይኑሩ ቆላ፣ በዘር፣ በሀብት፣ በሃይማኖት፣ ወዘተ፣ አድልዎ ሳይደረግባቸው የትምህርትና የጤና አገልግሎት እኩል ተጠቃሚ መሆን ይችላሉ፣ አለባቸውም:: በመሆኑም የጤና አገልግሎትን በስፋትና በጥራት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ማሰራጨት ድህነትን ለመቀነስ ጉልህ አስተዋጽኦ አለው::

በጤና በኩል ሕዝቡ በቀላሉ ለመከላከል በሚቻሉ በሳንባ ነቀርሳ፣ ወባና የዘመኑ በሽታ በሆነው ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በመሳሰሉ ተላላፊ በሽታዎች እያለቀ ነው:: የንጹህ ውሃ አቅርቦትና ተገቢ የንጽሕና አገልግሎት አለማግኘት፣ እንዲሁም በገቢ ዝቅተኛ መሆን ምክኒያት የተመጣጠነ ምግብ አለማግኘት (መቀነስ)፣ የአካባቢ ሁኔታዎች መበላሸት፣ እንዲሁም የጤና ሽፋንና የማኅበራዊ አግልግሎት አቅርቦት ዝቅተኛ መሆን ለመጠነ ሰፊ የጤና ችግሮች ምክኒያት ሆነዋል::

## 3.5 ቅድሚያ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች

ጤንነትን መጠበቅ የግል ኃላፊነት መሆኑን የሚያስርፁ ፅንሰ-ሃሳብና ድርጊቶችን ለማስፋፋት እንዲሁም ስለጤንነት የሚያስፈልገውን ግንዛቤ ለማጎልበት የመረጃ፣ የትምህርትና የመገናኛ መርሐ-ግብሮች ተገቢውን ትኩረት እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ነው:: ወረርሽኝና ተላላፊ እንዲሁም ከምግብ ማነስና ከዝቅተኛ የኑሮ ሁኔታዎች ጋር የተያያዙ በሽታዎችን መከላከልና መቆጣጠር፣ የሠራተኞችን ጤንነትና ደህንነት ማራመድ፣ የአካባቢ ደህንነትን ማጎልበት፣ የጤና ኢንፍራስትራክቸር ማቋቋም፣ ተስማሚ የጤና አገልግሎት አመራር ሥርዓትን መቅረጽ፣ የመሳሰሉት የጤና እንቅስቃሴዎች ይበልጥ ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል::

ለቤተሰብ በተለይ ለሴቶችና ለሕፃናት፣ በግንባር ቀደምትነት በማምረት ተግባር ላይ ለሚሳተፉ፣ እስከዛሬ ድረስ ተረስተው ለቆዩት አካባቢዎችና የኅብረተሰብ ክፍሎች እና በሰው ሠራሽና በተፈጥሮ አደጋዎች ለተጠቁ የጤና አገልግሎት ፍላጎት ልዩ ትኩረት መስጠት ተገቢ ነው::

በጤናው መስክ በቂና አግባብ ያለው የሰው ኃይልን ለማፍራት በግምባር ቀደምና በመካከለኛ ደረጃ የሠለጠኑ በተለይም በኅብረተሰቡ ፍላጎት ያተኮሩና ለተግባር የተዘጋጁ የጤና ባለሙያዎችን ማሠልጠን ቅድሚያ መሰጠት ያለበት ሌላው ጉዳይ ነው።

ዋና ዋና የጤና ችግሮች ላይ ያተኮረ ተግባራዊ ምርምርን ከፍተኛ ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል። የአስፈላጊ መድኃኒቶች፣ የሕክምና ግብዓቶች መሣሪያዎችና አገልግሎቶች አቅርቦትን ማጠናከር ትኩረት ማግኘት አለበት። ፈዋሽና የማገገም አገልግሎቶች የአእምሮ ጤንነትን ጨምሮ ተገቢውን ድጋፍ ሊሰጣቸው ይገባል።

የባሕል መድኃኒቶች በስፋት በጥቅም ላይ የወሉ ከመሆናቸውም በላይ ሥርጭታቸውም ሁሉን አካባቢ ያዳረሰ ነው። በመሆኑም የባህል መድኃኒቶችን ጠቃሚ ጎን ለማጎልበት ተገቢው ትኩረት መስጠትና ከዚህም ጋር የተያያዙ ምርምሮች እንዲሁም ከዘመናዊ የሕክምና ዘዴዎች ጋር ቀስ በቀስ ለማቀናጀት የሚረዱ ዘዴዎችን ማበረታታት አስፈላጊ ነው።

ኤች.አይ.ቪ/ኤድስ በሁላችንም ላይ እያስከተለ ያለውና ሊያስከትል የሚችለው የእልቂት አደጋ እጅግ አሳሳቢ ነው። በዚህ ከቀጠለ ሁላችንም አንኖርም፣ ትውልድም አይኖርም። በቅድሚያ በሕይወት መኖር ከድህነት መቀነስ አጀንዳ በላይ የሚያሳስበን ነው። ይህን መቅሰፍት መዋጋትና ማሸነፍ የሁላችንም ግዴታ ነው። ይህ መቅሰፍት ከሌላ አቅጣጫ ሲመጣ ፊት ለፊት ልናየው የምንችለው ጠላት አይደለም። ሚና ለይቶ የሚዋጋ ጠላት አይደለም፣ እኛው ውስጥ አብሮን ተቀላቅሎ የሚኖር እንጂ። ስለሆነም ሁላችንም በጋራ ሁላችንን መከላከል አለብን።

## 3.6 በመከላከል መርህ የሚመራ የጤና አገልግሎት

ምንም እንኳ የጤና እንክብካቤ በዋናነት የእያንዳንዱ ግለሰብ ኃላፊነት ቢሆንም ጠቅላላውን ሕብረተሰብም የሚመለከት ጉዳይ መሆኑ የታወቀ ነው። ሁሉም ዜጎች ያላቸው የፋይናንስና የማህበራዊ ሁኔታ ከግምት ውስጥ ሳይገባ ጤንታቸውን ለመንከባከብና ለመጠበቅ ተመሳሳይ እድል ሊኖራቸው ይገባል።

የሀገራችን የጤና ፖሊሲ መመስረት የሚገባው በመከላከል መርህ ላይ ነው። የዚህ ፖሊሲ ዓላማ ማንኛውም ሰው ጤንነቱን የመጠበቅ የራሱ ኃላፊነት መሆኑን ተገንዝቦ በጤንነት ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን እንዲያስወግድ ማድረግ ነው። የመከላከያ ወይም የቅድሚያ ምርመራ ስራ ማካሄድ ለዚህ ዓላማ ተግባራዊነት ቁልፍ ጉዳይ ነው። በሀገራችን የተለመደና የቆየ አንድ አባባል ከዚህ ነጥብ ጋር ተስማሚነት አለው። ይኸውም «ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መጠ ንቀቅ» የሚለው አባባል ነው። የመከላከል ተግባር በሕዝቡ ተቀባይነት እንዲያገኝና ውጤታማ እንዲሆን የመንግስትና የግል ተቋሞች፣ የኃይማኖትና የባህል ድርጅቶች የጤና መረጃና ትምህርት በማቅረብ ሰፊ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው። በእርግዝና ጊዜ ጥንቃቄ ማድረግ፣ ለእናቶች፣ ለሕፃናትና ለተማሪዎች የጤና ትምህርት መስጠት፣ የአልኮል መጠጥና የአደገኛ እፅ ሱሰኝነት የሚያስከትለውን የጤና ችግር በሚገባ ማሳወቅ፣ በከፋ ሁኔታ የታመሙትን ወይም በሕመም ምክንያት የተጎዱትን ለመርዳት የሚያስችል ፕሮግራም ዘርግቶ ተግባራዊ ማድረግ፣ ከጎጂ ባህልና ኋላቀር በሆነ ልማዳዊ አሰራር የጤና ችግር እንዳይደርስ ማስተማር ወዘተ. የመሳሰሉትን ስራዎች መስራት የመከላከሉን ጥረት የተሳካ ለማድረግ ያግዛል። የተለያዩ ዓይነት ምርመራዎችን ማድረግ ለቅድመ በሽታ ጥንቃቄ ስለሚረዳ ዜጎች በሚችሉት አቅም ይኸንን ባህል እንዲለማመዱ ማድረግ ያስፈልጋል።

ኤድስን (AIDS) መዋጋት እጅግ ከፍተኛ ጥረት የሚጠይቅ ከባድ ተግባር ነው። ሕዝቡን ከኤች አይ ቪ (HIV) ጥቃት ለመከላከልና በተመሳሳይ ሁኔታ በቫይረሱ ለተጠቁና ምልክት ለታየባቸው ሰዎች የምክርና የእንክብከቤ አገልግሎት ለመስጠት የሚያስችል ፕሮግራም ቀይሶ ስራ ላይ ማዋል ይገባል። በቫይረሱ የተጠቁት ወገኖች የመገለል ችግር እንዳይደርስባቸው ማድረግ ኤድስን በመዋጋቱ ተግባር ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ነው። ይህ በሽታ ውጤታማ ክትባትና ሕክምና እስኪገኝለት ድረስ ስርጭቱን ለመግታት የተሻለው ዘዴ ማስተማርና የምክር አገልግሎት መስጠት ነው። ዜጎች ራሳቸውን ከበሽታው የመከላከልና ለሌሎችም ጤንነት የመጠንቀቅ ኃላፊነት እንዲሰማቸው የሚያደርግ፣ የባህርይ ለውጥ እንዲፈጠርና ለሕይወት ዋጋ መስጠት እንዲዳብር የሚያስችል ፕሮግራም መቀየስ ያስፈልጋል።

መንግስት የኤድስ ወረርሽኝን ለመከላከል አሁን እያደረገ ከሚገኘው ጥረት በብዙ እጥፍ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይጠበቅበታል። በተለይም የመንግስት መገናኛ ብዙሃን በዚህ አረገድ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ ነው።

ከመከላከሉ ስራ ጋር አብሮ መያያዝ የሚገባው የአመጋገብ ባህልን የመቀየር ጉዳይ ነው። በሀገራችን ለጤንነት አጠባበቅ ተስማሚ የሆኑትን በቀላል ዋጋና በዝቅተኛ ድካም ሊገኙ የሚችሉትን ቅጠላ ቅጠሎች የመመገብ ባህል የለም። በቂ የካሎሪ መጠን ማግኘትና በሚፈለገው ደረጃ ተመጣጣኝ ማድረግ ከኢኮኖሚ አቅም ጋር የተያያዘ ቢሆንም ያለውን እንኳ ለማመጣጠን ቢሞከር ብዙ የጤና ችግርን መከላከል ይቻላል። ስለዚህ የመከላከሉ ፖሊሲ የአመጋገብ ባህልን ከማሻሻል ጋር ተያይዞ መካሄድ ይኖርበታል። በመከላከሉ ስራ ትኩረት ማግኘት የሚገባው የራስንና የአካባቢን ንፅህና የመጠበቅ ጉዳይ ነው። የመኖሪያና የስራ አካባቢን ንፅህና በመጠበቅ ብዙ ዓይነት ተላላፊ በሽታዎችን መከላከል ይቻላል።

የጤና ችግር ያጋጠማቸውን ዜጎች በማከም ረገድ ሀገሪቱ መከተል የሚገባት ፖሊሲ ለሕመምተኛ የሚሰጠው መድኃኒት ጥራት፣ ውጤታማነትና ሌላ ጉዳት የማያስከትል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስርዓት ማስፈን ነው። መድኃኒቶች በጥራት ተሰርተው በስርዓት የሚከማቹና በከፍተኛ ጥንቃቄ ለተጠቃሚው የሚሰራጩ መሆኑን በቅድሚያ ማረጋገጥ ይገባል። ይኸንን የጥራት ቁጥጥር ማሟላታቸው ከተረጋገጠ በኋላም ቋሚ ቁጥጥር ማድረግ አደጋዎች በፍጥነት እንዳይደርስባቸውና የመፍትሔ እርምጃዎችም እንዲወሰዱ በማድረግ የሕዝብን ጤንነት መጠበቅ ይቻላል። ይኸንን ለማስፈፀም የሚያስችል ሕግ ማውጣት ይገባል። ሕጉ ዝርዝር የጥንቃቄ ሕጎችን የሚያካትት ሆኖ መድኃኒት በማምረት ስራ የተሰማሩ ማድረግ ስለሚገባቸው ጥንቃቄ፣ የትኞቹ መድኃኒቶች በፋርማሲ ብቻ መሸጥ እንደሚገባቸው፣ የትኞቹ በሀኪም ትዕዛዝ ብቻ መሸጥ እንደሚኖርባቸው የሚደነግግ መሆን አለበት። ማንኛውም በቂ ጥራት በሌላቸው መድኃኒቶች አደጋ የደረሰበት ሰው ከመድኃኒት አምራቹ ካሣ መጠየቅና ማግኘት የሚያስችለው ሆኖ መደንገግ ይገባዋል።

በጤናው ዘርፍ ልዩ የመንግስት ትኩረት የሚያስፈልገው ሌላው ጉዳይ የወባ ወረርሽኝ ነው። ወባ ከጥንት ጀምሮ የሀገሪቱን ህዝብ እየገደለ የኖረና አሁንም እየገደለ ያለ በሽታ ነው። በአምራቹ ህዝብ ላይ የሚያሳድረው ተፅዕኖም ቀላል የሚባል አይደለም። ስለዚህ ይህንን ገዳይ በሽታ ለመቆጣጠር የሚያስችል ትኩረትና ጥረት በመንግስት በኩል መወሰድ አለበት።

# 4. የቋንቋ አጠቃቀምን በመተለከተ ኢዴፓ ያለው አቋም

## 4.1 ቋንቋ ምንድን ነው?

ቋንቋ የሰው ልጅ ከተናጠል ኑሮ ተላቅቆ በማኅበር መኖር ሲጀምር ለህልውናው መረጋገጥ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘው ሥርዓት ያለው የመግባቢያ መሣሪያ ነው። ሰዎች በተናጠል ይኖሩ በነበረበት ጊዜ አሁን ያሉት እንስሳት እንዳላቸው ዓይነት ደመ-ነፍሳዊ የሆኑ የስሜት መግለጫ ድምፆችና እንቅስቃሴዎች ነበሯቸው። በተናጠል መኖሩ ለህልውናቸው መቀጠል የማያዋጣ እየሆነ ሲመጣና በማኅበር በመኖርና በመተባበር መሥራት ሲጀምሩ ተግባራቸውን ውጤታማ ለማድረግ የሃሳብ መለዋወጫና የመግባቢያ ቋንቋ መኖር ወሳኝ እየሆነ መጣ። የማኅበራዊ ኑሮ ደረጃ እያደገና ውስብስብ እየሆነ ሲመጣ የቋንቋ ባህሪም በተመጣጣኝ ሁኔታ ውስብስብ እየሆነ መጣ። በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ ቋንቋ የሰው ልጅ ከፈጠራቸው መሣሪያዎች ሁሉ ወደር የሌለው መሣሪያ ሆኗል። የሰው ልጆች በአሁኑ ጊዜ በሆነ ምክንያት የመናገር፣ የመፃፍና በማንኛቸውም ዓይነት የመገናኛ ብዙሃን ስልቶች የመጠቀም ችሎታቸውን ድንገት ቢያጡ ዓለም ከፍተኛ ቀውስ ውስጥ ትገባለች።

ቋንቋ ከእንስሳት ቋንቋ በላቀ መልኩ መቼ እንደተጀመረ በእርግጠኝነት አይታወቅም። በግምት ግን የዛሬ 2 ሚሊዮን ዓመት ገደማ ሊሆን ይችላል ይባላል። ዘመናዊ መልኩን መያዝ የጀመረው ግን የዛሬ 40000 (አርባ ሺህ) ዓመት ገደማ እንደሆነ ይገመታል። ጽሕፈት የተጀመረው የዛሬ 6500 ዓመት ገደማ ነው ተብሎ ይገመታል።

ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ይሞታል። ሕዝብ ካለ ቋንቋ አለ። ቋንቋ ተወልዶ፣ አድጎ የሚሞተው ተናጋሪዎቹ በሆነ ሰው ሰራሽም ሆነ የተፈጥሮ ምክንያት ሲጠፉ፣ ቁጥራቸው ሲቀንስና በሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ሲዋጡ፣ ቋንቋው ለኑሮ ጥቅም የማያስገኝ ሆኖ ሲገኝና ሌላ አማራጭ ቋንቋ ሲኖር ነው። ለምሳሌ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ በርካታ ሕዝብ በተፈጥሮ አደጋ፣ በርሃብ፣ በጦርነት ወይም በወረርሽኝ በሽታ ሲያልቅ ቋንቋው ይጠፋል። በተለያየ ምክንያት ቁጥሩ ሲቀንስና በሌላ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝብ ሲከበብ፤ ቀስ በቀስ እየጠፋ ይሄዳል። በጦር ኃይል፣ በኢኮኖሚ፣ በሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ በሥነ ጥበባት፣ በፖለቲካ፣ በፍልስፍናና በሌሎች የእውቀት ዘርፎች የላቀ ደረጃ ላይ የደረሰ ሕዝብ እና ቋንቋው በእነዚህ ዘርፎች ደካማ የሆነ ሕዝብ አጠገብ ለአጠገብ ከሆኑ ቀስ በቀስ ያደገው ያላደገውን እየዋጠው ይሄዳል።

በተለያየ ተፈጥሮአዊ ምክንያት መዳከምና መሞት የጀመረን ቋንቋ ሕግ በማውጣት፣ በፖለቲካም ሆነ በሌላ ዓላማ ተነሳስቶ ከሞት ለማዳን መሞከር እጅግ በጣም አስቸጋሪ ነው። እንዲያውም አይቻልም ማለት ይቻላል። ለምሳሌ በአሁኑ ጊዜ የግዕዝ ቋንቋ ያለበት ሁኔታ ይታወቃል። ቀደም ሲል የሕዝብ የዕለት ተዕለት መግባቢያ የነበረ ቋንቋ ነው። ነገር ግን ተፈጥሮአዊ በሆነ ማህበራዊ ለውጥ ምክንያት የዕለት ተዕለት የጋራ መግባቢያነቱ እየቀነሰ መጥቶ በአሁኑ ግዜ በኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን በሥርዓተ ፀሎትና ሥርዓተ ትምህርት ማስፈፀሚያነት ተወስኗል። ይህም ሚና ቢሆን ቀስ በቀስ እየተዳከመና በአማርኛ እየተተካ ነው።

አሁን ግዕዝ የሕዝብ የዕለት ተዕለት መግባቢያ ቋንቋ ይሁን፤ መንግሥት የአስተዳደር ሥራውን በግዕዝ ያከናውን፤ ሕዝብ በግዕዝ ይገበያይ፤ ትምህርት በግዕዝ ይሰጥ፣ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፕሮግራሞች በግዕዝ ይሰራጩ፤ ጋዜጦች፤ መፅሔቶችና ወቅታዊ መጻሕፍት በግዕዝ ይታተሙ ይሰራጩ፣ አርቲስቶች በግእዝ ይዝፈኑ ቢባል ተግባራዊ ሊሆን የማይችል ጉዳይ ነው። ምንም ያህል ገንዘብና ጉልበት ቢፈስ፣ ምንም ዓይነት የማስገደጃ ሕግ ቢወጣ፣ የተፈለገው ውጤት አይገኝም። የማይገኝበትም ምክንያት ውሳኔው ከወቅቱ ሃገራዊ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር፤ ሊቀለበስ ከማይችል የታሪክ ሂደት ጋር፣ እንዲሁም ከአለም አቀፍ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የሚጋጭ በመሆኑ ነው።

በሌላውም ዓለም እንደሚታየው ሁሉ በሀገራችንም ከግዕዝ ቋንቋ በተጨማሪ በሌሎች ትላልቅ ቋንቋዎችና ባህሎች በመከበባቸው ወይም ትላልቅ ቋንቋዎችና ባህሎች በውስጣቸው በመስረጋቸው በመዳከምና በመጥፋት ላይ ያሉ ሌሎች ቋንቋዎችም አሉ። እነዚህ በዚህ የማይቀለበስ ታሪካዊ ሁኔታና ተፈጥሮአዊ በሆነ፣ ማለትም ከውጭ የሌላ ወገን አስገዳጅነት በሌለበት የተፈጥሮ ሂደት እየተዳከሙ የሚመጡ ቋንቋዎችን አይቀሬ ዕድል ለመለወጥ ጊዜ፣ ጉልበትና ሃብት ማፍሰስ ብልህነት አይሆንም። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ የመዳከሙ ሂደት ለማቆም በማይቻልበት ሁኔታ ቀጥሎ በመጨረሻ ቋንቋው መሞቱ አይቀርም። በዚህ ዓይነት ሂደት በዓለም ላይ ከተመዘገቡት ቋንቋዎች እስካሁን ድረስ ቢያንስ 113 ቋንቋዎች ሞተዋል። ብልህነት የሚሆነው ታሪክና የተፈጥሮ ሂደት ያመጣውን ሁኔታ በፀጋ በመቀበል የአላፊው ቋንቋ የዛሬ ተናጋሪዎች ለራሳቸውም ሆነ ለልጆቻቸው የተሻለ ነገ፣ የተሻለ ዕድል የሚያመጣላቸውን ቋንቋ በመያዝ ወደፊት መራመድ ነው። በፖለቲከኞችም ይሁን በሌላ የጎሳዊ ስሜት ተገፋፍቶ በመጥፋት ላይ ያለን ቋንቋ ከመጥፋት ለማዳንና የትምህርትና የአስተዳደር ቋንቋ ለማድረግ ከመጣርና ለልማት የሚውል ሃብት ጉልበትና ጊዜ ከማባከን በተጨማሪ መጪ ትውልድን መበደል ይሆናል። ይህም በትውልድና በታሪክ ተጠያቂነትን ያስከትላል።

ይህ መሆኑ እየታወቀ ሥልጣን ፈላጊ ፖለቲከኞችና ሌላ ጥቅም ፈላጊ ወገኖች ውስብስብ የሆነውን የቋንቋ ጉዳይ በተሳሳተ መንገድ ሊያናፍሱትና ሕዝቡን ወደተሳሳተ አቅጣጫ ሊመሩበት ይችላሉ። ቋንቋ በመሠረቱ የመግባቢያ መሣሪያ ቢሆንም በሌላ በኩል ደግሞ ከተናጋሪዎቹ ስሜትና ማንነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ መሆኑ ሕዝብን በጎ ወደሆነም ወደአልሆነም አቅጣጫ ለመሳብ እንደመቀስቀሻ መሣሪያ ሊያገለግል ይችላል። ጥቅም ፈላጊ ወገኖች ለሕዝብ ጥቅም የቆሙ በመምሰልና ጎሳዊ ስሜቱን በመቀስቀስ ሊቀለበስ በማይችል ሁኔታ እየተዳከመ ያለና መሞቱ የማይቀር ቋንቋን መማሪያ ቋንቋ ይሁን፣ በአካባቢ የመንግስት አካላትም የመሥሪያ ቋንቋ ይሁን ብለው ይከራከራሉ።

አንድ ብሔረሰብ ቋንቋውን፤ ጠንካራም ይሁን ሊቀለበስ በማይችል ሁኔታ በመዳከም ላይ ያለ፤ ለፈለገው ዓላማ የማዋል መብት አለው። እዚህ ላይ የሚነሳው ግን የመብት ጉዳይ ሳይሆን የብልህነት ጉዳይ ነው። የጎሳዊ ስሜት ሳይሆን የሚዛናዊነትና የዘለቄታ ጥቅም ጉዳይ ነው። አንድ

ቋንቋ የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንዲሆን ከመወሰኑ በፊት የሚከተሉት ጥያቄዎች ተነስተው ጥቂት ፖሊተከኞች ሳይሆኑ ሕዝብ በጋራ፣ በረጋ፣ በሰከነ አርቆ በሚያይና ሚዛናዊ በሆነ መንፈስ በሚካሄድ ውይይት ተካሄዶባቸው መልስ ሊሰጥባቸው ይገባል።

የቋንቋው ተናጋሪ ሕዝብ ብዛት ስንት ነው? በአካባቢው የበላይነት ያለው ቋንቋ ነው ወይስ የበላይነት ባለው ሌላ ቋንቋ የተከበበ ነው? ቋንቋው የሚያሳየው አዝማሚያ ጥንካሬውን ጠብቆ የመቀጠል ነው ወይስ በአካባቢው ባለ ቋንቋ እየተዋጠ የመሄድ? ሁሉንም የትምህርት ዓይነት በቋንቋው ለማስተማር የሚችሉ በቂ መምህራን ይኖራሉ? በየትምህርቱ ዓይነት በቋንቋው የተዘጋጁ በቂ የመማሪያ መጽሐፍት ይኖራሉ? ከአራተኛ ክፍል በላይ በቋንቋው ማስተማር ተማሪው ከክልሉ ሲወጣና በሥራ ዓለም ሲገባ በሀገሪቱ የትኛውም ክፍል እንዲሁም በውጭው ዓለም ብቁ ተወዳዳሪ ለመሆን ያስችለዋል? የሚሉት ጥያቄዎችና ቋንቋውን የአስተዳደር ሥራ ቋንቋ ለማድረግ በክልሉ ውስጥ ከሚገኙ ብሔረሰቦች ቅንብር በመዝገብ አያያዝ፣ በትርጉም፣ እንዲሁም ከማዕከላዊ መንግስትና ከአቻ ክልሎች ጋር ከሚደረግ መፃፃፍ አኳያ የሚከተሉት ሁኔታዎች በጥንቃቄ መታየት አለባቸው። ሕዝቡ በትምህርት አሰጣጥም ሆነ በአስተዳደር ስለቋንቋ አጠቃቀም በወሳኝነት በሚያይበት ጊዜ ከፖለቲካ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከሙያተኞችም የበሰለ፣ የሰከነ፣ ስሜታዊ ሳይሆን የአጭር ጊዜና የዘለቄታ ጠቀሜታን ያገናዘበ ምክር ማግኘት አለበት። ሕዝቡ ጉዳዩን ከግራና ከቀኝ ከአየና የፖለቲከኛውንና የሞያተኛውን ምክር ከአገናዘበ በኋላ የሚወስደው አቋም መከበር አለበት። ውሳኔው የጥቂት ፖለቲከኞች ሳይሆን የሕዝቡ መሆን አለበት።

## 4.2 ቋንቋ የሚማሩት እንጂ በዘር የሚወርሱት አይደለም

አንድ በአማርኛ ተናጋሪ ቤተሰብ ውስጥ የተወለደ ሕፃን ወዲያውኑ ወደ ቻይና ተወስዶ በቻይናዊ ቤተሰብ ውስጥ እንዲያድግ ቢደረግ አፍ መፍቻ ቋንቋው ቻይኒኛ እንጂ አማርኛ አይሆንም። ቋንቋ ከግለሰቡ ማንነት ጋር በቅርብ የተያያዘ ቢሆንም የሚማሩት እንጂ በዘር የሚወርሱት አይደለም። አንድ ሰው ከራሱ ቋንቋ በተጨማሪ ሌላ አንድ ቋንቋ አሳምሮ ሲያውቅ ልሣነ-ክልኤ፣ ባለሁለት ቋንቋ ይባላል። ከሁለት ቋንቋ በላይም ሊያውቅ ይችላል። የኢትዮጵያ ሕዝብ የተቀላቀለ ስለሆነ ብዙ ሕዝብ ቢያንስ ሁለት የኢትዮጵያ ቋንቋዎችን ይናገራል። ዘመናዊ ትምህርት ቀመስ ከሆነ ደግሞ ቢያንስ እንግሊዘኛ ይናገራል።

አንድ ቋንቋ በተለያየ ዘየ ሲነገር እያንዳንዱ ዘየ ቀበልኛ ይባላል። ለምሳሌ የሸዋ አማርኛ ከጎንደር ወይም ከጎጃም ወይም ከወሎ አማርኛ ለየት ይላል። በሸዋ፣ በወለጋና በሐረር ኦሮሚኛ መካከልም ልዩነቶች አሉ። የቀበልኛ ልዩነቶች እንጂ መሠረታዊ ልዩነቶች ግን አይደሉም።

አንድ ሰው የእናት (አፍ መፍቻ) ቋንቋውን በተለያዩ ምክንያቶች እርግፍ አድርጐ ሊተወው ወይም ሊረሳው ይችላል። በሌላ ቋንቋ መሥራት (መፃፍ፣ መናገር) ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማሕበራዊ ጠቀሜታ የሚያስገኝለት ከሆነ የራሱን ቋንቋ በፈቃዱ በመተው ጥቅም የሚያስገኝለትን ቋንቋ ይይዛል። ልጆቹም አፍ መፍቻ ቋንቋቸው የወላጆቻቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ መሆኑ ቀርቶ አዲሱ ቋንቋ ይሆናል።

## 4.3 በጥንት ጊዜ የታየ የቋንቋ አዝማሚያ ከአሁኑ ጊዜ አዝማሚያ ጋር ሲነፃፀር

በዓለም ላይ አንድ ቋንቋ ብቻ ነበረ፣ የዚያ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቁጥር እየበዛ ሲሄድ በተለያየ አቅጣጫ መበታተን መጣ፤ ይህም የቋንቋ ልዩነቶችን አስከተለ የሚል አፈታሪክ አለ። በታሪክ ተመራማሪዎች ዘንድ ያለው አመለካከት ለየት ያለ ነው። ያለው አስተሳሰብ የዓለም የመጀመሪያው ቋንቋ አንድ ሳይሆን ማህበራዊ ህይወት በጀመረባቸውና በኋላም የሰው ልጅ የሥልጣኔ መነሻ በሆኑ ማእከሎች ተጀመረ የሚል ነው። ስለዚህ በተለያዩ የማኅበራዊ ሕይወት ማዕከሎች የተለያዩ ቋንቋዎች ተጀምረዋል ማለት ነው።

አንድ አይነት ቋንቋ የሚናገሩ ሰዎች በአንድ አካባቢ ውስጥ ሲኖሩ ቁጥራቸው እያደገ ይሄዳል። የቦታ መጣበብ ሲመጣ ከዚያ ስብስብ ውስጥ የተወሰኑ ክፍሎች አዲስ መሬትና ለህይወት አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ነገሮችን ፍለጋ ወደየአቅጣጫው መፍለስ ይጀምራሉ። የተራራ ሰንሰለቶችን፣ በረሃማ

ቦታዎችን፣ ወንዞችን፣ ሸለቆዎችን፣ ባሕሮችን አቋርጠው እየራቁ ሲሄዱ ከእናት ሕዝባቸው ጋር የነበራቸው ግንኙነት እየተዳከመና እየተቋረጠ ይሄዳል። በአዲስ አካባቢ አዲስ ህይወት ይጀምራሉ።

አካባቢያቸውና የአኗኗራቸው ስልት እየተለወጠ በሄደ መጠን ቋንቋቸውም የዕለት ተእለት ህይወታቸው፣ የስነልቡናዊ፣ ማህበራዊና አካባቢያዊ ዓላማቸው ነፀብራቅ ነውና ለአዲሱ ህይወት በሚስማማ መልኩ እየተለወጠ ይሄዳል። ለምሳሌ ከእናት ግንዱ ተነጥለው የሄዱ ቡድኖች ሁለት ወይም ሦስት ወይም ከዚያ በላይ ከሆኑ የሚፈጠሩት ቋንቋዎችም የዚያን ያህል ይሆናሉ ማለት ነው። በዚህ ዓይነት ሂደት ቋንቋዎች እየተበራከቱ ሄዱ። በዚህ ዓይነት ሂደት በዓለም ላይ ከ3000 እስከ 4000 ቋንቋዎች ሊፈጠሩ ችለዋል የሚል ግምት አለ።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በዓለም ላይ የታዩ አስደናቂ ለውጦች የቋንቋዎችን የመከፋፈልና የመለያየት አዝማሚያን ለውጠውታል። የሳይንስና የቴክኖሎጂ መስፋፋት በዓለም ላይ በርካታ ሥርነቀል ለውጦችን አስከትሏል። የየብስ፣ የባሕርና የአየር መጓጓዣ ዘዴ እጅግ ፈጣን ሆኗል። ዘመናዊ የህትመት ጥበብ መስፋፋት አለምን በመፃሕፍት፣ በመፅሔቶች፣ በጋዜጦችና በሌሎች የህትመት ውጤቶች እንድትጥለቀለቅ አድርጓታል። የሳተላይት ሬዲዮ፣ ቴሌፎን፣ ቴሌቪዥን እንዲሁም የትምህርት ተቋማት በየደረጃው መስፋፋት፣ የፋብሪካ ውጤቶች በኃይለኛ የማስታወቂያ ጥበብ አማካይነት የዓለም ገበያዎችን ማጥለቅለቅ፣ የኮምፒውተር፣ የኢንተርኔትና የኢ- ሜይል መስፋፋት ዓለምን ወደ አንድ ትልቅ መንደርነት ለውጠዋታል። ሰዎች ረጅም ርቀቶችን በአጭር ጊዜ አቋርጠው በቀላሉ መገናኘት የሚችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል። ሕዝቦች በዚህ ሁኔታ በመገናኘ ታቸውና በመቀራረባቸው ህይወታቸውም ቀስ በቀስ መመሳሰል ጀምሯል። ይህ በመሆኑ ምክንያት ዛሬ ቋንቋዎችም ከመራራቅና በተለያየ መልክ ከመራባት ይልቅ የመቀራረብ፣ የመሰባሰብና የመመሳሰል አዝማሚያ እያሳዩ ነው። ይህ አዝማሚያ ከቀጠለ የዓለም ሰዎች ይበልጥ ከመቀራረባቸውና ከመመሳሰላቸው የተነሳ ምን ያህል ዘመን እንደሚወስድ ለማወቅ አይቻልም እንጂ ቋንቋዎችም እየተቀራረቡ በመምጣታቸው ምክንያት ቁጥራቸው እየቀነሰ መጥቶ በአንድ ወቅት የዓለም ሕዝብ አንድ ቋንቋ ወደሚናገርበት ደረጃ ይደርሳል የሚል ግምት አለ።

## 4.4 ቋንቋ አገናኝም አለያይም ነው

ቋንቋ በአንድ በኩል ሰዎችን የሚያገናኝ፤ የሚያግባባ መሣሪያ ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ በሰዎች መካከል የሚፈጠር አለያይ ግድግዳ ነው። የጥንት ሰዎች ከተናጠል ኑሮ ወደ ማህበራዊ ኑሮ የተሸጋገሩት መተባበር ለህልውናቸው መቀጠል ወሳኝ ሆኖ ስለአገኙት ነው። ዘመናዊ ሰዎችም መግባባትን፣ መተባበርን ከምን ጊዜውም የበለጠ ለሕይወታቸው አስፈላጊ ሆኖ አግኝተውታል። ስለሆነም በቋንቋ ልዩነት ምክንያት በሕዝቦች መካከል የሚፈጠረውን ያለመግባባት ግድግዳ ለማፍረስ በርካታ ጥረቶች በመደረግ ላይ ናቸው። እስከአሁን ድረስ አልተሳካም እንጂ በቋንቋ መለያየት ምክንያት በሰዎች መካከል የሚፈጠረውን ያለመግባባት ግድግዳ ለማስወገድ ይረዳል ተብሎ ታምኖበት የነበረውን «ኤስፔራንቶ» የተባለውን የዓለም ቋንቋ ለመፍጠርም ተሞክሮ ነበር። በአሁኑ ጊዜ በዓለም ላይ ካሉት ቋንቋዎች የዓለም ሕዝቦችን በጋራ መግባቢያነት በማገልገል ቀዳሚነቱን የያዘው ቋንቋ እንግሊዘኛ ነው። ይህ ቋንቋ ለ500,000,000 ያህል ሰዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋ ነው። በሁለተኛ ቋንቋነት የሚናገሩት ሰዎች ሲታከሉበት የቋንቋው ተናጋሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ ያድጋል። ምናልባትም ወደ አንድ ቢሊዮን ሊደርስ ይችላል። ቋንቋው በዓለም ላይ እንዲህ በስፋት በመነገሩ ሌሎች ቋንቋዎች የሚፈጥሯቸውን ግድግዳዎች በማለፍ ለዓለም ሕዝቦች በመግባቢያት ያገለግላል።

በአገራችንም ከ70 በላይ ቋንቋዎች አሉ። በሌላ አነጋገር እነዚህ ቋንቋዎች መግባባትን የሚያግዱ ግድግዳዎች ናቸው ማለት ይቻላል። አማርኛ ከእነዚህ ግድግዳዎች አብዛኞዎቹን በማለፍ የጋራ መግባቢያ ሆኖ ያገለግላል። ሌሎች በሥፋት የሚነገሩ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችም በየአካባቢያቸው እንደጋራ መግባቢያ ያገለግላሉ። ለምሳሌ በኦሮሚያ አካባቢ ያሉ ብሔረሰቦች ኦሮሚኛን እንደጋራ መግባቢያ ይጠቀሙበታል። በትግራይ አካባቢም እንደ ኩናማና ሳሆ ያሉ ብሔረሰቦች ትግርኛን እንደ ጋራ መግባቢያ ይጠቀሙበታል።

## 4.5 አንድ ቋንቋ ለተናጋሪው ሕብረተሰብ የተሟላ የመግባቢያ መሣሪያ ነው

አንድ ቋንቋ በቋንቋነት ባሕርይው ለተናጋሪው ኅብረተሰብ የተሟላ የመግባቢያ መሣሪያ ነው፡፡ የተናጋሪውን ዓለም አሟልቶ ይገልጽለታል፡፡ ከዚህ አንፃር ሁሉም ቋንቋዎች እኩል ናቸው፡፡ ለምሳሌ ወፍራምና ቀጭን ሰው ወይም አጭርና ረጅም ሰው በአካላዊ ባሕሪያቸው ይለያዩ እንጂ በሥነፍጥረታዊና በሰብአዊ ባሕሪያቸው እኩል ናቸው፡፡ አንድ ሰው ወፍራም ወይም ረጅም በመሆኑ ከቀጭኑ ወይም ከአጭሩ የበለጠ ሰው አይደለም፡፡ ቋንቋዎችም እንደዚሁ፡፡ ቋንቋዎች ሊበላለጡ የሚችሉት በሰዋስዋዊ ውስብስብነት ሳይሆን በመዝገበ-ቃላታቸው ሥፋትና ጥበት ነው፡፡ አንድ ኅብረተሰብ በእድገት የላቀ ስለሆነ ቋንቋውም ውስብስብ ይሆናል፤ ሌላው ህብረተሰብ ደግሞ ኋላቀር ስለሆነ ቋንቋውም ውስብስብነት የጎደለው ይሆናል ማለት አይደለም፡፡

የእንግሊዘኛ ቋንቋ ለእንግሊዞች፣ ለአሜሪካኖች፣ ለካናዳውያን፣ ለአውስትራሊያውያንና ለኒውዚላንዳውያን በቂ የመግባቢያ መሣሪያ ነው፡፡ አማርኛ ደግሞ ለአማርኛ ተናጋሪዎች በቂ የመግባቢያ መሣሪያ ነው፡፡ የኤስኪሞ ቋንቋ ለ ኤስኪሞዎች የተሟላ የመግባቢያ መሣሪያ ነው፡፡ ልዩነቱ ቀደም ሲል እንደተነገረው በቃላት ብዛት ላይ ነው፡፡ የእንግሊኛ ቋንቋ ቃላት ብዛት ወደ አንድ ሚሊዮን ይጠጋል፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ብዛት ምናልባት የዚህ አንድ ሦስተኛ ያህል ቢሆን ነው፡፡ የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ኅብረተሰብ በሳይንስና ቴክኖሎጂ እየገፋ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊ ሕይወቱ አየዳበረ ሲሄድ የዚህ የዳበረ ሕይወት ማንፀባረቂያ የሆነው ቋንቋ መዝገበቃላትም እየሰፋ ይሄዳል፡፡ በአንፃሩ እድገት የማያሳይ ኅብረተሰብ ቋንቋ በመዝገበቃላቱም እድገት አያሳይም፡፡ እንዲያውም እየተዳከመና በሌላ አዳጊ ቋንቋ እየተዋጠ ሄዶ እስከመጥፋት ይደርሳል፡፡ በዚህ ሁኔታ የጠፉ የዓለም ቋንቋዎች ቀደም ሲል እንደተጠቆመው በርካታ ናቸው፡፡

## 4.6 ቋንቋ የመግባቢያ መሣሪያም የማንነት መለያም ነው

ቋንቋ መሣሪያ ነው፡፡ የሰው ልጅ በእለት ተዕለት ኑሮው የሚጠቀምባቸው ቁጥር ስፍር የሌላቸው መሣሪያዎችን ፈጥሯል፡፡ ለምሳሌ መጥረቢያና ሌሎች ስለት ያላቸው መሣሪያዎችን ለመቁረጫ፣ ገመዳገመድ የመሳሱትን ለማሰሪያ፣ ብስክሌትና መኪና የመሳሰሉትን ለመጓጓዣ፣ ሰዓትን ለጊዜ መለያ፣ ብዕርን ለመፃፊያ ይጠቀምባቸዋል ወዘተ. ቋንቋንም ለእርስ በርስ መግባቢያ ይገለገልበታል፡፡ ቋንቋ በተጨማሪ አንድ ሰው የማን ወገን መሆኑን የሚለይበት ምልክት ነው፡፡

የሰው ልጆች ታሪካዊ አመጣጣቸው ይለያያል፡፡ ይህ የተለያየ ታሪካዊ አመጣጥ ከሚለይባቸው ባህሪያት አንዱ ቋንቋ ነው፡፡ ስለዚህ ቋንቋ በአንድ በኩል የአንድ ሰው የማንነት መግለጫ ነው፡፡ ለምሳሌ አንድ ህፃን ማንነቱን የሚገልፀው፣ ለአካባቢው ትርጉም የሚሰጠውና ራሱን ከአካባቢው ጋር የሚያዛምደው በቋንቋው ነው፡፡ በዚህ ምክንያት ቋንቋ ከግለሰቡ ማንነት ጋር በጥልቀት የተያያዘ ነው፡፡ ይህም በመሆኑ አንድ ሰው ቋንቋው ሲከበር እሱነቱ የተከበረ፣ ቋንቋው ሲናቅ ደግሞ እሱነቱ የተናቀ፣ ያልተከበረ ይመስለዋል፡፡ ስለዚህ ነው ቋንቋና ከቋንቋ ጋር የተያያዙ ጉዳዮች በጥንቃቄ ሊያዙ ይገባል የሚባለው፡፡

## 4.7 የቋንቋ ፖሊሲ አስፈላጊነት

ቀደም ሲል እንደተገለፀው ቋንቋ በመሠረታዊ ባህሪዩ የመግባቢያ መሣሪያ ነው፡፡ የቋንቋ ፖሊሲ የዚህን የመግባቢያ መሣሪያ በንግግርም ሆነ በፅሑፍ መልኩ አጠቃቀሙንና የመግባቢያ መሳሪያነቱ የሚዳብርበትን ሁኔታ በማመልከት ሥርዓት የሚያስይዝ ሀገራዊ መመሪያ ነው፡ ከዚህ አኳያ አንድ ቋንቋ ብቻ በሚነገርበትም ሆነ ብዙ ቋንቋዎች በሚነገሩበት አገር የቋንቋ ፖሊሲ መኖር አስፈላጊ ነው፡፡ በተለይ ግን ከአንድ በላይ ቋንቋዎች በሚነገሩበት አገር የቋንቋ ፖሊሲ መኖር ወሳኝ ጉዳይ ይሆናል፡፡

አንድ ቋንቋ በሚነገርበት አገር በሚወጣው የቋንቋ ፖሊሲ ውስጥ የሚነሱና መመለስ ያለባቸው ጥያቄዎች አሉ፡፡ ከእነዚህም ዋናዎቹ:-

- ከሚነገሩት ቀበልኛዎች (የአነጋገር ዘየዎች) የትኛው እንደ መደበኛ ይወሰድ?

- *የቋንቋው የአፃፃፍ ሥርዓት ምን ይሁን?*
- *ቋንቋው በማስተማሪያነትም ሆነ በትምህርት መልክ እንዴት ሥራ ላይ ይዋል?*
- *በአስተዳደር፣ በንግድ እንቅስቃሴ፣ በትምህርትና በሌሎች አገራዊና ዓለም-አቀፋዊ እንቅስቃሴዎች በየትኛው (በየትኞቹ የውጭ ቋንቋ) ቋንቋዎች እንጠቀም?*
- *የአገር መሪዎች በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ አገር ከሌሎች መሪዎችና ሕዝቦች ጋር ኦፊሴላዊ ግንኙነት በሚያደርጉበት ጊዜ የቋንቋ አጠቃቀማቸው ሥርዓት ምን መሆን አለበት?*
- *ቋንቋውን ለማዳበርና የመገናኛና የሃሳብ መግለጫ መሣሪያነቱን ይበልጥ ለማዳበር ምን መደረግ አለበት የሚሉ ናቸው::*

*ከአንድ በላይ ቋንቋዎች በሚነገሩበት አገር የሚወጣ የቋንቋ ፖሊሲ ከላይ በተጠቀሱት የአንድ ቋንቋ ፖሊሲ ከሚያጠቃልላቸው ጉዳዮች በተጨማሪ በሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌዎች ላይ በመመሥረት የቋንቋዎች እኩልነትን ያረጋግጣል:: በመንግሥት አወቃቀር በየደረጃው የመንግሥት የሥራ ቋንቋ ምን እንደሚሆን እንዲሁም የትኛው ቋንቋ እስከስንተኛ ክፍል ድረስ በማስተማሪያነት እንደሚያገለግል፣ የትኞቹ ቋንቋዎች በትምህርት እስከ ስንተኛ ክፍል ድረስ እንደሚሰጡ፣ ይወስናል:: በተጨማሪ የትኞቹ ቋንቋዎች በመገናኛ ብዙሃን (በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በሕትመት) በጥቅም ላይ እንደሚውሉ ይደነግጋል::*

# 4.8 የቋንቋ ፖሊሲ ሲወጣ ግንዛቤ ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች

*የአንድ አገር የቋንቋ ፖሊሲ ሲወሰን በጥንቃቄ ሊጤኑ የሚገባቸው በርካታ ጉዳዮች አሉ:: ከእነዚህ ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው:: የቋንቋዎች ብዛት፣ የየአንዳንዱ ቋንቋ ተናጋሪዎች ብዛት፣ የእያንዳንዱ ቋንቋ የእድገት ደረጃ፣ የልሣነ-ክልሌነት ሁኔታ፣ አገራዊው ተጨባጭ ሁኔታ፣ ዓለም አቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታ፣ ለፖሊሲው ተገዢ የሚሆኑ ወገኖች የወደፊት እድል፣ የወላጆችና የተማሪዎች ፍላጎት፣ እንዲሁም የግለሰብ መብት ናቸው:: እነዚህን ጉዳዮች ከዚህ ቀጥሎ በአጭር በአጭሩ እንመልከታቸው::*

## 4.8.1 የቋንቋዎች ብዛት፣

*በአገሩ ውስጥ ስንት ቋንቋዎች በመነገር ላይ ናቸው? የሚለው ጉዳይ ወሳኝ ነው:: ቀደም ሲል እንደተነሳው ቋንቋ ይወለዳል፣ ያድጋል፣ ያረጃል፣ ይሞታል:: በአገሩ ውስጥ ከሚነገሩ ቋንቋዎች የትኞቹ በማደግ ላይ እንዳሉ የትኞቹ ደግሞ በተፈጥሮ ሂደት ምክንያት በመዳከምና በመሞት ላይ እንዳሉ ማወቁ ፖሊሲውን ከተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር የተገናዘበ እንዲሆን ለማድረግ ይረዳል::*

## 4.8.2 የቋንቋው ተናጋሪዎች ብዛት፣

*የቋንቋ ፖሊሲ ሲወጣ አንድ ቋንቋ ከብዙዎች ቋንቋዎች መሃል ተመርጦ የጋራ መግባቢያ፣ የመንግስት የሥራ ቋንቋ እንዲሁም የትምህርት መስጫ ቋንቋ እንዲሆን ከሚወሰንባቸው መስፈርቶች አንዱ የቋንቋው ተናጋሪዎች ብዛት ነው:: የተናጋሪዎች ብዛት ሲባል አንድን ቋንቋ በአፍ መፍቻ ቋንቋነትና በሁለተኛ ቋንቋነት የሚናገሩትን ደምሮ ማለት ነው::*

## 4.8.3 የቋንቋዎች የእድገት ደረጃ

*አንድ ቋንቋ ለጋራ መግባቢያነት፣ ለትምህርት መስጫነትና ለመንግሥት የሥራ ቋንቋነት ከሚመረጥባቸው መሥፈርቶች ሌላው የዕድገት ደረጃውና የመግባቢያ መሣሪያነቱ የተሟላ መሆን ነው:: የአንድ ቋንቋ የእድገት ደረጃ የመገናኛ መሣሪያነቱን ብቃት ይወስናል:: የዕድገት ደረጃ ሲባል ዋናው መለኪያ የመዝገበቃላቱ ሥፋትና በየእውቀት ዘርፉ ያለውን ቁሳዊና ፅንሰ-ሃሳባዊ ገጽታ የመግለጽ ብቃት ነው:: ሌሎች መስፈርቶች የአፃፃፍና የአነባበብ ሥልቱ የተሟላ መሆን፣ በቋንቋው የሚወጡ የሥነ-ቃል፣ የሥነ-ጽሑፍ፣ የሥነ-ጥበብ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂና የሌሎች የእውቀት ዘርፎች ሕትመቶች ብዛትና የይዘታቸው ሥፋትና ጥልቀት ነው::*

## 4.8.4 የልሣነ-ክልኤነት ሁኔታ

ልሣነ-ክልኤነት አንድ ሰው ወይም የአንድ ቋንቋ ተናጋሪ ኅብረተሰብ ከራሱ ቋንቋ በተጨማሪ ሌላ ቋንቋ አጥርቶ የመናገር ችሎታ ያዳበረበት ሁኔታ ነው ተብሏል፡፡ በርካታ ቋንቋዎች በሚነገሩበት አገር ውስጥ የልሣነክልኤነት ሁኔታን ማወቅ በቋንቋ አወጣጥ ጊዜ የትኛው ቋንቋ ወይም የትኞቹ ጥቂት ቋንቋዎች ለሕዝብ በጋራ መግባቢያት ሊያገለግሉ እንደሚችሉ ወይም ለመንግሥት የሥራ ቋንቋም ሆነ ለትምህርት መስጫ እንደሚውሉ ለመወሰን ይረዳል፡፡ ልሣነ-ክልኤነት ባለበት አካባቢ አንድን ተግባር ለማከናወን በሁለት ወይም ከዚያ በላይ ቋንቋ ከመጠቀም በአንድ ቋንቋ ብቻ በመጠቀም የአገር ሀብት መቆጠብ ይቻላል፡፡

አንዳንድ ጊዜ ጉልህ የሆነ ልሣነ-ክልኤነት ባለበት ሁኔታ በሁለት ወይም በሦስት ቋንቋዎች የመጠቀም ሁኔታ ሊኖር ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአገራችን በተለይ በአዲስ አበባና በሌሎች ትላልቅ ከተሞች ግልፅ የሆነ ልሣነ-ክልኤነት አለ፡፡ አዲስ አበባን እንውሰድ፡፡ ነዋሪው ሕዝብ ከሞላ ጎደል ከራሱ አፍ መፍቻ ቋንቋ ሌላ አማርኛ አሳምሮ ይናገራል፡፡ ሆኖም አንድ ዓይነት ዜና በሬዲዮም ሆነ በቴሌቪዥን በሦስት ብሔራዊ ቋንቋዎች ማለትም በአማርኛ፣ በኦሮሚኛና በትግሪኛ ይነገራል፡፡

ዜናም ሆነ ሌሎች የተለያዩ ፕሮግራሞች በአማርኛ በኦሮሚኛና በትግሪኛ እንዲነገሩ የሚደረገው ኦሮሚኛና ትግሪኛ ተናጋሪዎች የሆኑ የአዲስ አበባም ሆነ የሌሎች ከተሞች ነዋሪዎች አማርኛ አይሰሙም ከሚል እምነት በመነሳት አይደለም፡፡ ይህ ከሆነ ታዲያ አንድ ዓይነት ፕሮግራም ከአማርኛ በተጨማሪ በሁለቱ ቋንቋዎች በተደጋጋሚ በማስነገሩ ገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት እንዲባክን የሚደረገው ለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ ሊነሳ ይችላል፡፡

በአንድ አገር ውስጥ የቋንቋ ፖሊሲ ሲወጣ የሚጤኑና ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጣቸው ገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት ላይሆኑ ይችላሉ፡፡ ቅድሚያ የሚሰጠው በቋንቋዎቹ መጠቀም የሚያስገኘው ፖለቲካዊና ሥነ ልቡናዊ ጠቀሜታ ሊሆን ይችላል፡፡ ለምሳሌ በአገራችን የቋንቋ አጠቃቀምን በተመለከተ የምናየው ይህን ሁኔታ ነው፡፡ ከገንዘብ፣ ጊዜና ጉልበት ቁጠባ ይልቅ በወቅቱ የታሪክ ተጨባጭ ሁኔታ ምክንያት ቅድሚያ የተሰጠው ለፖለቲካዊና ሥነልቡናዊ ጠቀሜታ ነው፡፡ በፖለቲካ ሥርዓቱ ምርጫ የተሰጠ የፖለቲካ ውሳኔ ነው፡፡ ምርጫው ትክክል ነው ወይስ አይደለም? ብልህነትን ያሳያል ወይስ አያሳይም? ለሚሉት ጥያቄዎች የሚሰጠው አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ መልስ አከራካሪ ነው፡፡ ወሳኙ ግን የፖለቲካ ሥልጣን ያለው አካል ነው፡፡

## 4.8.5 አገራዊ ሁኔታ

ኢትዮጵያ የዘመናዊው ዓለም አካል እንደመሆንዋ መጠን በውስጣዊ ሕይወትዋ ለዘመናዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሕግጋት ተገዥ እየሆነች በመምጣት ላይ ነች፡፡ ሕገመንግሥቱ ከአቀራረጽ፣ ከይዘትና ከአፀዳደቅ ሂደት አኳያ መሠረታዊ ድክመቶች ቢኖሩትም ለመነሻ የዘመናዊነትን አቅጣጫ የያዘ ሠነድ አለን ማለት ይቻላል፡፡ በሕገ መንግሥቱ መሠረትም በሀገሪቱ ውስጥ በርካታ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች በመካሄድ ላይ ናቸው፡፡

ከፍተኛ የሕዝብ እንቅስቃሴ አለ፡፡ በአንድ አካባቢ የተወለደ ሕፃን ሲያድግ ዕድሉ ወዴት እንደሚያመራው አይታወቅም፡፡ ከአካባቢው ወጥቶ በክልሉም ሆነ ከክልሉ ውጭ በመንግስት ቢሮክራሲ፣ በንግድ ሥራ፣ በግል ድርጅት ተቀጣሪነት፣ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት፣ በውትድርና፣ በየደረጃው በመምህርነት፣ በፖለቲካ ሥራ ወዘተ. ሊሠማራ ይችላል፡፡ ይህ በሚሆንበት ጊዜ ከሌላ ቋንቋ ተናጋሪዎች ጋር መገናኘት፣ አብሮ መሥራት፣ አብሮ መኖር፣ አብሮ መማር፣ ትዳር መመሥረት፣ ለሥራ ወይም ለትምህርት ዕድል ወይም ለደረጃ ዕድገት በጋራ መግባቢያ ቋንቋ መወዳደር ይመጣል፡፡ በዚሁ ቋንቋ በትምህርት ገበታ፣ በስብሰባዎችና ታላላቅ ጉባኤዎች በቃልም ሆነ በጽሑፍ ሃሳብን መግለጽ፣ መከራከር፣ ጥናትና ምርምር ማካሄድ፣ ሪፖርት መፃፍ ይከተላል፡፡ የከፍተኛ ዕውቀት፣ የከፍተኛ ሃብት ባለቤት መሆን፣ ሕዝብን መምራት፣ ከፍተኛ ኃላፊነትን መሸከም ይኖራል፡፡ በእነዚህና በመሳሰሉ ሌሎች ሂደቶች ቋንቋ ወሳኝ ሚና ይጫወታል፡፡ አንደበተ ርቱዕ ተናጋሪ፣ ሕዝብ በሚገባው ቋንቋ ተናግሮ ወይም ጽፎ አሳማኝ የመሆን ችሎታ ክቡር መሣሪያ ነው፡፡ የቋንቋ ፖሊሲው ለዜጎቹ ይህን ችሎታ፣ ይህን መሣሪያ የሚያስታጥቅ መሆን አለበት፡፡

አንድ ዜጋ በቋንቋው፣ በብሔራዊ ማንነቱ ሊኮራ ይገባዋል:: ይህ ማለት ግን ጎሳዊ ጥብቆ አጥልቆ፣ በጎሳዊ ቀፎ ውስጥ ተወስኖ ጠባብ ጎሳዊ ስሜቶችን የሚኮተኩትና የሚያስታምም መሆን አለበት ማለት አይደለም:: የብሔረሰባዊ ማንነት ስሜት መነሻ መሠረት እንጂ በውስጡ ተውጠን የምንቀርበት እስር ቤት አይደለም:: በቅድሚያ እኛ በዚች ፕላኔት ላይ የተፈጠረው የሰው ዘር አባል መሆናችንን አርቀን ማየት አለብን:: ከዚያ በመቀጠል በመልክዓምደር ተወስነን የራሱ ባህሪ ባለው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሥርዓት ተኮትኩተን ያደግንና የጋራ ታሪክ ያለን ኢትዮጵያውያን ነን:: ከዚያ ቀጥሎ ወደዝርዝር ሲኬድ ጎሣዊ ማንነት ይመጣል:: ከዚያም ተወርዶ፣ ቀበሌአዊና መንደራዊ ማንነት ይመጣል:: የዜጎች የእንቅስቃሴ አቅጣጫ ከጠባቡ ወደሰፊው እንጂ ከሰፊው ወደጠባቡ መሆን የለበትም:: ማንኛውም ኢትዮጵያዊ መነሻው ብሔረሰባዊ አካባቢ ሆኖ በማንኛውም የኢትዮጵያ ክፍል ሥሩን ሰዶ፣ በማንኛውም የሥራ መስክ ተሰማርቶ ብቁ ተወዳዳሪ ሆኖ አብቦና አፍርቶ መኖር መቻል አለበት:: የቋንቋ ፖሊሲው ለዚህ ሂደት መሳካት አመቺ አሁኔታ በመፍጠር ጉልህ አስተዋፅኦ ማድረግ አለበት::

## 4.8.6 ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ

የኢትዮጵያ የቋንቋም ሆነ አጠቃላይ የትምህርት ፖሊሲ ዓለም አቀፍ ሁኔታን ያገናዘበ መሆን አለበት:: ቀደም ሲል እንደተገለጸው በሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ምክንያት ዓለም እየጠበበች በመምጣቷ፣ የዓለም ሕዝቦችም የዚያኑ ያህል እየተቀራረቡ መጥተዋል:: በመቀራረባቸው ምክንያትም ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ሕይወታቸውም የዚያኑ ያህል እየተቀራረበና እየተወሳሰበ መጥቷል:: በአንድ ሕዝብ ላይ የሚደርስ በጎም ሆነ ጎጂ ክስተት በሌላው የዓለም ሕዝብ ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ተጽእኖ ያሳድራል:: እያንዳንዱ አገር፣ እያንዳንዱ ሕዝብ በዚህ ዓይነት ዓለም አቀፋዊ ድባብ ሥር የሚገኝ በመሆኑ ተነጥሎና በብሔራዊ ወይም ብሔረሰባዊ ቀፎ ውስጥ ተወስኖ መኖር አይችልም::

በአሁኑ ጊዜ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በዓለም ዙሪያ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ በጥናትና ምርምር ማዕከሎች፣ በንግድ ድርጅቶችና በሌሎችም መስኮች ተሰማርተው ይገኛሉ:: በየትኛውም ክፍለ ዓለም ሠርቶ ማደርና ኑሮአቸውን መምራት የቻሉት አብረው ከሚሠሩትና ከሚኖሩት ሕዝብ ጋር በቋንቋ መግባባት በመቻላቸው ነው:: ለወደፊትም ቢሆን ከሃገራቸው አልፈው በዓለም ዙሪያ የሚሠማሩ ኢትዮጵያውያን ቁጥር እያደገ ነው የሚሄደው:: ስለዚህ የሃገራችን የቋንቋም ሆነ አጠቃላይ የትምህርት ፖሊሲ ኢትዮጵያውያንን ከሃገራቸውም አልፈው የዓለም ዜጎች እንዲሆኑ፣ በሃገራቸው በየትኛውም ክፍል ሆነ በየትኛውም ዓለም በየትኛውም መስክ ጠንካራ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ የሚያስችል መሆን አለበት:: አድማሳቸውን የሚያሰፋ እንጂ የሚያጠብ መሆን የለበትም::

እስከ አሁን ድረስ በተነሱ ቋንቋ ነክ መሠረተ-ሃሳቦች ላይ በመመሥረት ኢዴፓ በሀገራችን የሚኖረው የቋንቋ ፖሊሲ የሚከተለው አይነት አቅጣጫ እንዲከተል ይፈልጋል::

# 4.9 የቋንቋ ፖሊሲ አጠቃላይ አቅጣጫ

ኢዴፓ ከሚከተለው አጠቃላይ መርህ አንፃር ማንኛውም ዜጋ በተናጠልም ሆነ በጋራ ቋንቋውን የመጠቀምና የማሳደግ መብቱ ሊጠበቅለት ይገባል ብሎ ያምናል:: ማንኛውም ዜጋ በአፍ መፍቻ ቋንቋ ለመማርና በቋንቋው ለመጠቀም ያለውን መብት ከማክበርም በላይ መንግስት ዜጎች በቋንቋ ረገድ ያላቸው መብት እንዲከበር ለማድረግ ሁኔታዎችን የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት ብሎ ያምናል:: በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያ ህዝብ አንድነቱን ጠብቆ ለመኖር፣ በትምህርት፣ በንግድ፣ በቴክኖሎጂና በመሳሰሉት ጉዳዮች የጋራ መግባባት በመፍጠር አስተዳደራዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገቱን ለማፋጠን የሚያስችለው የጋራ የስራ ቋንቋ ያስፈልገዋል:: አሁን ባለንበት የኢኮኖሚ የአቅም ደረጃ ከአንድ የስራ ቋንቋ በላይ ለመጠቀም ያለን አድል ጥያቄ ወስጥ የሚገባ ቢሆንም ኢትዮጵያውያን በጋራ የስራ ቋንቋነት የሚያስፈልገን የግድ አንድ ቋንቋ ብቻ ነው የሚል እምነት ግን ኢዴፓ የለውም:: ኢኮኖሚያዊ አቅማችን ወደፊት ሲፈቅድ በሌሎች ሀገሮች ጥቅም ላይ እንደዋለው ሁሉ በኛም አገር ከአንድ በላይ የሆኑ ቋንቋዎችን በስራ ቋንቋነት ለመጠቀም የሚኖረን እድል ክፍት መሆን አለበት::

*ይህንን መሰረታዊ አስተሳሰብ መሰረት በማድረግ የፌዴራሉ መንግስት መስሪያ የሚሆነውንና የፌዴራል መንግስቱ ከክልል መንግስታት ጋር የሚናገርበትን ቋንቋ የባለሞያዎችን ጥናትና የህዝቡን ቀጥተኛ ተሳትፎ መሰረት ባደረገ ሁኔታ መርጦ በስራ ላይ ማዋል ያስፈልጋል። የጋራ የስራ ቋንቋ መኖር ማለት ግን እያንዳንዱ ዜጋ ያንን ቋንቋ እንዲናገርና እንዲጠቀም ግዴታ ይጣልበታል ማለት አይደለም። ግዴታ መጣል የመብቶች ሁሉ መሰረት የሆነውን የግለሰብ መብት የሚፃረር በመሆኑ ተቀባይነት አይኖረውም። ስለዚህ የፌዴራሉን የስራ ቋንቋ መናገር የማይችሉ ሰዎች ጉዳይ በሚያስፈፅሙበት አካባቢ በቂ የሆነ የትርጉም አገልግሎት የሚያገኙበትን አሰራር መከተል ያስፈልጋል። በፌዴራሉ መንግስት የስራ ቋንቋ የሚሰጡ ሰነዶችንም እንደአስፈላጊነቱ ወደ ሌሎች የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እየተረጎሙ ማቅረብ ይገባል።*

*ከፌዴራል የስራ ቋንቋ በተጨማሪ የአካባቢ መንግስታትም የራሳቸውን የስራ ቋንቋ የባለሞያን ጥናትና የህዝብ ተሳትፎን መሰረት ባደረገ አሰራር እያስመረጡ በስራ ላይ ማዋል ይኖርባቸዋል። ነገር ግን አንዱ የአካባቢ መንግስት ከሌላው የአካባቢ መንግስት ጋር የሚያደርገው ግንኙነት በፌዴራሉ የስራ ቋንቋ ሊሆን ይገባዋል። በእያንዳንዱ የአካባቢ መንግስት ክልል ውስጥ ኗሪ የሆኑ ዜጎችም የአካባቢ መንግስቱን የስራ ቋንቋ መናገር የማይችሉ ከሆነ አስፈላጊው የትርጉም አገልግሎት በመንግስት በኩል እንዲመቻች ማድረግ ያስፈልጋል።*

*ከአስተዳዳራዊ ጉዳዮች በተጨማሪ ሌላው በቀዳሚነት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው በትምህርት ቤቶች የሚኖረው የቋንቋ አጠቃቀም ጉዳይ ነው። በመዋዕለ ሕፃናት ደረጃ የሚገኙ ህፃናት በሚኖሩበት የቅርብ አካባቢ የህብረተሰቡና የራሳቸው የአፍ መፍቻ የሆነው ቋንቋ ጥቅም ላይ እንዲውል ማድረግ ያስፈልጋል። መሰረተ ትምህርትና ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል የሚሰጠው መደበኛ ትምህርት የክልሉ መንግስት በሚመርጠው ቋንቋ እንዲሰጥ ተደርጎ የክልሉን ቋንቋ መናገር ለማይችሉ ተማሪዎች ግን በፌዴራሉ የስራ ቋንቋ የሚማሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል። በተመሳሳይ ሁኔታ ተማሪዎች ከአንደኛ ክፍል ጀምሮ የፌዴራልን የስራ ቋንቋና እንግሊዝኛን እንደአንድ መደበኛ ትምህርት እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ እንዲማሩዋቸው ማድረግና ከሰባተኛ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ድረስ ኮሌጆችና ዩንቨርስቲዎችን ጨምሮ አጠቃላዩ መደበኛ ትምህርት በእንግሊዘኛ ቋንቋ እንዲሰጥ ቢደረግ ለትምህርቱ ጥራትም ሆነ ለአጠቃላዩ የሀገሪቱ እድገት የተሻለ መፍትሄ ይሆናል ብሎ ኢዴፓ ያምናል። ቋንቋን በተመለከተ በትምህርት ቤቶች የሚዘረጋው አማራጭ በሁሉም የአገሪቱ አካባቢም ወጥ እንዲሆን ማድረግ ተገቢ ይሆናል። የኮሚኒቲ ትምህርት ቤቶች እራሳቸው በመረጡት ቋንቋ ትምህርት እንዲሰጡ መፍቀድ አስፈላጊ ቢሆንም እንግሊዘኛና የፌዴራሉን የስራ ቋንቋ ግን በቋንቋነት እንዲያስተምሩ ማድረግ ተገቢ ነው።*

*የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀምን በተመለከተ በፌዴራል ደረጃ የሚዘጋጁ ጋዜጦችና መፅሄቶች፣ የሚሰራጩ የቴሌቪዥንና የሬዲዮ ስርጭቶች በፌዴራሉ የስራ ቋንቋ እንዲሆኑ ማድረግ፣ በክልል መንግስታት ደረጃ የሚዘጋጁና የሚሰራጩትን ደግሞ የክልል መንግስታቱ በሚወስናቸው የክልል የስራ ቋንቋዎች ማድረግ ተገቢ ነው። ሥነ ጽሁፍ፣ ሙዚቃ፣ ትያትርና ፊልምንም በተመለከተ በማንኛውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እየተዘጋጁ የሚሰራጩበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ይሆናል። በተለይም በፌዴራል ደረጃ የሚወጡ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጠቀሜታ ያላቸው ህትመቶች በፍጥነት እየተረጎሙ የማሰራጨትን ሰራ ማጠናከር እንደ ኢትዮጵያ ለብዙ ቋንቋዎች የሚነገርበት አገር በጣም ጠቃሚ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ የኢትዮጵያን ብሔር ብሔረሰቦች ባህል፣ ታሪክና ቋንቋ በተመለከተ የተደረጉ ምርምሮችንና የታተሙ ህትመቶችን፣ ከውጭ ሀገር የሚገኙ የተለያዩ ጠቃሚ መረጃዎችን ህዝቡ እንዲገለገልባቸው ላደርግ መንግስት ለትርጉም ስራና ለስርጭት ልዩ ትኩረት መስጠት ይገባዋል። በስራ ጠባያቸው ምክንያት ከውጭ መንግስታት፣ ዓለም አቀፍ ተቋማት፣ የንግድ ድርጅቶችና ሌሎች አባላት ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ የመንግስት አካላትና ሌሎች ድርጅቶች ለስራቸው መቃናት አግባብ ባለው ቋንቋ እንዲጠቀሙ ማድረግም አስፈላጊ ነው። በመገናኛ ብዙሃንም ልዩ ልዩ የውጭ ቋንቋዎች አስፈላጊነታቸው እየተመዘነ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በህትመት አገር ውስጥ የሚራጩበት ሁኔታ ቢመቻች ጠቃሚ ነው።*

እነዚህ ቋንቋን በተመለከተ የጠቀስናቸውን ጠቃሚ ሀሳቦች በብቃት ተግባራዊ ለማድረግም የኢትዮጵያ ህዝብ የተለያዩ ቋንቋዎች ባለቤት መሆኑ እንደጥሩ ፀጋ ሊቆጠር የሚችል እንጂ እንደመጥፎ አጋጣሚ ተቆጥሮ ህዝብን በመለያየ መሳሪያነት ጥቅም ላይ እንዳይውል የሚያስችል ስልት መከተል እንደሚያስፈልግ ኢ.ዴ.ፓ በፅኑ ያምናል፡፡

# 5. <u>ባህል</u>

ኢትዮጵያ በተለያዩ ባህሎች ያሸበረቀች ሀገር ናት፡፡ የኢትዮጵያ ውበትና ድምቀት በሚገባ ከሚንፀባረቁባቸው ሁኔታዎች መካከል የተለያዩ ባህሎች ባለቤት መሆኗ አንዱና ዋነኛው ነው፡፡ በሀገሪቱ የዴሞክራሲ ስርዓት ባለመኖሩና ሁሉም ባህሎች በእኩል ደረጃ እንዲያድጉና እንዲስፋፉ ባለመደረጋቸው የባህል የእድገት ደረጃ ልዩነቶች ጎልተው መታየታቸው እውነት ነው፡፡ በሀገሪቱ ውስጥ ከሚገኙት ባህሎች መካከል የተወሰኑት የተሻለ እድገት ሲያገኙ ሌሎቹ ደግሞ ጨርሶ የተረሱ ናቸው፡፡ ከ1966ቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በኋላ ለባህሎች እኩልነት መፈጠር የሚረዱ አስተያየቶችና ክርክሮች ወደ አደባባይ መውጣት ቢጀምሩም ጥልቀት ባለው ደረጃ የተከናወኑ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎች የሉም፡፡

እስካሁን ድረስ የባህል እኩልነት መረጋገጥ አለበት የሚል መፈክር ከማሰማትና ፕሮፓጋንዳ ከመንዛት በስተቀር ለባህሎች እኩልነትና እድገት መረጋገጥ የሚረዳ የተጨበጠ ተግባር የለም፡፡ ቀደም ሲል እንደተገለጸው ከ1966ቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በኋላ በተለያዩ ቋንቋዎች የመሰረተ ትምህርትና መደበኛ ትምህርት፣ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ስርጭትና የመሳሰሉት ጅምሮች እየታዩ ቢመጡም የሁሉንም ባህሎች እኩልነትና እድገት ለማረጋገጥ በሚያስችል መሰረት ላይ የቆሙ ባለመሆናቸው ከፕሮፓጋንዳ ያለፈ ፋይዳ አስገኝተዋል ለማለት አይቻልም፡፡

ለባህሎች እኩልነትና እድገት የመጀመሪያው እርምጃ መሆን ያለበት ለባህል ነጻነት፣ እኩልነትና እድገት መረጋገጥ የሚበጅ ፌዴራላዊ አደረጃጀት መመስረት ነው፡፡ ከዚያ ቀጥሎ ባህሎች በሚገባ እንዲጠኑና እንዲታወቁ የሚያስችል ስራ መምጣት አለበት፡፡ በየቦታው የባህል ማዕከላት እንዲፈጠሩና ተግባራዊ እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

በአሁኑ ወቅት እያንዳንዱ ባህል የራሱ ነጻነትና እኩልነት እንዲረጋገጥለት ሳይሆን የራሱን እየተወ ሳይወድ በግድ አንድ ወጥ የክልል ባህል እንዲቀበል እየተደረገ ነው፡፡ አሁን የተዘረጋው የቋንቋ ፌዴራሊዝም ትልቁ ችግርም ይኸው ነው፡፡ በአማራ ክልል አንድ የክልል ባህል፣ በኦሮሚያ፣ በአፋር፣ በሶማሊያ፣ በሀረሪ ወዘተ. እንደዚሁ ዓይነት አሰራር እንዲሰፍን እየተደረገ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደረገው ትልቁ ችግር የሀገሪቱ ፌዴራላዊ አደረጃጀት በቋንቋ ላይ የተመሰረተ መሆኑ ነው፡፡ በዚህም የተነሳ አንደኛው ቋንቋ ለክልሉ እንደዋና ባለቤት ብቻ ሳይሆን እንደብቸኛ ወሳኝ ኃይል በመቆጠሩ ከክልሉ ስያሜ ጀምሮ ሁሉንም መብቶች በብቸኝነት ለመያዝ ስለቻለ በእርሱ ስር የተጠቃለሉትን ሌሎች ቋንቋዎች በእኩል ደረጃ አይመለከታቸውም፡፡ ባህላቸውን ለማሳደግና ለማስፋፋትም እኩል እድል የላቸውም፡፡ የሚደረግ ድጋፍ ካለ የክልሉ ዋና ባለቤት ተደርጎ የተሰየመው ባህል የራሱን የአንበሳ ድርሻ አንስቶ የሚቀር ትርፍራፊ ካለ ብቻ ነው ለሌሎቹ ትኩረት ለመስጠት የሚሞክረው፡፡ የአሁኑ የቋንቋ ፌዴራላዊ አደረጃጀት በቋንቋና ባህል እኩልነት ስም ከፍተኛ የቋንቋና የባህል አድሎ የሚፈፀምበት አደረጃጀት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ አደረጃጀት በቋንቋ መሰረት ላይ ብቻ እንዲቆም እስከተደረገ ድረስ የባህል ነጻነት፣ እኩልነትና እድገት ይመጣል ተብሎ አይጠበቅም፡፡ አንዱ የራሱን ባህል በሌላው ላይ ለመጫን በሚፈጽመው አድሎ መገለልና ተፅዕኖ የሚደርስባቸው ሌሎች ባህሎች መብታቸው እንዲጠበቅና በእኩል ደረጃ እንዲታዩ ከመታገል ወደኋላ አይሉም፡፡ በዚህ መንገድ እየተንተቱ የባህል እኩልነትን ማረጋገጥ የማይታሰብ ነው፡፡ ስለዚህ የፌዴራሉን አደረጃጀ በቋንቋ መሰረት ላይ ብቻ እንዲቆም ከተደረገበት የተሳሳተ አቅጣጫ በማውጣት የሁሉንም ባህሎች እኩልነትና ነጻነት ሊያረጋግጥ በሚችል ሰፊ መሰረት ላይ እንዲቆም ማድረግ ቀዳሚው እርምጃ መሆን አለበት፡፡ የባህል ነጻነትና እኩልነት ቋንቋን በማሳደግ ብቻ የሚረጋገጥ ተደርጎ መታየትም የለበትም፡፡ ቋንቋን መጠቀምና ማሳደግ አንዱ የባህል ነጻነትና እኩልነት ማረጋገጫ መንገድ ቢሆንም ብቻውን የተሟላ መብት መገለጫ ሊሆን አይችልም፡፡

*የተለያዩ ባህሎች ነጻነታቸውና እኩልነታቸው በተሟላ መንገድ እንዲረጋገጥ በቋንቋቸው ከመጠቀም በተጨማሪ ራሳቸውን የማስተዳደር መብት በማረጋገጥ፣ ከሀገሪቱ ሀብትና ጥሪት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ እንዲጋሩ በማድረግ፣ የልማት እድሎችን የማግኘት እኩል መብት እንዲኖቸው በማድረግ፣ ለቀልጣፋ አስተዳደራዊ አገልግሎትና ለፈጣን ኢኮኖሚያዊ እድገት የሚረዱ የመሰረተ ልማት ፋሲሊቲዎችን በማግኘት እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በማስቻልና በመሳሰሉት ጭምር ተጨባጭ እርምጃዎች መውሰድ አለባቸው:: ይኸንን ተግባራዊ ለማድረግ አንድን ቋንቋ የአንድ ክልል ዋነኛ ባለቤት፣ አድራጊና ፈጣሪ በሚያደርግ፣ ሌሎቹን ደግሞ ዋጋቢስና የበታች ተደርገው እንዲታዩ በሚያቅድ የቋንቋ መሰረት ላይ የተገነባውን አደረጃጀት መቀየር ያስፈልጋል:: ሁሉንም በእኩልነት፣ በጋራ ጥቅምና አንድነት ሊያሰባስብ በሚያስችል ሰፊ መሰረት ላይ የተገነባ ፌዴራላዊ አደረጃጀት በመከተል የሀገሪቱን ልዩ ልዩ ባህሎች ነጻነትና እኩልነት በተጨባጭ ማረጋገጥ ይገባል:: እንዲህ ዓይነቱን ፍትሃዊ አቅጣጫ በመከተል ሁሉም ባህሎች እንዲያድጉና እንዲስፋፉ ማድረግ ይችላል:: ሰፊ በሆነ መሰረት ላይ የተገነባ ፌዴራላዊ ስርዓት በሀገሪቱ በሚኖርበት ጊዜ የተለያዩ ባህሎች ካለ አድሎ በነጻነትና በእኩልነት የሚያድጉበት ዘላቂ ሁኔታ ይፈጠራል::*

*አብዛኛዎቹ የባህል ግንባታና አገልገሎቶች መካሄድና መስፋፋት የሚገባቸው በአካባቢ የመንግስት አካላት አማካይነት ነው:: ምክንያቱም ለእያንዳንዱ ባህሎች የሚቀርቡት የመንግስት አካላት እነርሱ ስለሆኑ ነው:: በጠቅላላው በሀገሪቱ ውስጥ የሁሉም ባህሎች ነጻነትና እኩልነት ተጠብቆ እንዲያድግ የሚያስችል ሕግ የማውጣት ኃላፊነት ደግሞ የፌዴራል መንግስት መሆን አለበት:: አንዳንድ የተለዩ ሁኔታዎች በክልል መንግስታት ሕግ ውስጥ ሊወጡና የፌዴራሉን ሕገመንግስት በማይቃረን ሁኔታ ተግባራዊ ሊሆኑ ይችላሉ:: በተለያዩ የከተማና የገጠር አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች ባህላቸውን የሚያንፀባርቁ ሙዚቃዎችን፣ ቲያትሮችን፣ ሙዚየሞችን፣ ቤተመፃህፍቶችን ሊያስፋፉና የራሳቸውን የባህል ማዕከላት ሊፈጥሩ ይችላሉ:: የፌዴራል መንግስት ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ ልዩ ልዩ ባህሎች በተናጠልና በጋራ ያፈሯቸውን ባህላዊ እሴቶች ሊያንጸባርቁ የሚችሉ የባህል ማዕከላትን በሀገር ደረጃ ማቋቋም ይገባዋል:: ከዚህ ሌላ የተለያዩ ባህሎች በነጻነትና በእኩልነት የሚያድጉበትን የሕግ፣ የቴክኒክ፣ የፋይናንስና የምክር ድጋፍ መስጠት ይገባዋል:: በሥርዓተ ትምህርቱ ውስጥ የሁሉንም ባህሎች ደረጃ ተመጣጣኝነት የሚጠብቁ ፖሊሲዎችና አሰራሮች እንዲኖሩ በማድረግ ከአንዱ ባህል ወደሌላው ባህል የሚደባለቁ ዜጎች የትምህርት ጥራት ችግር እንዳያጋጥማቸው መከላከል አለበት:: የፌዴራልና የክልል መንግስታት በባህል ማዕከላት ግንባታ፣ በትምህርት እቅድ ዝግጅትና በባህል ማስፋፋት ስራ የሚተባበሩበት ስርዓት መኖር አለበት:: ለትምህርትና ባህል መስፋፋት የሚበጅ እቅድና ምርምር የሚያደርግ የጋራ ኮሚሽን መስርተው መስራት ይገባቸዋል::*

# 6. ኃይማኖትና የኃይማኖት ተቋሞች

*የኃይማኖትና የሕሊና ነጻነቶች የማይጣሱ የሰው ልጅ መሰረታዊ መብቶች ናቸው:: በማንኛውም ወገን ጣልቃ ገብነትና ተፅዕኖ የማይደረግባቸው የግለሰብ መብቶች ናቸው:: በኢትዮጵያ ውስጥ ተቀራራቢ የሆነ አማኝ ያላቸው የኦርቶዶክስ ክርስትናና የእስልምና ኃይማኖቶች ናቸው:: እነዚህ ሁለቱ ኃይማኖቶች ወደ ኢትዮጵያ የገቡበት ዘመን ረጅም ከመሆኑም በላይ ተቻችለው አብረው በመኖራቸውና በክፉም ሆነ በመልካም ጊዜ ሳይለያዩ በትብብር መርህ በመቆማቸው በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ጉልህ ስፍራ ያላቸው ናቸው:: የልዩነት መኖር ብቻውን ትብብርና ዝምድና እንዳይፈጠር ምክንያት ሊሆን እንደማይችልና ከልዩነት ጋር በአንድነት መኖር እንደሚቻል ከፍተኛ ትምህርት የሰጡ ተቋሞች ናቸው:: እንደውም ሕዝቡን እርስ በርስ ከማስተሳሰር አልፈው ሕዝብና መንግስትንም በማስተሳሰር ረገድ የተጫወቱት ሚና በሀገሪቱ ታሪክ ውስጥ ትልቅ ግምት የሚሰጠው ነው:: ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ደግሞ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንትና የሌሎችም ኃይማኖቶች በሀገሪቱ ውስጥ በርካታ ተከታዮችን እያፈሩና እየተጠናከሩ መጥተዋል::*

*ሁሉም ኃይማኖቶች ለተከታዮቻቸው ከሚያስተምሩት የኃይማኖትና የሞራል እሴት በተጨማሪ በበጎ አድራጎትና በልማት ተግባር እየተሳተፉ ጠቃሚ አስተዋፅኦ በማድረግ ላይ ናቸው:: እነዚህ የኃይማኖት ተቋሞች በአንድ በኩል ከመንግስት የተለዩ ሲሆኑ በሌላ በኩል የግለሰቦች ማህበራት ተደርገው የሚታዩም አይደሉም:: የኃይማኖት ተቋሞች ነጻ ሆነው የቆሙና እንደ መንግስት አጋር ሆነው የሚታዩ ልዩና ከማንም ጣልቃ ገብነት የተጠበቀ ደረጃ ያላቸው የሕዝብ ተቋሞች ናቸው:: ከመንግስት ጋር የሚኖሯቸው ግንኙነት በትብብርና በስምምነት መርህ ላይ የተመሰረተ ብቻ*

ነው። የራሳቸውን የአደረጃጀትና የአሰራር አማራጭ በራሳቸው እየወሰኑ የሚንቀሳቀሱ ተቋሞች ናቸው። እነዚህ ተቋሞች በበጎ አድራጎትና በልማት ስራ እየተሳተፉ ለሕዝቡ ጠቃሚ ነገር በመስራት የመንግስትን የልማት ጥረት እንደሚያግዙ ሁሉ መንግስትም ከኃይማኖት ተቋሞቹ የትብብር ጥያቄ ሲቀርብለት የሚችለውን ሁሉ በማድረግ የበኩሉን እገዛ ማደረግ ይኖረበታል። ከመንግስት የሚሰጥ እገዛ በተቋሞቹ ነጻነት ላይ ተፅዕኖ የሚያሳድር እንዳይሆን ብርቱ ጥንቃቄ ማድረግ የተገባ ነው።

የኃይማኖት ተቋሞች የንብረት ባለቤትነት መብታቸው ሊጠበቅ ይገባል። ለአገልጋዮቻቸው የሚፈፅሙት የደመወዝና የአበል ክፍያ ስላለባቸው፣ የኃይማኖት አገልግሎታቸውን ለማስፋፋት የሚያካሂዱት የመሰረተ ልማትና የፋሲሊቲ ግንባታ ስለሚኖር ከአማኞችና ደጋፊዎች በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ መዋጮና እርዳታ የመሰብሰብ መብት አላቸው። ለኃይማኖት አገልግሎት፣ ለበጎ አድራጎትና ለልማት ስራ የሚውል ቋሚ ገቢ እንዲኖራቸው የገቢ ማስገኛ ተቋሞችን በባለቤትነት ማቋቋምና ማስተዳደር ይችላሉ። ከሀገርና ከውጭ በጎ አድራጊዎች እርዳታ ሊያሰባስቡ ይችላሉ። የአቅም ችግር ሲያጋጥማቸው ከመንግስትም ድጋፍ ሊጠይቁና ሊያገኙ ይችላሉ። የኃይማኖት መሪዎቻቸውን የመሰየምና አገልጋዮቻቸውን የመመደብ፣ የተቋሞቹን ንብረትና ገንዘብ የማስተዳደር፣ በተቋሞቹ ውስጥ የሚመደቡ ሰራተኞችን የመቅጠርና የማስተዳደር ኃላፊነት የራሳቸው ብቻ ይሆናል።

በኃይማኖት ተቋሞች የሚካሄዱ የበጎ አድራጎትና የልማት ስራዎች በራሳቸው ነፃ አሰራር የሚመሩና የሚሰሩ መሆን አለባቸው። የሕክምና፣ የትምህርት፣ የአረጋዊያን መጦሪያ፣ የሕፃናት ማሳደጊያ፣ የአካል ጉዳተኞች መንከባከቢያ፣ የሞያ ማሰልጠኛ፣ የምክር አገልግሎት መስጫና የመሳሰሉትን ተቋሞች ሰርተው በነፃነት ለማስተዳደርና ለመምራት መብት አላቸው። በእርግጥ የሕክምናም ይሁን የትምህርት የሞያ ማሰልጠኛም ይሁን የምክር አገልግሎት መስጫዎቻቸው የሀገሪቱን የጥራት መለኪያዎችና ሕጋዊ ስርዓቶችን የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ ይገባል።

ማንኛውም ሰው አንድን ኃይማኖት እንዲከተል ወይም እንዳይከተል ማስገደድ የተከለከለ መሆኑን በመርህ ደረጃ መቀበል ተገቢ ነው። ውሳኔው ለግለሰቡ ብቻ መተው አለበት። በኃይማኖቶች መካከል ምንም አይነት ልዩነትና አድሎ እንደማይኖር ማረጋገጥም ያስፈልጋል። ኃይማኖቶች እርስ በርስ የሚያደርጉት ግንኙነት በእኩልነት ላይ የተመሰረተና በትብብር መርህ ላይ የቆመ መሆን አለበት። እያንዳንዱ ኃይማኖት ሰዎችን ለመሳብና አባል ለማድረግ የሚጠቀምበት ዘዴ በማስተማርና በማሳመን ላይ ብቻ መመስረት የሚገባው ሲሆን አንድን ኃይማኖት ወይም የዚያን ኃይማኖት ተከታይ ማንቋሸሽና ማጥላለት አይገባም። የተለያዩ ኃይማኖቶች በተናጠል ከሚያደርጉት ተግባር በተጨማሪ በጋራ ለሕዝብና ለሀገር የሚጠቅም ብዙ ስራ ማከናወን ይችላሉ። የበጎ አድራጎት ስራዎችንና የልማት ተግባሮችን በጋራ ሊሰሩ ይችላሉ። የሕዝብን ሰላምና ጤንነት የሚጎዱ ተግባሮች በማስተማርና በመከላከል የጋራ እንቅስቃሴ ሊያደርጉ ይችላሉ። ለሕዝቡ ጤናና ሰላም ጠቃሚ የሆኑ መረጃዎችን በጽሑፍና በሌላም የማሰራጫ ዘዴ ተጠቅመው በጋራ ማሰራጨት ይችላሉ። ለሰራ አጦች ስራ በመፍጠርና በማፈላለግ፣ ለስራ ብቁ የሚያደርግ ስልጠና በመስጠትና በመሳሰሉት ተባብረው ሊሰሩ ይችላሉ። በአካባቢ ጥበቃ፣ በተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ፣ በሀገር ደህንነት ጥበቃና በመሳሰሉት መስኮች ተቀናጅተው ለመንቀሳቀስና በሀገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ተከታዮቻቸውን፣ ደጋፊዎቻቸውንና አጋሮቻቸውን ለማስተባበር ይችላሉ።

# 7. ሴቶች

በሐገራችን በሕግ ደረጃ ሴቶች ከወንዶች ጋር እኩል መብት እንዳላቸው የሚያረጋግጡ ድንጋጌዎች ቢወጡም በተግባር ግን የሴቶችን እኩልነት የሚጎዱ ሁኔታዎች እንዳሉ ናቸው። በሀገራችን ሴቶች በፖለቲካ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎ ገና ዝቅተኛ ነው። በሥራ፣ በንብረት ባለቤትነት፣ በጤና፣ በትምህርት ወዘተ. የሴቶች ተሣትፎ አሁንም ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር በብዙ ርቀት ወደኋላ የቀረ ነው። በቤተሰብ ኃላፊነትና በቤት ውስጥ ስራ ከወንዶች የበለጠ ሸክም እንደተጫናቸው ነው። ከጠቅላላው የሕዝብ ቁጥር የሴቶች ድርሻ ከሞላ ጎደል ከወንዶች ጋር ተቀራራቢ ቢሆንም በሕብረተሰቡ ውስጥ ከወንዶች ጋር እኩል እድል አላቸው ለማለት አይቻልም። እንዲያውም በአንዳንድ ከተሞች ከሚገኘው ጠቅላላ ሕዝብ ውስጥ የሴቶች ቁጥር የሚበልጥ ቢሆንም በተሣትፎ ደረጃ ግን በጣም ዝቅተኛ ነው።

በትምህርት ረገድ የሴቶች ተሣትፎ መሻሻል የጀመረ ቢሆንም አሁንም በሚፈለገው ደረጃ ላይ አልደረሰም። በተለይም በሞያ ሥልጠና ሴቶች እጅግ ወደኋላ ቀርተዋል። በከፍተኛ ትምህርት ያላቸው ተሣትፎም አጥጋቢ የሚባል አይደለም። በተለይ በገጠር ያሉት ሴቶች በሁሉም መስክ ያላቸው ደረጃ እጅግ በጣም ዝቅተኛ ነው። ይህ የሚያሣየው ሴቶች አሁንም ከባድ በሆነ የቤት ውስጥ ሥራ የተጠመዱ መሆናቸውን ነው። ይህ ሁኔታ በጤንነታቸውም ላይ የሚፈጥረው ከባድ ተጽእኖ በመኖሩ ከወንዶች በባሰ ሁኔታ ለበሽታና ለሞት ተጋልጠዋል። እንደምንም ለመማርና ሥራ ለማግኘት የቻሉትም ቢሆኑ ቁጥራቸው አነስተኛ መሆኑ ብቻ ሣይሆን አብዛኞዎቹ የሚሰሩት ስራ በቂ የመተዳደሪያ ገቢ የማያስገኝ በመሆኑ ከችግር የተላቀቁ አይደሉም።

በሀላፊነት ቦታ ላይ የተመደቡ ሴቶች ቁጥር ከወንዶች ጋር ሲነጻጸር እዚህ ግባ የሚባል አይደለም። በመንግሥት ሥልጣን የሚመደቡ ሴቶች ቁጥር በየጊዜው የሚያሣየው እድገት ፈጣን አይደለም። ሥልጣን በያዘው ፓርቲ ብቻ ሣይሆን በተቃዋሚነት በተሠለፉ ፓርቲዎችም ጭምር ከሕዝቡ ቁጥር ግማሽ የሚሆኑትን ሴቶች ድርሻ ታሣቢ ያደረገ ተሣትፎ እዲኖራቸው የሚካሄድ ጠንካራ ጥረት የለም።

ይኸንን ሁኔታ ከመሠረቱ በመቀየር የሕዝቡን አመለካከትና ጐጅ ልማድ የሚለውጥ ተከታታይ የማስተማር ሥራ ይጠይቃል። የሴቶችን እኩልነት የሚጐዱ ሕጐችንና ልማዶችን የሚከላከል የሕግ ሥርአት መመሥረት ያስፈልጋል። ለሴቶች እኩልነት የሕግ እውቅናና ጥበቃ ከመስጠት አልፎ በተግባር የሚገለጽ ገንቢ እርምጃ መውሠድ ይገባል። በትምህርት ተሣትፎ ከሚገኙበት ዝቅተኛ ሁኔታ ለማውጣትና የወንዶችን መብት በማይጐዳ መንገድ ለሴቶች ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት ይገባል። ለሕክምና፣ ለሥራ፣ ለኃላፊነት፣ ለሀብት ባለቤትነት፣ ወዘተ. ለሁሉም ነገር ከወንዶች እኩል እድል እንዲኖራቸው ተጨባጭ እርምጃ መውሠድ ያስፈልጋል። በተለይ የሴቶች መብትና ሕልውና በሚወሰንባቸው የመንግሥት ሕግ አውጭ አካላት ውስጥ የሴቶች ቁጥር በየጊዜው እያደገ እንዲሄድ የሚያስችል አቅጣጫ መከተል ይገባል። ብዙ ቁጥር ያላቸው የሕግ አውጭ አባላት እንዲኖሩ ብቻ ሣይሆን ብዙ ቁጥር ያላቸው የሴት ሚኒስትሮች፣ ምክትል ሚኒስትሮች፣ ኮሚሽነሮች፣ ሥራ አስኪያጆች፣ መምሪያ ኃላፊዎችና ባለሥልጣኖች እንዲኖሩ ማድረግ የሴቶችን እኩልነት ለማረጋገጥ እንቅፋት የሆኑትን መዋቅራዊ ችግሮች ለማስወገድ ትልቅ አስተዋጽኦ ይኖረዋል።

በመንግስት ሕግ አውጭ አካላት ውስጥ ብዙ ሴቶች ሊገቡ የሚችሉት በምርጫ የሚወዳደሩ የፓለቲካ ፓርቲዎች ሴት አባሎቻቸውን በብዛት ለምርጫ ውድድር ሲያቀርቡ ነው። ስለዚህ ፓለቲካ ፓርቲዎች ለመንግሥት ሥልጣን ውድድር እጩ ተመራጭ በሚያቀርቡበት ጊዜ ከሀገሪቱ ሕዝብ ቁጥር ግማሽ ያህሉን የሚሸፍኑትን ሴቶች ተወዳዳሪዎች ከወንዶች ጋር በሚመጣጠን ደረጃ ለማቅረብ ብርቱ ጥረት ማድረግና የተለየ ትኩረት መስጠት ይገባቸዋል። ከወንዶች ጋር እኩል የሥራ እድል የማግኘት፣ የመደመጥና በሁሉም ጉዳዮች በእኩል ደረጃ የመታየት መብት እንዲኖራቸው መሠረታዊ መፍትሔው የትምህርት ተሳትፎአቸውን በፍጥነት ማሣደግ ነው። ከዚሁ ጐን በሕዝቡ ውስጥ ስለሴቶች የሠፈነውን የተዛባ አስተሣሰብና ጐጂ ልማድ የሚለውጥ ተከታታይ የማስተማር ሥራ መስራት እንደ አስፈላጊነቱም ሕጋዊ ሥርዓቶችን አውጥቶ ተግባራዊ ማድረግ ያስፈልጋል።

የሕዝቡን አመለካከት ለመቀየር የሚደረገው ጥረት በሥርዓተ ትምህርቱም በሕጋዊ ዘርፍ የሚካተትበትን አቅጣጫ መከተል እንዳሚገባው ያለው ግንዛቤ እንደተጠበቀ ሆኖ ሴቶች ራሣቸው የሚያደርጉት ጥረት ለመብታቸው መከበር ምትክ የማይገኝለት ድርሻ አለው። ሴቶች ከወንዶች እኩል እድል ባለማግኘታቸውና እኩል ባለመታየታቸው ያስከተለባቸውን የመብት መጓደል ራሳቸው ለማስወገድ እስካልተንቀሳቀሱ ድረስ በሌሎች መልካም ፈቃድ ብቻ የሚፈታ ችግር አይደለም። በሴቶች ላይ የሚፈጸመውን አድሎ ሴቶች ራሳቸው እንደተገቢና ትክክለኛ ነገር አድርገው በሚመለከቱበት ሁኔታ ውስጥ ለውጥ ለማምጣት ያስቸግራል። ስለዚህ በሴቶች በራሣቸው ውስጥ ያለውን የተዛባ አመለካከትና ጐጅ ልማድ መታገል በቅድሚያ የሴቶች ኃላፊነት መሆኑን ማስጨበጥ ተገቢ ነው። ከቆየ ልማድ፣ ከእምነት፣ ከጐጂ ባህልና ከመሣሠሉት ሁኔታዎች ጋር በተያያዘ የተሠራጨና በሴቶች ውስጥ ስር የሰደደ የአመለካከት ችግር በመኖሩ በተለይ በገጠ ር የሚገኙ ሴቶች በተፈጥሮና በህግ ያላቸውን የእኩልነት መብት አምኖ ለመቀበል ሲያንገራግሩ ይታያል። ከዚህ አንገታቸውን ከሚያስደፋ ልማዳዊ አስተሳሰብና ጐጂ አመለካከት ለማውጣት

ሴቶች የራሳቸውን ድርጅት ፈጥረው መታገል ይጠበቅባቸዋል። የሴቶች ድርጅት መቋቋም ያለበት ከሴትነታቸው ጋር የተያያዘውን የእርግዝና፣ የወሊድና የእናትነት ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስችል የመማሪያ፣ የመደጋገፊያና የልምድ መለዋወጫ መድረክ ለማግኘት ብቻ አይደለም። በሕብረተሰቡ ውስጥ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ባህላዊ መስክ ተገቢ ስፍራ እንዲኖራቸው በሚያስችል መሰረታዊ ጉዳይ ላይ በጋራ እንዲመክሩና የተቀናጀ አቅም እንዲፈጥሩ ለማድረግም የራሳቸው ድርጅት ሊኖራቸው ይገባል። ሴቶች የራሳቸውን ድርጅት መመስረት ያለባቸው ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሥልጣን መንጠላጠያ መድረክና የፕሮግራም ማስፈፀሚያ ክንድ ለመሆን አይደለም። ይልቁንም የራሳቸውን መሰረታዊ የመብትና የእኩልነት ጥያቄዎች ለመፍታት የሚያስችል ድርጅታዊ አቅም እንዲፈጥሩና ለራሳቸውና ለጠቅላለው ሕዝብ የሚጠቅም ቁምነገር መስራት እንዲችሉ ነው።

እስካሁን ድረስ በተጠናከረ ሁኔታና አብዛኞቹን ሴቶች በሚያሳትፍ ደረጃ ነፃ የሴቶች ማህበራት በሀገራችን ለመመስረት የሚያስችል የዴሞክራሲ ስርዓት ባለመኖሩ በሴቶች ስም የሴቶችን የመብትና የእኩልነት ጥያቄ እየጠለፉ የፖለቲካ አጀንዳ ማሳያ ከማድረግ የተለየ ጠቃሚ ነገር ለመስራት ሳይቻል ቆይቷል። የቀድሞው አኢሴማ የኢሠፓ አጀንዳ ማስፈፀሚያ እንደነበረው ሁሉ የአሁኑ አገዛዝም በየክልሉና በየከተሞች በራሱ አምሳል በፈጠራቸው የሴቶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች አማካይነት የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ፕሮግራሙ ማስፈፀሚያ መሳሪያ አድርጎ ይጠቀምባቸዋል። ራሳቸውን ከገዥው ፓርቲ ተፅዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ ለማደራጀት የሞከሩ በሕግ፣ በጋዜጠኛነትና በንግድ የተሰማሩ ሴቶች ቢኖሩም የሚገባውን ድጋፍ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆነ የመንግስት ስርዓት ስለሌለ ሁሉንም መሰረታዊ የሴቶች ችግሮች ሴቶች ወደህዝቡ በሰፊው ለማድረስና ትርጉም ያለው መፍትሔ ለማግኘት የሚረዳ ውጤት ለማስመዝገብ አልቻሉም። በሕግ ስርዓቱ ውስጥ ከዚህ በፊት ይንፀባረቁ የነበሩ ችግሮችን እንዲወገዱና ተገቢ ትኩረት ሳያገኙ የቀሩ ነጥቦችን የሕግ እውቅና እንዲያገኙ በማድረግ፣ በሕብረተሰቡ ውስጥ ደግሞ ሴቶችን በሚጎዳ ሁኔታ የተስፋፉትን እንደ ጠለፋ፣ ያለእድሜ ጋብቻ፣ አስገድዶ መድፈርና ግርዛት ወዘተ. የመሳሰሉ ችግሮች በይፋ ወጥተው የመነጋገሪያ አጀንዳ እንዲሆኑ በማድረግ የሚመሰገን ጥረት የጀመሩ ቢሆንም የሚባለውን ያህል የመንግስት ድጋፍ አላገኙም። ስልጣን ላይ ያለው መንግስት ለእነዚህ ማህበራት የሚደራጁበት የምስክር ወረቀት መስጠቱን እንደትልቅ የዴሞክራሲ እርምጃ እየጠቀሰ ከመመፃደቅ በስተቀር ጥረታቸውን የሚያዳክሙ ልዩ ልዩ ተፅዕኖዎችን ከማድረግ ተቆጥቦ አያውቅም። መደራጀት በማንም ሊነፈግ የማይገባና በማንም ችሮታ ሊሰጥ የማይችል መሰረታዊ መብት መሆኑን የማይገነዘብ መንግስት እስካለ ድረስ የምስክር ወረቀት መስጠትን እንደ ዴሞክራሲ መጀመሪያና መጨረሻ አድርጎ የመመልከት ደካማ ግንዛቤ መኖሩ የማይቀር ነው። የአብዮታዊ ዴሞክራሲን አጀንዳ ከማስፈፀም በስተቀር ለሴቶችም ይሁን ለጠቅላላው ሕዝብ የሚጠቅም አንዳች ቁምነገር ሰርተው ለማያውቁትና «የሴቶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት» እያለ ላቋቋማቸው ቅርንጫፎቹ መጠነ ሰፊ የሀገር ሀብትና ልዩ ልዩ ድጋፍ በገፍ የሚያቀርበው ገዥው ፓርቲ በነፃነት ለተደራጁት የሴቶች ማህበራት ምቹ የስራ ሁኔታ በመፍጠር ትብብር ሊያሳይ አለመቻሉ ስርዓቱ የሴቶችን ጥያቄ ለፕሮፓጋንዳ ጥቅም እንጂ ከልቡ ለመፍታት ፍላጎት የሌለው መሆኑን የሚያሳይ ነው።

ስለዚህ አሁን ስልጣን ለይ ያለው ፓርቲ በሴቶች ስም የሴቶችን የመብትና የእኩልነት ጥያቄ እየጠለፈ ለራሱ የፖለቲካ አጀንዳ ማሳኪያ መድረክ ሆኖ የሚያገለግል ጥገኛ ማህበር እንዲኖር ከመጣር በስተቀር በነፃነት ለሚደራጁና ለሚሰሩ ማህበራት ማበብ ጠቃሚ ድጋፍ እንደማያደርግ መገንዘብ አስፈላጊ ነው። የሴቶችን ነፃ ማህበር መቋቋም አስፈላጊ የሚያደርገው አንዱ ሁኔታም ለመብታቸውና ለእኩልነታቸው መረጋገጥ መሰረት የሚሆን የዴሞክራሲ ስርዓት በሀገሪቱ እንዲመሰረት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ማበርከት ስለሚገባቸው ነው። ሴቶች በሞያቸው፣ በፆታቸው፣ በስራ ዘርፋቸው፣ በመኖሪያ ክልላቸው ወዘተ. እንደየሁኔታው ሊደራጁና የሴቶችን የጋራ ጥረት የማስተባበር ሚና ሊጫወቱ ይችላሉ። ይሁን እንጂ ጥረታቸው የተበታተነ እንዳይሆን፣ የተሻለ ቅንጅትና ትብብር መፍጠር እንዲችሉ፣ ሊደመጥ የሚችል ጠንካራ ድምጽ እንዲኖራቸውና ለውጥ የሚያመጣ ትርጉም ያለው ተጽዕኖ ማሳረፍ እንዲችሉ ይበልጥ የተቀናጀ አደረጃጀት መፍጠር ይኖርባቸዋል። በተለያየ መንገድ የተደራጁ ነፃ የሴቶች ማህበራት የሚተሳሰሩበት፣ ጥረታቸውን አቀናጅተው ለማስተባበርና ለመምራት የሚችሉበት በየደረጃው አንድ የጋራ መድረክ መፍጠር ይገባቸዋል። እንዲህ ዓይነት አደረጃጀት ሲፈጥሩ በመላ ሀገሪቱ ያሉትን ሴቶች በጋራ ለማሰለፍ፣ በጠቅላላው ሕዝብ ውስጥ ሊደርስ የሚችል ሰፊ እንቅስቃሴ

ለማድረግና በዓለም አቀፍ የሴቶች እንቅስቃሴ ውስጥም ትርጉም ያለው ተሳትፎ ለማድረግ የሚረዳ ውክልና እንዲኖራቸው ያስችላል:: ገንዘብን፣ እውቀትን፣ ጉልበትንና ጊዜን በቁጠባና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመጠቀምም ይረዳቸዋል:: ሴቶች በነጻነት ተደራጅተው የመብትና የእኩልነት ጥያቄያቸውን በሰፊው ለማንፀባረቅ፣ በሁሉም መስኮች ከወንዶች ጋር እኩል እድል እንዲኖራቸው ለማድረግና በመብታቸው እንዲጠቀሙ ለማስቻል በመንግስት በኩል የሕግ ጥበቃ ሊደረግላቸው ይገባል:: የማህበራቸው የፋይናንስ ምንጭ በዋናነት ከአባሎቻቸው በፈቃደኝነት ከሚሰጥ የአባልነት መዋጮና እርዳታ፣ ከገቢ ማስገኛ ተቋሞች፣ ለፕሮጀክቶች ማስፈፀሚያ ከሀገር ውስጥና ከውጭ የሚገኝ ብድርና እርዳታ፣ ከሌሎች ማህበራት የሚገኝ ድጋፍና እርዳታ ወዘተ. ቢሆንም ከመንግስትም የሚቀርብ ድጋፍ መኖር አለበት:: ለሥልጠና፣ ለፕሮጀክቶች ዝግጅት፣ ለጥናትና ምርምር ወዘተ. የፋይናንስ፣ የቴክኒክና የምክር ድጋፍ እንዲያገኙ በመንግስት በኩል ትኩረት ሊሰጣቸው ይገባል:: የሴቶች ጥያቄ በነፃነት የመደራጀት፣ በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ከወንዶች እኩል ተሳትፎ የማድረግና ለዚሁ መብታቸው መረጋገጥ ዋስትና የሚሆን የዴሞክራሲ ስርዓት የመመስረት ጥያቄ ብቻ አይደለም:: በሀገሪቱ ልማት ውስጥ በእኩልነት የመሳተፍ፣ ሀገሪቱ ካላት የኢኮኖሚ ጥሪትና ማህበራዊ አገልግሎት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከወንዶች እኩል ተጠቃሚ ለመሆን የሚያስችል የልማትና የፍትሃዊነት መስፈን ጥያቄም ነው::

ስለዚህ የሴቶችን ጥያቄ መደገፍ በአንድ በኩል ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ግማሽ የሆነውን ሕዝብ ጥያቄ መደገፍ ማለት ሲሆን በሌላ በኩል የዜጎችን እኩል ተሳትፎ የሚያረጋግጥ ልማትንና እድሎን የሚያጠፉ ፍትሃዊነትን መደገፍ ማለት ነው:: በአጭሩ ለሴቶች የሚደረግ ድጋፍ ለዴሞክራሲ ስርዓት፣ ዜጎችን በእኩልነት ለሚያሳትፍ ልማት፣ ፍትሃዊ ለሆነ የሀብትና የአገልግሎት ክፍፍል የሚደረግ ድጋፍ ነው:: የሴቶችን እኩልነት መብት መደገፍ በአጠቃላይ የሰውን ልጅ እኩልነት መብት ከመደገፍ ጋር የተያያዘ ነው:: የሴቶችን የትምህርት፣ የጤና፣ የስራ ወዘተ. ችግሮች ማቃለል ማለት የሕፃናትን፣ የቤተሰብንና በአጠቃላይ የሕብረተሰብን መሰረታዊ ችግሮች ማቃለል ማለት ነው:: በመሆኑም ሴቶችን በሁሉም ረገድ እኩል መብት እንዲኖራቸው በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ባህላዊ ጉዳዮች ለመደገፍ የሚያስችል ፖሊሲ አቅጣጫ መከተልና በስራ ላይ ማዋል ይገባል ብሎ ኢዴፓ ያምናል::

# 8. ወጣቶች

ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ ከፍተኛውን ቁጥር የያዘው በወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ነው:: ይህ የሕብረተሰብ ክፍል ማንኛውንም ዓይነት እውቀት ለመቅሰም የሚያስችል ቀልጣፋና ብሩህ አእምሮ፣ ለምርት ተግባር ሊውል የሚችል ጉልበትና በቀላሉ የማይዝል አካላዊ ጥንካሬ ያለው ነው:: በዚያው ልክ በአግባቡ ካልተያዘና ጠቃሚ ለሆነ ነገር ፍላጎት እንዲኖረው በሚያስችል ትምህርት እየተኮተኮተ ካልታነፀ በስተቀር ከወጣትነቱ ተፈጥሯዊ ሁኔታ በተያያዘ ለተለያዩ አደጋዎች በቀላሉ ሊጋለጥ የሚችል ነው:: ወጣቱ የሕብረተሰብ ክፍል ወደመልካም አቅጣጫ እንዲጓዝ ወይንም ወደመጥፎ ዝንባሌ እንዲነሳሳ የሚያደርጉ በርካታ ሁኔታዎች ቢኖሩም ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤትና አጠቃላዩ ሕብረተሰብ ወዘተ. የሚጫወቱት ሚና ቀላል አይደለም::

የወጣቱ ሕብረተሰብ ዝንባሌ የብዙ ጉዳዮች ድምር ውጤት ነው:: ብዙ ጊዜ በወጣትነት እድሜ ክልል ውስጥ ከሚገኙት ዜጎች መካከል አንዳንዶቹ ጥፋት በሚፈፅሙበት ወቅት ወጣቱን እንዳለ የማውገዝና የማማረር አዝማሚያ ጎልቶ ይንፀባረቃል:: «የዘቀጠ፣ ደካማ፣ የሀገር ፍቅር የሌለው፣ ለሰዎች ክብር የማይሰጥ፣ በንቀት የተወጠረ ወዘተ. ትውልድ» እያሉ ለወጣቱ ባህርይ መጥፎ ምስል የሚሰጡ ሰዎች ጥቂት አይደሉም:: ቤተሰብ፣ መንግስትና የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የኃይማኖት ተቋሞችና የትምህርት ተቋሞች ወዘተ. ይኸንን አስተሳሰብ የሚያንፀባርቁበት ጊዜ ጥቂት አይደለም:: እንዲያውም የሀገራችንን ወጣቶች መልካም ገጽታ በአደባባይ ለመግለጽ የሚሞከረው ካለወጣቱ ተሳትፎ ምንም ለማድረግ የማይቻልበት የጦርነት ሁኔታ ከተፈጠረ ብቻ ነው:: ከዚያ ውጭ ለወጣቱ በጎ ጎን ከበሬታ የሚሰጥና የወጣቱን ጉዳይ መሰረታዊ ነጥብ አድርጎ ሲወጣና ሲወርድ የሚታይ አካል በኢትዮጵያ ማግኘት ከባድ ነው::

በሰላሙ ጊዜ የሚያናንቁትንና የሚረግሙትን ወጣት ወይንም ከማንኛውም የውይይት አጀንዳ ውጭ አድርገው የረሱትን ወጣት ቀውጢ ሲፈጠር፣ ጦርነት ሲነሳና መውጫ መግቢያ ሲጠፋ

ብቻ «መመኪያችን፣ ኃይላችን፣ ተስፋችን፣ መኩሪያችን ወዘተ.» እያሉ ማሞካሸት ኢትዮጵያ ውስጥ የተለመደ ነው። መብቴ ተነካ፣ ጥቅሜ ተጓደለ፣ ነጻነቴ ተገፈፈ ወዘተ. የሚል ሰላማዊ ጥያቄ ባነሳ ቁጥር የሳንጃና የጥይት ምላሽ የሚሰጡት፣ ከሀገር እንዲሰደድ፣ እንዲገረፍ፣ ወህኒ እንዲወረወርና ስቃይ እንዲቀበል፣ ጨካኝ እርምጃ የሚወስዱበት የፖለቲካ ኃይሎችና መንግስታት ሳይቀሩ የጨበጡትን ስልጣን ላለመነጠቅ የወጣቱን ኃይል መጠቀም ባስፈለጋቸው ጊዜ ለወጣቱ የማይገቡት ቃል፣ የማይሰጡት ተስፋና የማያቀርቡት ውዳሴ የለም። የሚፈልጉትን ካገኙ በኋላ ግን መልሰው ወጣቱን እስከመፈጠሩ ይዘነጉታል።

ለወጣቱ ትምህርት፣ ጤንነት፣ ስራና ዘላቂ ሕልውና የሚጠቅም አንድም የዴሞክራሲና የልማት አጀንዳ ቀርፀው የረባ ነገር ሳይሰሩ ይኸውና ወጣት የነበረው ጎልማሳ እየሆነ ዘመንን ዘመን እየተካው መኖር የተለመደ ሆኗል። በአለም ውስጥ እንደ ኢትዮጵያ ወጣቶች ሁሉም ዓይነት እድል ተነፍጓቸው ለመከራና ስቃይ ብቻ የተጋለጡ አሳዛኝ ወጣቶች ስለመኖራቸው ያጠራጥራል። በኢትዮጵያ ወጣቶች ልክ ጦርነት የሚለበልበው፣ ርሃብ የሚጨርሰው፣ እስርና ግርፋት የበዛበት፣ ሀገር ጥሎ መሰደድ ያንገሸገሸው፣ የመማርና ስራ የማግኘት መብቱን የተገፈፈ፣ ለበሽታና ለተለያዩ አደጋዎች የተጋለጠ፣ በነፃነት ለመደራጀት፣ ሀሳቡን ለመግለፅና ሰላማዊ ተቃውሞ ለማሰማት በሞከረ ቁጥር በአደባባይ በጥይት የሚረሸን ወጣት በየትም ሀገር ማግኘት አይቻልም። ላለፉት ዓመታት መንግስት በሌለባት ጎረቤት ሶማሊያ የሚገኙ ወጣቶች እንኳ በአንዳንድ ጉዳዮች ከኢትዮጵያ ወጣቶች የሚሻል ተነጻጻሪ ነፃነትና መብት አላቸው።

በየትኛውም አለም የሚገኙ ወጣቶች በአብዛኛው ተቀራራቢ የሆኑ የጋራ ፍላጎቶች እንዳሏቸው የታወቀ ነው። ብዙውን ጊዜ የወጣቱ ሕብረተሰብ ዋነኛ ፍላጎቶች መማር፣ ስራ ማግኘት፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትና የተረጋጋ ሰላም ማግኘት፣ ከበሽታ መጠበቅና መዝናናት ወዘተ. የመሳሰሉት ፍላጎቶች ናቸው። ለብዙዎቹ የታዳጊ ሀገር ወጣቶች እነዚህ ፍላጎቶች የሚሟሉበት እድል የጠበበ ቢሆንም ለኢትዮጵያ ወጣቶች ደግሞ ጨርሶ የማይጨበጡና ለማሰብ እንኳ የሚከብዱ ናቸው። የኢትዮጵያ ወጣቶች ሕይወታቸውን ለማቆየት የሚያስችል አንድ ቁራሽ ዳቦ በቀን ማግኘት በማይችሉበት አሳዛኝ ሁኔታ ውስጥ ስለሚገኙ ሌሎቹ ፍላጎቶቻቸው እንደሕልም የሚያዩ ናቸው። እስኪጠግብ በልቶ ለማደር የማይችለው የኢትዮጵያ አብዛኛው ወጣት ስለትምህርት፣ ስለሕክምና፣ ስለዴሞክራሲ፣ ስለሰላም፣ ስለሥራ፣ ስለመዝናኛ ወዘተ. ፍላጎቶቹ መሟላት ማሰቡ ባይቀርም በቀላሉ የሚያገኛቸው ነገሮች አልሆኑም። ለዚሁ ሁሉ ስቃይ መሰረታዊ ምክንያቱ ደግሞ በሀገሪቱ ውስጥ የአገዛዝ ስርዓት መተከሉ ነው። ልማትን በማምጣትና ድህነትን በማጥፋት የወጣቱን የትምህርት፣ የጤና፣ የስራ፣ የሰላም፣ የዴሞክራሲና የመዝናናት ወዘተ. ፍላጎት የሚያሳካ የዴሞክራሲ ስርዓት እስካልተፈጠረ ድረስ አሁንም የኢትዮጵያ ወጣቶች ችግር በከፋ መልኩ መቀጠሉ የማይቀር ነው። እናም እንደማንኛውም ሌሎች የሀገሪቱ ችግሮች ሁሉ ለኢትዮጵያ ወጣቶች ችግር መፈታትም አማራጭ ሀሳብ በሚቀርብበት ጊዜ ከሁሉ በፊት ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባው ጉዳይ የአገዛዝ ስርዓት ከሀገሪቱ የሚነቀልበትና በምትኩ የዴሞክራሲ ስርዓት የሚተከልበት መንገድ መፈጠር አለበት የሚለው ነጥብ ነው።

ለዚህ ትልቅ አላማ ከፍተኛ አስተዋፅኦ የሚጠበቀው ደግሞ የሀገሪቱ ተረካቢና የወደፊቱ መሪ ከሆነው ከራሱ ከወጣቱ ትውልድ ነው። የወጣቱ ትውልድ የወደፊት ራዕይና ተስፋ በሀገሪቱ ሊኖር በሚችለው መፃኢ ሁኔታ የሚወሰን የመሆኑን ያህል የሀገሪቱ መፃኢ እድል ደግሞ በተራው በወጣቱ ተሳትፎ የሚወሰን መሆኑ የግድ ነው።

የኢትዮጵያ ወጣቶች አለመታደል ሆኖ በሁሉም ሁኔታ እጥረት በሚታይበት አስቸጋሪ ፈተና ውስጥ ለመኖር ቢገደዱም ከዚህ ለመውጣት የሚያስችል የሕይወት አማራጭ መፈለግ ይጠበቅባቸዋል። ሞትን፣ ረሃብን፣ ስደትን፣ መሀይምነትን፣ በሽታን፣ ጦርነትን፣ የመብት ረገጣን ወዘተ. እየኖሩበት ስለሆነ ጉዳቱን በሚገባ ያውቁታል። ይኸንን ውርደት ተሸክሞ መቆየት ጥሩ የሕይወት አማራጭ እንዳልሆነም በሚገባ ይረዱታል። ከዚህ የተሻለው የሕይወት አማራጭ ለራሳቸው ብቻ ሳይሆን ለጠቅላላው ሕዝብ ፍላጎት መሳካት መሰረት የሚሆን የዴሞክራሲ ስርዓት እንዲፈጠር መስራትና መታገል ነው።

የኢትዮጵያ ወጣቶች ለመብታቸውና ለፍላጎታቸው መረጋገጥ መሰረት የሚሆነውን የዴሞክራሲ ስርዓት በመፍጠር የተሻለ የሕይወት ምርጫ እንደሚኖራቸው ከታመነበት ይኸንን ዓላማ

የሚያሳኩት በተናጠል ሳይሆን የተደራጀ አቅም በመፍጠር ነው። ወጣቶች እስካልተደራጁ ድረስ ለመብታቸውና ጥቅማቸው መሳካት የሚበጅ መሰረታዊ ለውጥ በሀገሪቱ ማምጣት ይቅርና ቁራሽ ዳቦ በቀን እያገኙ ሕይወታቸውን የማቆየት እድል ለረጅም ጊዜ መኖሩን በእርግጠኝነት ለመተንበይ አይቻልም። ወጣቶች መደራጀት ያለባቸው የፖለቲካ ኃይሎች አጀንዳ አስፈፃሚ መሳሪያ እንዲሆኑ፣ ለአገዛዝ ስርዓት መወጣጫ መሰላል ሆነው እንዲያገለልሉና ለአገዛዝ ስርዓት እድሜ መቀጠል የሚያግዝ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ አይደለም። ከሁሉም በፊት መደራጀት ያለባቸው በፍላጎታቸውና ጥቅሞቻቸው ዙሪያ በሚገባ እንዲመክሩ፣ ለፍላጎቶቻቸውና ጥቅሞቻቸው መሳካት የተቀናጀ ጥረት እንዲያደርጉና ድምፃቸው እንዲሰማ በሚያስችል ደረጃ ተባብረው እንዲቆሙ የሚያግዝ ነፃና ዴሞክራሲያዊ መድረክ እንዲኖራቸው ነው። ነፃና ዴሞክራሲያዊ የሆነ ድርጅት እስካልመሰረቱ ድረስ በኢኢወማ ተሰባስበው የነበሩ ወጣቶች ድካም መና ሆኖ እንደቀረው ሁሉ አሁንም ተመሳሳይ እጣ ሊያጋጥማቸው እንደሚችል መገመት ነቢይ መሆንን አይጠይቅም። የአሁኑ አገዛዝ «የወጣቶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅት» እያለ በየክልሉና በየከተማው አቋቁሞ በተላላኪነት ያሰለፋቸውን ዓይነት ድርጅቶች በመመስረት የወጣቱን ፍላጎቶችና ጥቅሞች ለማሳካትና የሚጠቅም አንዳች ቁምነገር መስራት የማይቻል ነው። ኢሠፓ ሲወድቅ አኢወማ አብሮ እንደወደቀው ሁሉ አብዮታዊ ዴሞክራቶች ሲወድቁ የእነርሱ ተላላኪ የሆኑት የወጣቶች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶችም ሕልውና አብሮ ያበቃለታል። ስለዚህ የሀገሪቱ ወጣቶች መመስረት የሚገባቸው ማህበር ለወጣቶች ፍላጎቶችና ጥቅሞች መሳካት የሚያገለግል፣ በፖለቲካ ፓርቲዎች እየተጠመዘዘ የአገዛዝ መሳሪያ የማይሆንና በነፃነት የሚመራ ዴሞክራሲያዊ ተቋም ነው። አገዛዝ ሲፈርስ አብሮ የሚናድ ተቀፅላ ድርጅት ሳይሆን በወጣትነት እድሜ መስመር የሚያልፉ ተከታታይ ትውልዶች በፈቃደኝነትና በፍላጎት የሚቀላቀሉት፣ የወጣቶችን እምነትና ከበሬታ ያገኘ ዴሞክራሲያዊ ተቋም እንዲሆን በሚገባ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ለዚህ ዓይነቱ ዴሞክራሲያዊ ተቋም ሕብረተሰቡ በሚችለው ሁሉ ድጋፍ እንዲያደርግ ያስፈልጋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ ነፃና ዴሞክራሲያዊ የሆነ የወጣቶች ማህበር መኖር ወጣቶች የራሳቸውን ባህርይና ችሎታ በነፃነት እንዲገነቡ ያስችላል። የራሳቸውን ሕይወት በራሳቸው ኃላፊነት የመቅረጽ ትምህርት እንዲያገኙ ይረዳል። የአንድ ዴሞክራሲያዊ መንግስት ኃላፊነት ይኸንኑ ዓላማ በተለያየ መንገድ ማበረታታትና መደገፍ ነው። መብታቸውን በሚገባ እንዲጠቀሙበት መርዳት ነው። የወጣቶችንም ሆነ የሌሎችን ማህበራት የፖለቲካ አጀንዳ ማስፈፀሚያ መሳሪያና ተላላኪ አድርጎ መጠቀም የአብዮታዊ ዴሞክራቶች እንጂ የዴሞክራሲዊ ፓርቲዎች ባህርይ አይደለም። ወጣቶች ሀገራቸውን የሚወዱት፣ ታሪካቸውንና ባህላቸውን የሚያከብሩት፣ ሀገራቸውን ከማንኛውም አደጋና ችግር ለመከላከል በሚያስችል ማንኛውም ተልዕኮ በፈቃደኝነት የሚሰለፉት ሀገራቸው የመብታቸውና የጥቅማቸው መከበሪያ እውነተኛ ቤታቸው መሆኗን ሲያረጋግጡ ነው። ዴሞክራሲያዊ መንግስታት የሚሰጡት ድጋፍ ወጣቶች ይኸ ስሜት በሚገባ እንዲኖራቸው ለማድረግ እንጂ እጅ እየጠመዘዙ ይኸንን አጀንዳ ደግፍ ያኛውን ይኸንን ተቃወም የሚል ተፅዕኖ ለማሳደርመሆን የለበትም። ይኸ አይነቱ ባህርይና ተግባር የአብዮታዊ ዴሞክራቶች ወይም የአገዛዝ ስርዓቶች ነው።

በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የተቋቋመ ነፃና ዴሞክራሲያዊ የወጣቶች ማህበር ድጋፍ የሚደረግለት በመንግስት ብቻ ሳይሆን በሁሉም ፈቃደኛ ወገኖች ነው። መንግስትም ለወጣቶች መብትና ጥቅም መጠበቅ የሚያገለግሉ ሕጋዊ ስርዓቶችን ከመዘርጋት በተጨማሪ ከማህበራዊ መድረኮችና ከበጎ ፈቃደኞች ድጋፍ የሚያገኙበት እድል እንዲፈጠር ጥረት ያደርጋል። የተለያዩ ማህበራዊ ድርጅቶችና ከፖለቲካ ነጻ የሆኑ ተቋሞች ለወጣቱ የትምህርት ስልጠናና የስራ እድል፣ የሕክምና፣ የመዝናኛ ወዘተ. ድጋፍ እንዲያደርጉ ያበረታታል። የፌዴራል መንግስት ብቻ ሳይሆን የክልል መንግስታትም ተገቢውን የሕግ ጥበቃ ከማድረግ ጀምሮ ነጻ ተቋሞችና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የወጣቱን ጥቅምና ፍላጎት በሚጠብቁ መስኮች ድጋፍ እንዲያደርጉ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ይገባቸዋል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ነፃ ድርጅት ከማግኘት በተጨማሪ ትልቁ ችግራቸው ለመማር የሚያስችላቸውን የገንዘብ ወጪ የሚሸፍን የኢኮኖሚ አቅም ማጣት ነው። በዚህ ረገድ መንግስት፣ ከፖለቲካ ተፅዕኖ ነፃ የሆኑ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ማህበራዊ ተቋሞች ትምህርት ቤቶችን አብዛኛው ወጣት ወደሚገኝበት የገጠር መንደሮች ቀረብ ባለ ሁኔታ በመክፈት፣ ለልዩ ልዩ የትምህርት ወጪዎች መደገፊያ የሚሆኑ ፕሮግራሞችን እየቀየሱ በስራ

ላይ በማዋል፣ በረጅም ጊዜ የሚከፈል ብድር በመስጠት፣ ስፓንሰር ሽፕ በመሆንና የስኮላር ሽፕ እድል እንዲያገኙ በመርዳት ወዘተ. ድጋፍ የሚያደርጉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ይገባል:: የወላጆችንና አሳዳጊዎችን አቅም የሚያጠናክር ድጋፍ ማድረግም ለወጣቶች የትምህርት ችግር አንድ መፍትሔ ሊሆን ይችላል::

ሌላው የኢትዮጵያ ወጣቶች ችግር እንደምንም ተምረው የተወሰነ የትምህረት ደረጃ ከጨረሱና ወደስራ ለመሰማራት ከተዘጋጁ በኋላ የስራ እድል ማጣት ነው:: ለዚህ ዋናው ምክንያት በሀገሪቱ የኢንቨስትሜንት አለመኖርና የኢኮኖሚው ደካማ መሆን ነው:: ሌላው ደግሞ ወጣቶቹ የሚማሩት ትምህርት በአብዛኛው በቀለም ትምህርት ላይ ያተኮረ ሆኖ በመቆየቱና የሞያ ትምህርት የተከታተሉትም ለስራ ብቁ በሚያደርግ የጥራት ደረጃ አለመማራቸው ነው:: ከዚህ በተጨማሪ የሰራተኛ አቀጣጠር ስርዓቱ ለችሎታ ቅድሚያ የሚሰጥ ወይንም ስራና ሰራተኞችን በማገናኘት ዓላማ ላይ የተመሰረተ ሳይሆን ለዘርና ለፖለቲካ ታማኝነት እንዲያገለግል ሆኖ የተቃኘና ግልፅ ለሆነ ሙስናና አድሎ የተመቻቸ መሆኑ ነው:: ስለዚህ የአቀጣጠር ስርዓቱ ግልፅና ፍትሃዊ እንዲሆን፣ ስራና ሰራተኛን የማገናኘት ዓላማ ያለውና በችሎታ መመዘኛ ላይ ተመስርቶ እንዲከናወን በሚያስችል ሁኔታ መለወጥ ይኖርበታል:: የትምህርት አሰጣጡም ለስራ ብቁ የሚያደርግ ጥራት እንዲኖረው ማድረግ ያስፈልጋል:: መንግስትና መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞች ትምህርት ጨርሰው ስራ ለሌላቸው ወጣቶች ተጨማሪ የስራ እድል የሚያስገኙ የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴዎች እንዲበረታቱ ሁለገብ ጥረት ከማድረግ በተጨማሪ ለስራ ብቁ ተወዳዳሪ የሚያደርጉ ተጨማሪ ስልጠናዎችን በመስጠት፣ ስራ በማፈላለግ፣ የራሳቸውን ስራ እንዲፈጥሩ የሚያስችል የቴክኒክና የፋይናንስ እርዳታ፣ የብድር አገልግሎትና የመሳሰሉትን ድጋፎች ለማቅረብ በሚያመቻቸው አቅጣጫ መንቀሳቀስ ይገባል:: ስራ እስከሚያገኙ ድረስ ቀድሞ የቀሰሙት እውቀት እንዳይጠፋባቸው፣ አልባሌ ወደሆነ አቅጣጫ እንዳያመሩና መጪው ሕይወታቸውን ለሚያበላሽ አደጋ እንዳይጋለጡ የነፃ አገልግሎት እየሰጡ የሚቆዩበትን እድል መፍጠር መጻህፍት ቤቶችና ሌሎች ጤንነትን ለመጠበቅ የሚረዱ የጊዜ ማሳለፊያዎች እንዲስፋፉ ማድረግም ሌላው ጠቃሚ ነገር ነው::

የኢትዮጵያ ወጣቶች ሌላው ትልቅ ችግርና ስጋት የኤድስ በሽታ መስፋፋት ነው:: ወጣቶች ለዚህ ስጋት በግንባር ቀደምትነት መጋለጣቸውና የበሽታውም ዋነኛ ተጠቂ መሆናቸው ቢታወቅም ኤድስ በአጠቃላይ የሀገሪቱ ስጋት መሆኑ ግልጽ ነው:: ምክንያቱም አምራች የሆነውን ኃይል በከፍተኛ ደረጃ የሚያጠቃ በመሆኑ መዘዙ በሀገሪቱ ልማትና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ማስከተሉ ስለማይቀር ነው:: በኤድስ የሚጠቁት ወጣቶች ሕፃናት ልጆቻቸው ያለአሳዳጊ፣ አቅመ ደካማ ወላጆቻቸው ደግሞ ያለጧሪና ቀባሪ እንዲቀሩ ምክንያት ስለሚሆኑ የሀገሪቱን ኢኮኖሚና ማህበራዊ አገልግሎት በእጅጉ የሚያዳክም ውጤት ይኖረዋል:: በዚህና በሌሎችም ምክንያቶች የኤድስ በሽታ መስፋፋት የሀገሪቱም ትልቅ ስጋት ነው::

ወጣቶች ከዚህ አደጋ የሚጠበቁበት እድል የተንጠለጠለው በዋናነት በራሳቸው ጥንቃቄ የማድረግ ችሎታ ላይ ነው:: አንድም ራሳቸውን ከበሽታ መተላለፊያ መንገዶች ለማቀብ የሚያስችል ጥንቃቄ ያደርጋሉ፤ አልያም የመከላከያ ክትባት በሌለውና ከበሽታው ለመዳን የሚያስችል መድኃኒት ባልተገኘለት ቀሳፊ በሽታ ይለከፋሉ:: ይህ እንዳይሆን ትልቁ መፍትሔ የወጣቶችን ግንዛቤ በማሳደግ ከበሽታው እንዲጠነቀቁ ማድረግ ነው:: በዚህ ተግባር መንግስት ብቻ ሳይሆን ቤተሰብ፣ ትምህርት ቤት፣ የስራ ቦታ፣ የኃይማኖት ድርጅቶች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ተቋሞችና መላው ሕብረተሰብ በጋራ መስራት ይኖርባቸዋል:: ወጣቶች ስለበሽታው መረጃ እንዲያገኙ በመርዳት፣ በተለይም በሀገሪቱ ገጠር አካባቢ የሚገኙ ወጣቶች መረጃ የሚያገኙበትን ሁኔታ በመፍጠር መረባረብ ይገባል:: በአሁኑ ወቅት የወጣቶች ማህበራት ዋነኛ ስራ መሆን ያለበት ወጣቶች ራሳቸውን ከኤድስ በሽታ መጠበቅና መከላከል በሚችሉበት ሁኔታ ላይ ነው::

የወጣቶች መሰረታዊ ችግሮች የተባሉትን የትምህርት፣ የስራ አጥነትና የጤና ሁኔታዎች ለማሻሻል መንግስት ራሱን የቻለ የወጣቶች ፖሊሲ ቀርፆ፣ የተግባር መርሃ ግብር አውጥቶና ለዚህ ተፈፃሚነት የሚያገለግል ፈንድ ከሀገር ውስጥና ከውጭም አፈላልጎ ሰፊ እንቅስቃሴ ማድረግ ይኖርበታል:: በዚህ ፈንድ አማካይነት ለወጣቶች ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ባህላዊ አቅም መጎልበት የሚያግዝ ተጨባጭ ስራ መስራት ይጠበቅበታል::

# 9. ስፖርትና መዝናኛ

ስፖርት የሰዎችን ጤና በመጠበቅና የእረፍት ጊዜ ማሳላፊያ በመሆን ከሚሰጠው ጥቅም በተጨማሪ ለሕዝቦች ግንኙነትና ትብብር፣ የሀገርን መልካም ገጽታ ለማሳወቅና ኢኮኖሚን ለመደገፍ ይረዳል:: በዘርፉ ለተሰማሩትም መተዳደሪያና የኑሮ መሰረት ሆኖ ያገለግላል:: ይሁን እንጂ በሀገራችን ለስፖርት የሚሰጠው ትኩረት እጅግ ዝቅተኛ በመሆኑ ከዘርፉ መገኘት የሚገባ ጥቅም እየተገኘ ነው ለማለት አይቻልም:: በእርግጥ በአትሌቲክስ ስፖርት ጥቂት በዓለም አቀፍ ደረጃ ውጤታማ የሆኑና ከፍተኛ ስምና ዝና ማግኘት የቻሉ ስፖርተኞች በመታየታቸው ለሀገሪቱ ያጎናጸፏት ክብር የሚናቅ አይደለም:: በአሁኑ ጊዜ በየትኛውም የዓለም ማዕዘን ኢትዮጵያ በመልካም ስም የምትጠራበት አጋጣሚ ካለ የአትሌቲክስ ስፖርት ጀግኖቿ ያስመዘገቡት የሚያስመካ ውጤት ነው:: ሀገሪቱ ካላት ውስን ሀብት እየሸረፈች በምትመድበው የውጭ ምንዛሬ በየሀገሩ ከከፈተቻቸው የኤምባሲ ጽህፈት ቤቶችና በዲፕሎማሲ ስራ ከመደበቻቸው ሰዎች ይልቅ እነ አበበ ቢቂላ፣ ደራርቱ ቱሉ፣ ኃይሌ ገብረ ስላሴና ሌሎች የአትሌቲክስ ጀግኖች በኦሎምፒክ መድረክ ያስመዘገቡት ድልና በዚህ ምክንያት ከፍ ብሎ የተውለበለበው የሀገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ ለኢትዮጵያ ያስገኙት መልካም ስምና እውቅና የበለጠ ዋጋ እንዳለው የሚያከራክር አይደለም:: የሀገሪቱ መሪዎች ዓለምን ከጫፍ እስከጫፍ ቢዞሩ የማራቶን ጀግኖች የሚስቡትን ትኩረትና ለሀገሪቱ የሚያስገኙትን ክብር ለማስገኘት ፈጽሞ አይቻላቸውም:: አንድ የውጭ ዜጋ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ሚኒስትር ማነው ተብሎ ቢጠየቅ መልስ ለመስጠት የሚቸገረውን ያህል አበበ ቢቂላ ወይም ደራርቱ ቱሉ ወይም ኃይሌ ገብረ ስላሴ ማነው ቢባል በቀላሉ ለመለየት አይሳነውም:: ሀገሪቱ የድርቅ፣ የረሃብና የጦርነት ተምሳሌት ብቻ ሆና እንዳትቀር በአትሌቲክስ ስፖርት የተሰማሩ ዜጎች የሚጥሩት መልካም ገጽታ በሌላ የዲፕሎማሲ ስራ በቀላሉ ሊገኝ የሚችል አይደለም:: በሌሎችም የስፖርት ዓይነቶች ትኩረት ቢደረግ ኖሮ በርካታ የስፖርት አምባሳደሮች ለኖሩና የሀገራችንም መልካም ገጽታ በሰፊው ሊታወቅ የሚችልበትን እድል ማመቻቸት ይቻል ነበር::

በሀገራችን ግልፅ የሆነ የስፖርት ፖሊሲ የለም:: በልዩ ልዩ ስፖርት ዓይነቶች ነጻ በሆነ መንገድ ተደራጅተው የሚንቀሳቀሱ የስፖርት ድርጅቶች እንዲኖሩ የሚያስችል የፖሊሲ ማእቀፍ አልተፈጠረም:: የሀገሪቱ ስፖርት በክለቦችና በማህበራት ተደራጅቶ ሕዝባዊ መሰረት እንዲኖረውና በትብብር መርህ ላይ እንዲቆም በሚያስችል አቅጣጫ የተቃኘ ሳይሆን በጥቂት የውድድር ስፖርቶች ላይ ብቻ የተንጠለጠለ ነው:: ማስ ስፖርት በሰፊው ጥቅም ላይ ባለመዋሉ በዘርፉ በርካታ ስፖርተኞችን በየጊዜው ለማፍራትም ሆነ የስፖርት ፋሲሊቲዎችን በሕዝቡ ትብብር ለማሟላት አልተቻለም:: በጣት ከሚቆጠሩ ክለቦች፣ አሰልጣኞችና ዳኞች ጥረት በስተቀር ሕዝብን በሰፊው የሚያሳትፍ የስፖርት አደረጃጀትና አመራር ስለሌለ የስፖርቱ ዘርፍ ካለጠንካራ መሰረት የሚውተረተር፣ በአየር ላይ የተንሳፈፈ፣ ብልጭ ድርግም የሚልና ተከታታይነት የሌለው ነው::

ለማስ ስፖርትም ሆነ ለውድድር ስፖርት የሚሆኑ የማዘውተሪያ ቦታዎች፣ የስልጠና ማዕከሎችና ሌሎች ፋሲሊቲዎች አሉ ብሎ ለመናገር አይቻልም:: ዘርፉን መንግስት ሙሉ በሙሉ እንዲቆጣጠረው በመደረጉ ሕዝባዊ መሰረት ይዞ ሊገነባና ሊያድግ አልቻለም:: በየትኛውም የስፖርት ዘርፍ አህጉራዊና አለማቀፋዊ ወድድሮችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ምቹ ሁኔታ እስካሁን አልተፈጠረም:: ሌሎች የአፍሪካ ሀገሮች ከደረሱበት የስፖርት ክለቦች ምስረታና የማዘውተሪያ ስፍራዎች ግንባታ ደረጃ አንጻር ኢትዮጵያ ያለችበት ሁኔታ እጅግ ወደ ኋላ የቀረ ነው:: ለእግርና ለመረብ ኳስ፣ ለጠረጴዛና ሜዳ ቴኒስ፣ ለሞተርና ብስክሌት፣ ለፈረስ ግልቢያና ለዝላይ፣ ለውኃ ዋና፣ ለቅርጫትና እጅ ኳስ፣ ለሌሎች ዘመናዊና ባህላዊ ስፖርቶች መለማመጃና ማዘውተሪያ ቦታዎች በሀገሪቱ ውስጥ እንዳሉ በሚቆጠሩበት ሁኔታ ላይ አይደሉም:: ሕዝቡ ለስፖርት ያለው ስሜትና ፍላጎት ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገ ቢሆንም ይኸንን ፍላጎቱን የሚያረካ የስፖርት አገልግሎት ሊገኝ አልቻለም::

ለአካል ጉዳተኞች፣ በእድሜ ለገፉ አዛውንቶችና ሕፃናት በአቅማቸው መጠን የስፖርት እንቅስቃሴ የሚያደርጉበት አደረጃጀትና ስርዓት ጨርሶ የለም ለማየት ይቻላል:: በተወሰኑ ወቅቶች በቋሚነት እየተዘጋጁ ሕዝብ የሚሳተፍባቸው ልዩ ልዩ የስፖርት ፕሮግራሞች በሚገባ አልተዘረጉም:: ለፕሮፌሽናል ስፖርተኞች ስልጠናና ምክር የሚሰጡ የተደራጁ ማዕከላት የሉም:: በፕሮፌሽናል ስፖርት የሚወዳደሩ ስፖርተኞች ለሥልጠናና ለትጥቅ የሚያስፈልጋቸውን የፋይናንስ ወጪ የሚደግፉ የበጎ ፈቃድ ድርጅቶች እንዲመሰረቱ የሚያስችል በቂ ጥረት የለም:: ክለቦች ሕዝቡን በሚያሳትፉበት ሁኔታ አለመደራጀታቸው ብቻ ሳይሆን አንድ ክለብ የተለያየ ፍላጎትና ችሎታ ያላቸውን ሰዎች ለመሳብ በሚያስችል መንገድ ልዩ ልዩ የስፖርት ዓይነቶችን በሚያቅፉበት

መንገድ አልተቋቋሙም:: አንድ ክለብ እግር ኳስ፣ መረብ ካስ፣ ቅርጫት ኳስ፣ የሜዳና የጠረጴዛ ቴኒስ፣ ብስክሌት፣ ሩጫ፣ ዋና ወዘተ. የመሳሰሉትን አቅፎ እንዲይዝ ሆኖ ቢደራጅ የተለያየ ፍላጎት ያላቸው ሰዎች እንደየፍጎታቸው በክለቡ አባልነት ሊሳቡና ተገቢ ድጋፍ ሊሰጡ የሚችሉበት እድል ይኖራል::

የእግር ጉዞ፣ የቤት ውስጥና ከቤት ውጪ የሚካሄዱ የእረፍት ጊዜ ማሳለፊያዎችና ሌሎች የመዝናኛ ፕሮግራሞች ሕዝቡን በሚያሳትፍና ተከታታይነት ባለው ሁኔታ ተደራጅተው ተግባራዊ የሚሆኑበት ሁኔታ የለም:: በበዓላት፣ ከስራ ሰዓት ውጭና በዓመት እረፍት ጊዜ ሰዎች አየተዝናኑ ጊዜያቸውን ለማሳለፍ የሚችሉበት አደረጃጀትና አሰራር የለም:: ከስፖርት እንቅስቃሴ ሌላ የቤተመፃህፍት፣ የሙዚየም፣ የቲያትር፣ የሙዚቃ፣ የኤግዚቢሽን፣ ወዘተ. አገልግሎቶች ስላልተስፋፉ አብዛኛው ሰው ጤንነቱን በሚጎዳ መዝናኛና ጊዜ ማሳለፊያ ውስጥ እንዲገባ ይገደዳል::

ስለዚህ የስፖርትና መዝናኛ እንቅስቃሴ ሕዝባዊ መሰረት እንዲኖረው ከተፈለገ ክለቦች፣ ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና የበጎ ፈቃድ ቡድኖች በየደረጃው በሚገባ ተደራጅተው በሕዝቡ ውስጥ የሚንቀሳቀሱበትን እድል የሚፈጥር አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል:: አማተር ስፖርተኞችን ለመደገፍና ለፕሮፌሽናል ስፖርት መነሻ መሰረት እንዲሆኑ ለማድረግ በሚያስችል መንገድ እንዲደራጁና እንዲሰሩ ማድረግ ይገባል:: በመንግስት በኩል የስልጠና ማዕከላትን ለማደራጀት፣ የስፖርትና መዝናኛ ጥናትና ምርምር ስራዎችን ለመደገፍ፣ የስፖርት ማዘውተሪያና መዝናኛ ፋሲሊቲዎችን በሕዝብ ድጋፍ ለመገንባት፣ ብቁ አሰልጣኞች፣ ዳኞችና አማካሪዎች እንዲኖሩ ለማድረግ በሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ መሰራት አለበት:: ማስ ስፖርትና የቡድን ስፖርት እንዲጠናከር ከመደገፍ ጎን ለጎን ለፕሮፌሽናል ስፖርተኞችና ለውድድር ስፖርቶች ማደግ የሚያግዝ ሕግ ማውጣት፣ የቴክኒክና የፋይናንስ ድጋፍ ማድረግ፣ ለዚሁ ተግባር የሚሆን ልዩ ልዩ ደጋፍና እርዳታ ከውስጥና ከውጭ የሚገኝበትን ሁኔታ ማስተባበር ይኖርበታል:: አህጉራዊና አለም አቀፋዊ ውድድሮችን ሀገሪቱ ለማዘጋጀት እንድትችል የሚረዳ መሰረተ ልማት በመገንባትና ውጤታማ የዲፕሎማሲ ስራ በመስራት የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለዓለም ሕብረተሰብ ለማሳየትም ሆነ የኢኮኖሚ ግንባታውን የሚደግፍ ገቢ ለማግኘት በሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫ መመራት ይገባዋል:: በስፖርትና መዝናኛ መስክ መንግስት በፌዴራልና በክልል ደረጃ የሚሰራው ሰፊ ተግባር መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ የተለያዩ የልማት ተቋሞች፣ ማህበራት፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችና ተቋሞች የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ግለሰቦች በዚህ መስክ ሰፊ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ያስፈልጋል:: ለዚህ ጠቃሚው አማራጭ የስፖርትና መዝናኛ እንቅስቃሴዎችን መንግስት በብቸኝነት የሚመራበትን አደረጃጀት በመለወጥ ሕዝባዊ ተሳትፎን በሚያስገኝና ከመንግስት ቀጥተኛ ቁጥጥርና ተፅዕኖ ነጻ በሆነ መንገድ እንዲደራጅና እንዲሰራ ማድረግ ነው::

# 10. ሥነ ጥበብ፣ ሙዚየምና ኤግዚቢሽን

በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በዋሻዎች፣ በሀውልቶች፣ በሥነ ሕንፃዎችና በሌሎችም ተጨባጭ ማስረጃዎች የተረጋገጠና ለረጅም ጊዜ የቆየ የሥነ ጥበብ ስራ እንደነበር የሚታወቅ ነው:: ይሁን እንጂ በማንኛውም መስክ እንደታየው በዚህም ረገድ ሀገሪቱ እንደአጀማመሯ መሪ ሚና ለመጫወት ወደሚያስችል እድገት ለመራመድ ሳትችል ቀርታለች:: በዚህ መስክ የሚታየው አዝጋሚነት ደግሞ በሌሎች መስኮች ከታየውም የባሰ ነው:: ስነጥበብ አሁን በመላው ዓለም ከደረሰበት የእድገት ደረጃ አንፃር ሲመዘን የኢትዮጵያ ሁኔታ ከቀድሞው አሰራር ብዙም ርቆ ለመጓዝ አልታደለም:: የስነጥበብ ሰዎች ለማፍራት የሚያስችል ተገቢ ጥረት በየወቅቱ ባለመደረጉ የዘርፉ ወደኋላ መጎተት እንዲመጣ ታስቦና ተፈልጎ የመጣ መምሰሉ ሊያስገርም አይችልም:: አንድ ለአናቱ» የሚል ስም ያለው ብቸኛ የስነጥበብ ትምህርት ቤት ከተወሰኑ አስርት ዓመታት በፊት በአዲስ አበባ ተከፈቶ የነበረ ቢሆንም የሚገባው ድጋፍ ሳይደረግለት እንደገባህ ውጣው ስለተባለ የሀገሪቱን ስነጥበብ በዓለም ደረጃ ብቁና ተወዳዳሪ ሆኖ እንዲገኝ ለማድረግ ሳይቻለው ቀረ:: ከዚሁ ትምህርት ቤት የወጡ፣ በውጭ ትምህርት ቤቶች የተማሩና በግል ጥረታቸውም የስነጥበብ ችሎታ ያዳበሩ ባለሞያዎች ሁሉም ባይሆኑም እንኳ አንዳንዶቹ አስደናቂ የጥበብ ስራ ሰርተው ማውጣት ቢችሉም የድካማቸውን ፍሬ አላገኙም:: ሞያውን በሰፊው ለማሳደግ በሚያስችል ደረጃ የተደራጀ ጠንካራ የስነ ጥበብ አካዳሚ ሳይኖር፣ የስነጥበብ ውጤቶች ለእይታ የሚቀርቡበት ሙዚየም፣ ጋለሪ፣ ኤግዚቢሽን ወዘተ. ሳይኖር ዝም ብሎ ያደገና በዓለም ደረጃ ብቁ ተወዳዳሪ መሆን የቻለ ስነ ጥበብ የለም:: የመንግስትና የሕዝብ ድጋፍ ሳይታከልበት አብቦ ያፈራ

የስነ ጥበብ ስራ በዓለም ታሪክ ውስጥ አልተመዘገበም፡፡ የኢትዮጵያ ስነጥበብ በመስኩ ከተሰለፉ ጥቂት አብሪ ኮከብ የሆኑ ዜጎች ብርታትና ጥረት በስተቀር ትርጉም ያለው ድጋፍ ከየትም ወገን ሳያገኝ የቀረና የተረሳ ዘርፍ ነው፡፡

ይኸንን ዘርፍ ለማነቃቃት መሰረታዊ የፖሊሲ ለውጥ ማምጣት ይጠይቃል፡፡ በመጀመሪያ ደረጃ ዘርፉ የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለማሳየትና ቱሪስቶችን ለመሳብ ከሚያስችሉን ጠቃሚ ነገሮች መካከል እንደ አንድና ዋነኛው በመቁጠር በመንግስት የልማት አጀንዳ ውስጥ እንዲካተት መደረግ አለበት፡፡ እንደትርፍ ስራና በአመቺ ጊዜ ብቻ እንደሚሰራ ተግባር ወይንም ለፕሮፓጋንዳ ፍጆታ ሲባል እንደሚንጠለጠል መፈክር መታየቱ መቅረት አለበት፡፡ በዚህ መስክ ሀገራቸውንና ራሳቸውን ሊጠቅሙ የሚችሉ እጅግ ብዙ የጥበብ ሰዎችን ለማፍራት የሚያስችል ጠንካራ የሥነጥበብ አካዳሚ ራሱን በቻለ መንገድ ማቋቋም ያስፈልጋል፡፡ የዚህ ዓይነቱ የጥበብ አካዳሚ መኖር የሥነጥበብ ሞያተኞችን የሚያፈራ ብቻ ሳይሆን ከዓለም የሥነጥበብ ስራ ጋር የሚያስተሳስር፣ ለሥነጥበብ ስራ ውጤቶች ማሳያ የሚሆኑ የጋለሪዎችና የኤግዚቪሽኖች ፋሲሊቲ የሚፈጥር፣ የጥበብ ሰዎች በምርምር፣ በጋለሪና በኤግዚቪሽን ፋሲሊቲ እጥረት የሚያጋጥማቸውን የፋይናንስና የሥነልቦና ጭንቀት ለማቃለል ጭምር ያገለግላል፡፡ ከዚህ ሌላ የመንግስት ተቋሞች፣ የግል ኩባንያዎች ማህበራትና መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለሚያካሂዱት የግንባታ ስራ ከሚመድቡት ወጪ የተወሰነውን መጠን ለጥበብ ስራ የሚመድቡበትን አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል፡፡ በብዙ ሚሊዮን ወጪ የተገነባ ግዙፍ ሕንፃ በከፊል የሰዓሊዎች ጥበብ እንዲያርፍበት ተደርጎ ካልተዋበና የጥበብ ስራ ካላጌጠና ዝም ብሎ ከተቀመጠ ከቋጥኝ የተለየ ሊሆን አይችልም፡፡ የተመልካቾችን ስሜት የሚማርክና ቀልብ የሚገዛ ውበት አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ከግንባታዎች ውስጥ የተወሰነውን ገጽ ወይም ኮሪደር በሰዓሊዎች ስራ እንዲያጌጥ ገንዘብ መመደብና በጥበብ ሰዎች የድካማቸውን ዋጋ መክፈል ጥበቡን የሚያሳድግ አንድ መንገድ ተደርጎ መወሰድ አለበት፡፡

የጥበብ ውጤቶች ለእይታ የሚቀርቡባቸው ሙዚየሞችን በፌዴራል ደረጃ ብቻ ሳይሆን በክልሎችና በአካባቢ ደረጃ መክፈት ያስፈልጋል፡፡ ይህ ዘዴ የጥበብ ሰዎችን ማለትም የሰዓሊዎችንና የቀራጺዎችን የስራ ውጤት ለማሳወቅ ከመርዳቱም በተጨማሪ የቱሪስት መስህብም ሆኖ ያገለግላል፡፡ ሙዚየሞች ለሥነጥበብ ማሳያ ብቻ ሳይሆን ለታሪክ፣ ለባህል፣ ለአንትሮፖሎጂ፣ ለሳይንስና ለሌሎች መስኮችም ማስተዋወቂያ ሆነው የሚያገለግሉ ናቸው፡፡ በተለያየ መስክ ምርምርና ጥናት ለሚሰሩ ተቋሞችና ግለሰቦችም ያገለግላሉ፡፡ የታሪክና የባህል ቅርሶችን፣ የሥነጥበብና የምርምር ውጤቶችን ለመመዝገብ፣ ለመጠበቅና ለእይታ ክፍት ለማድረግ ያገለግላሉ፡፡ እነዚህ ተቋሞች በመንግስት ብቻ ሳይሆን በባለሀብቶች፣ በግል ኩባንያዎችና በኃይማኖት ድርጅቶች፣ በሕዝብ ዋና ዋና ማህበራትም ሊስፋፉ የሚችሉ ናቸው፡፡ ለሁሉም የሥነጥበብ መስኮችና ለስዕል፣ ለቅርፃ ቅርፅ፣ ለህውልትና ለመሳሰሉት ለሁሉም ዓይነት እንቅስቃሴዎች የሚያገለግሉ ሙዚየሞች በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች በማቋቋም ሁሉንም የሀገሪቱን መልካም ገጽታ ለሁሉም ተመልካች እንዲቀርብ የሚያደርግ አሰራር መከተል ተገቢ ነው፡፡

የሥነጥበብ ውጤቶች ለዕይታ የሚቀርቡባቸው ጋለሪዎች በየስፍራው እንዲቋቋሙ፣ ቢያንስ በየ5 ዓመቱ የሚዘጋጅ ዓለም አቀፍ ኤግዚቢሽን ማሳያ ማዕከልና ከዚያም ባነሰ ጊዜ ለሀገር ተመልካቾች የሚዘጋጁ ኤግዚቢሽኖች የሚቀርቡባቸው ማዕከላት በየስፍራው እንዲደራጁ መንግስት፣ የግል ኩባንያዎች፣ ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ድጋፍ የሚያደርጉበት ሁኔታ መኖር አለበት፡፡ ሙዚየሞች ለጋለሪዎችና ለኤግዚቪሽኖች ዝግጅት ስፖንሰር በመሆን ሊደግፉ የሚችሉበት አቅጣጫ መኖር አለበት፡፡ የጥበብ ሰዎች በአለም አቀፍ ኤግዚቪሽኖች ለመካፈል የሚያጋጥማቸው የቪዛ፣ የፋይናንስና የቢሮክራሲ ማነቆ እንዳይኖር መንግስት የተለየ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡

የሥነጥበብ ሰዎች ሽልማትና ማበረታቻ የሚያገኙበትን አሰራር በመከተል መንግስት የግል ኩባንያዎችና ሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ተባብረው እንዲሰሩ ማድረግ ይገባል፡፡ በግላቸው ሙዚየም፣ ጋለሪና ኤግዚቢሽን ለማቋቋም ለሚፈልጉ መሬት፣ የቀረጥ ቅነሳና ብድር በመስጠት መንግስት መደገፍ አለበት፡፡

ከስነ-ጥበብ ጋር የተያያዙ ከውጭ የሚገቡ እቃዎችን በአነስተኛ ቀረጥ እንዲያስገቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሊጠቀስ የሚገባው ዋናው መሰረታዊ ጉዳይ የስነ ጥበብ ሰዎች የደከሙበትና ፈጠራቸው የሆነው ስራ ሁሉ የሌሎች መጠቀሚያ እንዳይሆን የሚያስችል የባለቤትነት መብት ፖሊሲና ጠንካራ የቁጥጥር ስልት ሊኖር ይገባል፡፡

# 11. ሥነ-ጽሑፍና ቤተመጽሐፍት

*ኢትዮጵያ የራሷ ቋንቋና ፊደል ያላት ሀገር መሆኗ የታወቀ ነው:: የዚህ ዓይነት እድል ያላቸው ሀገሮች በአፍሪካ ቀርቶ በዓለም ደረጃም እንኳ በጣም ብዙ የሚባሉ አይደሉም::*

*ምንም እንኳ የራሷ ፊደልና ቋንቋ ያላት ሀገር መሆኗ የመልካም ታሪኳ አንድ አካል ቢሆንም በሥነጽሑፍ ዘርፍ ዓለም ከደረሰበት ከፍተኛ የእድገት ደረጃ እጅግ ወደኋላ መቅረቷ አስገራሚ ነው:: ረዘም ያለ እድሜ ያለው የሥነጽሑፍ ስራ ሲከናወን የነበረው በቤተክህነት አካባቢ ብቻ ስለነበር ከዚህ አጥር ወጥቶ በሰፊው ለማደግ ሳይችል ቆይቷል:: ስራው ከሃይኖማት ጋር መያያዙ ብቻ ሳይሆን ቆዳ ፍቆ፣ የመቃ ብዕር ቀርጾ፣ ከቅጠላ ቅጠልና ስራ ስር የተጨመቀ ቀለም አዘጋጅቶ ወዘተ. በሰው ኃይል ብቻ የሚከናወን ስለነበር እጅግ አድካሚ፣ ጊዜ አባካኝና በጥራትም ሆነ በብዛት ደረጃ እንደተፈለገው ማምረት የማይችል ስለነበር ጭምር ነው:: በእርግጥ ለዘመናዊው የሀገራችን ሥነፅሑፍ ያበረከተው አስተዋፅኦ መኖሩ የማይካድ ነው:: ዘመናዊ ስነፅሑፍ በሀገራችን የተጀመረበት ዘመን ረጅም የሚባል አይደለም:: ከተጀመረም በኋላ እድገትና መሻሻል ማሳየቱ ባይቀርም ፈጣን በሆነ ደረጃ የታየ እድገት ነው ለማለት ግን አይቻልም::*

*በሀገር ቋንቋ የተፃፉ ስነፅሑፎች በቁጥርም ሆነ በይዞታቸው ውስን ናቸው:: በአማርኛ፣ በኦሮሚኛ፣ በትግርኛ፣ በጉራጊኛና በሌሎችም የሀገር ቋንቋዎች የተዘጋጁ የሥነጽሑፍ ስራዎች ቢኖሩም ከኢትዮጵያ ኋላ ተነስተው ሥነጽሑፍ የጀመሩ ብዙ የአፍሪካ ሀገሮች ከደረሱበት ደረጃ ጋር እንኳ የሚቀራረብ አይደለም:: በሀገር ቋንቋ ከተሰሩት ሥነፅሑፎች መካከል በታሪክ፣ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊና ባህላዊ መስክ የሚያተኩሩት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው:: በሀገር ፍቅር ስሜት፣ በተለያዩ የሳይንስ እውቀትና የትምህርት ዘርፎች ላይ ያተኮሩ ስራዎችም ተሰርተዋል:: አጫጭር ታሪኮች፣ ልቦለዶችና ጭውውቶችም በተወሰነ ደረጃ በሥነፅሥሑፍ መልክ ቀርበዋል:: ከውጭ ቋንቋ ወደ ሀገር ቋንቋ የተተረጎሙ ስነፅሑፎች አሉ:: በሀገር ቋንቋ ከተሰሩ ወጥ ስራዎችም ሆነ ከትርጉም ስራዎች መካከል ስነፅሑፋዊ ውበት አላቸው የሚባሉት የተወሰኑት ብቻ ናቸው:: እንዲሁም የማስተማር የማሳወቅና የማዝናናት ተልዕኳቸውን በመወጣት ተገቢውን ማህበራዊ ተግባር መፈፀም የቻሉት ጥቂቶቹ ብቻ ናቸው:: በቲያትርና በግጥም መልክ የቀረቡ የሥነፅሑፍ ስራዎች አስተዋፅኦም ያንኑ ያህል የተወሰነ ነው::*

*ለሥነፅሑፍ እድገት መጓተት በርካታ ምክንያቶች ቢኖሩም ዋነኛው የመፃፍ ነፃነት የሚያከብርና ለሥነፅሑፍ እድገት አመቺ የሆነ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት አለመኖሩ ነው:: ከዚሁ ስርዓት አለመኖሩ ጋር በተያያዘ ሁኔታ ሕዝቡ ከመሃይምነት ጨለማና ከድህነት የሚወጣበት እድል በመጥፋቱ ለሥነፅሑፍ ፈጣን እድገት የተመቻቸ መድረክ አልተፈጠረም:: ቁጥራቸው አነስተኛ የሆኑና በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ዘመናዊ ትምህርት የቀሰሙ፣ በግል ጥረታቸውና ታታሪነታቸው አስደናቂ ችሎታ ያዳበሩ ዓለም አቀፍ ዝና ያገኙ የሥነጽሑፍ ሰዎች አልፎ አልፎ ብቅ ቢሉም በነፃነት መንፈስ የሚሰሩበት አመቺ ሁኔታ ባለመኖሩ የሚገባውን ያህል ለመስራት አልቻሉም:: ለሥነፅሑፍ የተመቻቸ ሁኔታ በሀገሪቱ ሊፈጠር አለመቻሉ አንድ ዋነኛ ችግር ሆኖ የሥነፅሑፍ ስራ በባህርይው እውነታን ለማብላላትና ስነፅሑፋዊ ውበት እንዲኖረው ለማድረግ ረጅም ጊዜ የሚወስድ በመሆኑ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፈጣን እድገት ለማምጣት ያስቸግራል:: ከደራሲዎች ቁጥር ማነስ በተጨማሪ ያሉትንም ሞራልና የስራ ተነሳሽነት የሚያሳድግ የመንግስት ፖሊሲ ባለመኖሩ የቻሉት አገር ጥለው ለመሰደድ ያልቻሉት ደግሞ ሳይወዱ በግድ ኑሮን ለማሸነፍ ያመቻል ወደሚሉት ሌላ የስራ መስክ ለመግባት ይወሰናሉ::*

*የሥነፅሑፍ ስራ በሀገራችን እንዳይጠናከር ያደረገው ሌላ ነጥብ ጥራትና ብቃት ያላቸው፣ ከመንግስት ተፅዕኖና ቁጥጥር ነፃ የሆኑ አሳታሚዎችና የሕትመት ድርጅቶች አለመኖራቸው ነው:: ቀድሞም ሆነ አሁን ይኸ ስራ በመንግስት ሞኖፖል የተያዘ ነው:: ከ1966ቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ በኋላ በሚያስገርም ፍጥነት ተነቃቅቶ የነበረው የስነፅሑፍና የሕትመት ስራ በመንግስት የሚደርስበት ቁጥጥርና ጫና ከጊዜ ወደጊዜ እየተጠናከረ በመሄዱ መልሶ ወደ ውድቀት ጎዳና እያመራ ነው:: አሁን ያለው ሁኔታ ደግሞ የባሰበት ነው:: ይኸንን የውድቀት ጉዞ የሚከታተሉ አንዳንድ ሰዎች የችግሩን መንስኤ ከደራሲዎች ፍላጎት ማጣት፣ ከማሳተሚያ ድርጅቶች ጉድለት፣ ከሕትመት ዋጋ መናር፣ ከገበያ መጥፋት፣ ከሕዝቡ የንባብ ፍላጎት መቀነስ ወዘተ. ከመሳሰሉት*

ነጠላ ጉዳዮች ጋር ለማያያዝ ይሞክራሉ። በእርግጥ እነዚህ የተባሉት ችግሮች ሁሉ በእርግጥም ያሉና የሚታወቁ መሆናቸው እውነት ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ ግልፅ ተደርጎ የማይቀርበው ነጥብ እነዚህ ሆን ተብለው የተፈጠሩና በመንግስት ፖሊሲ የሚደገፉ ችግሮች የመሆናቸው ነገር ነው። በአሁኑ ጊዜ እንዲጻፍ የሚፈለጉትና የመንግስት ልዩ እርዳታ የሚደረግላቸው ጽሑፎች እውነታን ክሪቲካል በሆነ መንገድ የሚገልጹና ሥነጽሑፋዊ ውበት ያላቸው ስራዎች አይደሉም። «ተራሮችን ያንቀጠቀጠ ትውልድ» እንደሚለው ዓይነት ትምህርትም እውነትም የማይገኝባቸውና ሥነጽሑፋዊ ውበት የሌላቸው የፕሮፓጋንዳ መድብሎች ናቸው። እንደነዚህ ዓይነቶቹ ስራዎች አንባቢ ወደዳቸው ወይም ጠላቸው ተብሎ የሚጨነቁላቸው አይደሉም። በግዳጅና በኮታ ለየመስሪያ ቤቱና ለየድርጅቱ እየታደሉ እንዲሸጡ መንግስት ሁኔታዎችን ያመቻቻል። የማተሚያ ቤቶችና አሳታሚ ድርጅቶችም እንደነዚህ ዓይነቶቹን ስራዎች አትሞ ለማውጣት ሊያንገራግሩ አይችሉም። በመንግስት ቁጥጥር ስር ስለሆኑ የሚደርሰውን ኪሳራና ድካም ሁሉ ችለው እንዲህ ዓይነቶቹን ስራዎች አትሞ ማውጣት ይኖርባቸዋል።

የአሳታሚነት ስራ ከመንግስት ሞኖፖሊነት በተጨማሪ በገዥው ፓርቲ ሞኖፖሊ ስር የወደቀ ነው። ሜጋ አሳታሚ ድርጅት የሚባለው የሕወሓት/ኢህአዴግ ተቋም ከፍተኛ የፋይናንስ፣ የማስታወቂያ፣ የቴክኒዎሎጂና የስርጭት አቅም እንዲገነባ በመንግስት ልዩ ድጋፍ ስለተደረገለት ሌሎች የግል አሳታሚዎች ከጨዋታ ውጭ ሆነዋል። ይባስ ብሎ በየወቅቱ የወረቀትና የማተሚያ ዋጋ እንዲጨምር በመንግስት በመወሰኑ ተወዳድረው ለመስራት ይቅርና እየተንገዳገዱ ጊዜ ለመግዛት እንኳ በማይችሉበት ሁኔታ ውስጥ ወድቀዋል።

ሜጋ አሳታሚ ድርጅት በመንግስት ልዩ ድጋፍ ሁለገብ አቅም መገንባቱ ብቻ ሳይሆን የራሱ ባልሆነና በተነጠቀ ገንዘብ፣ ቁሳቁስና ጽህፈት ቤት የተመሰረተ በመሆኑ የሚፈራው ኪሳራ የለም። የግል ባለሀብቶች ደግሞ ወጥተው ወርደው በላባቸው ያገኙትን ካፒታል ኢንቨስት ያደረጉ በመሆናቸው አላስፈላጊ ኪሳራ እንዳይኖር መስጋታቸው የተገባ ነው። አሁን የአሳታሚነት ስራ በገበያ ውድድር ስርዓት የሚመራ ሳይሆን በተነጠቀ ንብረትና በግል ንብረት መካከል የሚካሄድ ነው። ሜጋ አሳታሚ ድርጅት ባለፈው መንግስት ቁጥጥር ስር የነበረውን የኩራዝ አሳታሚ ድርጅት ከሕግ ውጪ የሕወሓት/ኢህአዴግ ንብረት እንዲሆን በማድረግ የተመሰረተ ነው። የራሱ ባልሆነ ሀብትና ንብረት ተመስርቶ እንዲሁም በመንግስት ልዩ እርዳታና እንክብካቤ ከሚሰራ ጉልበተኛ ጋር በነጻ የገበያ ስርዓት መወዳደር ብሎ ነገር የለም። የግል አሳታሚዎችን ብቻ ሳይሆን የመንግስት አሳታሚዎችንም ስራ ጠቅልሎ እንዲይዝ ፈቃድ በማግኘቱ በትምህርት መሳሪያዎች ማምረቻ ተቋም ይታተሙ የነበሩት የተማሪዎች መሳሪያ መፃህፍት እንኳ ሳይቀር በሜጋ እየታተሙ በውድ ዋጋ ለሕዝቡ ይቀርባሉ። ከውጭ የሚገቡ መፃሕፍትና መጽሔቶችን የማስገባቱንና በሀገር ውስጥ የማሰራጨቱንም ተግባር ሜጋ ጠቅልሎ እንዲይዘው ተደርጓል። በመንግስት ሬዲዮና ቴሌቪዥን እንደፈለገው የማስታወቂያ ሽፋን የሚሰጠው ሜጋ አሳታሚ ሁሉንም እድሎች ከሌሎች በበለጠ መንገድ እንዲያገኝ ከመንግስት በኩል ሙሉ ድጋፍ ሲሰጠው ሌሎቹ ደግሞ በፖሊሲና በቢሮክራሲ ማነቆ አናት አናታቸውን ይኮረኮማሉ።

ከዚህ ሌላ የቤተመጽሀፍት አገልግሎት ከጊዜ ወደጊዜ እየተዳከመ መምጣት ለሥነጽሑፍ ፈጣን እድገት አለመታየት አንደኛው እንቅፋት እየሆነ ነው። ጠንካራ የደራሲዎችና የአሳታሚዎች ማህበራት እንዲደራጁ በመንግስት በኩል የሚደረግ ድጋፍና ማበረታታት ስለሌለ በደራሲነትና በአሳታሚነት ስራ የተሰማሩ ወገኖች ተባብረው የመንግስት ፖሊሲ ለውጥ እንዲፈጠር ለማድረግ የሚያስችል የተደራጀ አቅም አልፈጠሩም።

ስለዚህ በዚህ ዘርፍ ያለውን ችግር ለማቃለል የሚያስችል ፖሊሲ ያስፈልጋል። ደራሲዎችንና የግል አሳታሚዎችን በነፃነት እንዲደራጁና ለዘርፉ እድገት ጠቃሚ አስተዋጽኦ እንዲያደርጉ የመንግስት ተፅዕኖንና ጣልቃ ገብነትን የሚያስቀር የፖሊሲ አቅጣጫ መኖር አለበት። ለደራሲዎች ማበረታቻ በመስጠት ሞራላቸውና የስራ ተነሳሽነታቸው እንዲነቃቃ የሚያደፋፍር አሰራር መኖር አለበት። የገዥው ፓርቲ ንብረት እንዲሆን የተደረገው የሜጋ አሳታሚ ድርጅት የሕግን አግባብ በተከተለ መንገድ ንብረቱ ሁሉ ወደመንግስት ግምጃ ቤት ተመላሽ እንዲሆንና ለአንድ ፖለቲካ ድርጅት ባለስልጣኖች መጠቀሚያ መሆኑ ቀርቶ ለሀገር ልማትና ለሕዝቡ የጋራ ጥቅም እንዲውል መደረግ አለበት። ወይንም በግልጽ ጨረታ ወደግል ንብረትነት መዛወር ይኖርበታል። የሕትመት፣ የማስታወቂያና የስርጭት ስራ በገበያ ሕግ እንዲገዛ መደረግ አለበት። ለደራሲዎችና

ለአሳታሚዎች ስራ ማነቆ የሆነውን የወረቀትና የሕትመት ዋጋ በገበያ ሁኔታ እንዲረጋጋ እድል መስጠትና በዚህ መስክ የመንግስትን ሞኖፖሊ ስልጣን በመቀነስ ስነጽሑፍ እንዲያድግ መደረግ አለበት። በትምህርት ተቋሞች፣ በመንግስትና በግል ድርጅቶች፣ በኃይማኖት ድርጅቶች፣ በሕዝባዊና በሞያ ማህበራት፣ በሰራተኛ ማህበራት፣ በንግድ ማህበራት ወዘተ. ቤተመፃህፍቶችና የንባብ ክለቦች እንዲስፋፉ የሚያስችል አሰራር መስፈን አለበት።

# 12. ሙዚቃ፣ ቲያትር፣ ሲኒማና ፌስቲቫል

የሀገራችን ሙዚቃ ባህላዊውን ገጽታ እንደጠበቀ ለረጅም ጊዜ የቆየ ቢሆንም ከተወሰኑ አስርተ ዓመታት ወዲህ በዘመናዊ ሙዚቃ መታጀብ ጀምሯል። ሁለቱንም ጎን ለጎን ማስኬድ የሚጠላ ነገር አይደለም። ከፍተኛ ችግር የሚፈጠረው ባህላዊውንም በአግባቡ መጠበቅ ወይንም ዘመናዊውንም በአግባቡ መጨበጥ የማይቻልበት ሁኔታ ከተፈጠረ ነው። በአንድ በኩል ነባሩን ጨርሶ መጥላትና መርሳት በሌላ በኩል አዲሱን ከሚገባው በላይ ማምለክ ከመጣ የራሳችን የምንለውና ለሌላው የምናበረክተው ነገር ማጣት ይመጣል። የራሳችንን ክብርና መልካም ነገር እየናቅን የእኛ ባልሆነው የተውሶ ጌጥ ወደመብለጭለጭ እናመራለን። ይህ አዝማሚያ በሀገራችን አልተጀመረም የሚባል አይደለም።

ስለዚህ ሙዚቃ እንዲያድግ ስንፈልግ በነበረንና ወደፊት እንዲኖረን በምንመኘው መካከል የሚፈጠረውን ቅራኔ አንዳንድ ጊዜ በቀድሞው ትውልድና በአዲሱ ትውልድ መካከል የሚፈጠር ቅራኔ እንደሆነ አድርገው የሚመለከቱ ሰዎች አሉ። ወይም እያረጀ በሚሄደው ነባር ባህልና እያደገ በሚመጣው አዲስ ባህል መካከል የሚከሰት ግጭት አድርገው የሚመለከቱም አሉ። ዞሮ ዞሮ የዛሬው በትናንቱ፣ የነገው ደግሞ በዛሬው ላይ እየተገነባ የሚጓዝ የቅብብሎሽ ጉዞ እንደመሆኑ ካለፈው መልካም የሆነውን ጠብቀን አዲስ ነገር እየጨመርን መሄድ ይገባናል። ካለፈው ሁሉም የሚወደድ ወይም ሁሉም የሚጠላ ባለመሆኑ የሚወደደውን መርጦ መጠበቅ የሙዚቃ እርምጃችን ሊከተለው የሚገባ አቅጣጫ ነው። ባለፈው ነገር ተወስነን መቀመጥ ደግሞ ከሰው ልጅ ተለዋዋጭ ፍላጎትና የአስተሳሰብ እድገት ጋር የማይጣጣም እንደመሆኑ በአዳዲስ ፈጠራ ማጀብና ማበልፀግ አሁንም የሙዚቃ እርምጃችን የሚጓዝበት መንገድ መሆን አለበት።

ለዚህ ዓላማ መሳካት የሚያገለግሉ የሙዚቃ ማሰልጠኛዎች በመንግስትና በግል የሚስፋፉበትን አቅጣጫ መተለም ይገባል። ትምህርት ቤቶች ታሪኮቻቸውን ከባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ መሣሪያዎች ጋር የሚያስተዋውቁበት አሰራር እንዲኖር በስርዓተ ትምህርቱ ውስጥ መካተት ይኖርበታል። የሙዚቃ ትርኢት የሚቀርብባቸው ማዕከላት በከተሞችና በየአካባቢው እንዲፈጠሩ ማድረግ ይገባል። ሀገራችን የተለያዩ ባህሎች ሙዚየም እንደመሆኗ ለሁሉም ባህላዊ ሙዚቃዎች እድገት የሚያመቹ ማዕከላትን በየአካባቢው ማቋቋም፣ በትምህርት ቤት የሚሰጠውንም የሙዚቃ ትምህርት ከየባህሉ ጋር በሚጣጣም መንገድ ማከናወን ይገባል። ችሎታ ያላቸው ወጣት ሙዚቀኞችን ለማስተዋወቅ የሚያግዙ ውድድሮችን ማድረግ፣ ለሀገራችን ሙዚቃ መሻሻልና በዓለም ደረጃም ተቀባይነት ማግኘት የሚያግዙ የሙዚቃ ፌስቲቫሎችን በየዓመቱ በፌዴራል፣ በክልልና በአካባቢ ደረጃ ማዘጋጀት፣ በዓለም አቀፍ የሙዚቃ ፌስቲቫሎች ላይ ተሳትፎ ማድረግ ያስፈልጋል። እንደዚህ ባሉ መድረኮች ተሳትፎ ማድረግና ከአርቲስቶች ጋር የልምድ ልውውጥ ማካሄድ የሀገሪቱን ገጽታ በመልካም አቀራረብ ለማሳየት ከማስቻሉም በላይ በሙዚቃ ሞያ ለተሰማሩ ሰዎች እውቅናና ዝና ያግዛል። በአጠቃላይ ለሙዚቃው እድገት የሚረዳ ዓለም አቀፍ ተባባሪና አጋር ለመፍጠር ያስችላል። ፕሮፌሽናል ሙዚቀኞች ማፍራት እንዲቻል በሀገር ውስጥ ከሚሰጠው ስልጠና በተጨማሪ የውጭ ትምህርት እድል የሚገኝበትን ሁኔታ ማመቻቸት ተገቢ ነው።

በባህላዊና ዘመናዊ ሙዚቃ የተሰማሩ ሰዎች የሚያወጡትን ስራ በሕገወጥ መንገድ እያባዙ በመሸጥ ኪነጥበባዊ ውበቱን የሚያበላሹና የሙዚቀኞቹን ድካም መና የሚያስቀሩ የኪነጥበብ ስርቆቶች በሕግ የሚከላከሉበት ስርዓት ማውጣት ይገባል። የፈጠራ ባለቤትነት መብት ሕግ ተግባራዊ እንዲሆን ማድረግና የኪነጥበብ ስራቸውን የተሰረቁ ወይም ኪነጥበባዊ ውበቱንና ዋጋውን እንዲያጣ በደል የተፈፀመባቸው ሰዎች በሕግ የሚካሱበትን ስርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። በዚህ ሞያ ለተሰማሩ ሰዎች የማበረታቻ ሽልማትና ልዩ ልዩ ድጋፎችን እንዲያገኙ በመንግስት፣ በግል

ኩባንያዎችና በሌሎች መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች አማካኝነት ጥረት ማድረግ ይገባል፡፡ በዘርፉ የተሰማሩ ሰዎች ሞያቸውን ለማዳበር የሚረዳ የተቀናጀ አስተዋፅኦ ማድረግ እንዲችሉ የራሳቸውን ነጻ ማህበር መመስረት ይገባቸዋል፡፡ የኪነጥበብ ሥራዎቻቸውን የሚያሳትሙ፣ የሚያስተዋውቁና የሚያሰራጩ ጠንካራ የግል ኩባንያዎች የሚፈጠሩበትን አቅጣጫ መከተል ይገባል፡፡

በሀገራችን የቲያትር ጥበብ በዘመናዊ መልክ መድረክ ላይ መውጣት ከጀመረ ረጅም ጊዜ ባይሆነውም በዚህች አጭር እድሜው አያሌ መውደቅና መነሳት አጋጥሞታል፡፡ የቲያትር ጥበብ ለእይታ የሚቀርብበት ፋሲሊቲ በሁሉም የሀገሪቱ ክልሎች ሊሟላ ቀርቶ በአዲስ አበባ እንኳ በበቂ ሁኔታ የተዘጋጀ ተቋም የለም፡፡ አዲስ አበባ ያሉት ቲያትር ቤቶች ከተመልካቹ ብዛት ጋር የማይመጣጠኑ መሆናቸው ብቻ ሳይሆን ሌሎች ተጓዳኝ አገልገሎቶች የማይቀርቡባቸውና ምቾት የጎደላቸው ናቸው፡፡ ሁሉም በመንግስት ቁጥጥርና ተፅዕኖ ስር የወደቁ በመሆናቸው የቲያትር ጥበብ የሚፈልገውን ነጻነትና እርጋታ የሚነፍጉ ናቸው፡፡ በየጊዜው በተለያየ መንገድ ለሚካሄድ ሴንሰር ሽፕ የተጋለጡ ናቸው፡፡ በማያላውስ ኋላቀር ቢሮክራሲያዊ አሰራር የተቀየሱ ናቸው፡፡ የቲያትር ጥበብ ለተመልካቹ እርካታን በሚያስገኝና ለተቋሙና ለሞያተኞቹ ጠንካራ የኢኮኖሚ ምንጭ በሚሆን ደረጃ እንዳያድግ እንቅፋት በሆኑ አሰራሮች የታጠሩ ናቸው፡፡ በሌሎች የሀገሪቱ ክልሎች ያለው ሁኔታ ደግሞ ጨርሶ የባሰበት ነው፡፡ በካድሬዎችና በባለሥልጣኖች ትዕዛዝ የሚዘጋጁ ፖለቲካዊ ቀልዶችና ትዕይንቶች ካልሆኑ በስተቀር አማተር የቲያትር ሰዎች በነፃነት የፈጠራ ስራቸውን የሚያቀርቡበት እድል የተዘጋ ነው፡፡ ከአዲስ አበባ ቲያትር ቤቶች ወደ ክልል ከተሞች ሄደው ቲያትር በሚያሳዩበት ጊዜ የአካባቢው ካድሬዎች የሚያነሱት ጦርነትና የሚፈጥሩት ሽብር ከፍተኛ ነው፡፡ አንዳንድ የቲያትር ደራሲዎችና አዘጋጆች ግድያ፣ እስራት፣ ግርፋት፣ ከስራ መባረር፣ ስደትና ሌላም ዓይነት ግፍ ተፈፅሞባቸዋል፡፡ በሕዝቡ የሚወደዱና የሚከበሩ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ መልካም ስም ያገኙና የተሸለሙ የቲያትር ጥበብ ሰዎች በሀገሪቱ ፖለቲከኞች ሲወቀሱና ሲከሰሱ ማየት የተለመደ ነው፡፡ ይኸንን ከባድ ተፅዕኖ እየተቋቋመና ምንም ዓይነት አበረታች ነገር በሌለበት ሁኔታ ውስጥ የኢትዮጵያ ቲያትር እስካሁን ድረስ ህልውናውን ጠብቆ ማቆየቱ እንደ ተዓምር የሚቆጠር ነው፡፡

በዴሞክራሲ ስርዓት ውስጥ የሙዚቃ፣ የቲያትርና የሌላም ጥበብ እየተከታተሉ መዝናናት፣ መማርና የእረፍት ጊዜን ማሳለፍ እንደ ሲቪል መብት የሚቆጠሩ በመሆናቸው የመንግስት ከፍተኛ ድጋፍ አይለያቸውም፡፡ በእኛ ሀገር ደግሞ የመንግስት ባለስልጣኖች እንደ ብርቱ ተቀናቃኝ የሚቆጥሯቸው የቲያትር ሞያተኞችን ነው፡፡

የሀገራችን ቲያትር እንዲያድግ ከተፈለገ የቲያትር ጥበብ ለሕዝብ እይታ ማቅረብ እንደ አንድ የተከበረ የሲቪል መብት መሆኑን መቀበል ያስፈልጋል፡፡ በነፃነት እንዲንቀሳቀስ የመንግስትን ተፅዕኖና ጣልቃ ገብነት ማስቀረት ያስፈልጋል፡፡

ይልቁንም ለሕዝቡ ሰፊና ብቁ የቲያትር አገልግሎት ማቅረብ እንዲቻል በሁሉም የሀገሪቱ ክፍሎች ፋሲሊቲዎች የሚሟሉበትን ድጋፍ ማፈላለግና ማስተባበር ይገባል፡፡ ለሞያተኞች ማበረታቻ፣ ሽልማት፣ በቂ ክፍያና የሥልጠና ድጋፍ መስጠት ያስፈልጋል፡፡ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ብቻ የሚሰጠውን የቲያትር ትምህርት በሌሎችም ዩኒቨርስቲዎች እንዲሰጥ፣ በውጭ ሀገር በዘርፉ የሚሰለጥኑ ወጣቶች ወደሀገራቸው ተመልሰው ሀገራቸው ለማገልገል እንዲችሉ የሚስብ አያያዝ መኖር አለበት፡፡ ለቲያትር ቤቶች የውስጥ አስተዳደር ነጻነት መስጠት፣ አሰራራቸውና አደረጃጀታቸው ቀልጣፋና ዘመናዊ እንዲሆን ማድረግ፣ በውድድር እንዲሰሩና ራሳቸውን እንዲችሉ ማበረታታት ያስፈልጋል፡፡ ጎን ለጎን የግል ባለሀብቶችም የስልጠና የትወና ወዘተ. ማዕከላትን ማቋቋም እንዲችሉ የሚያግዝ አቅጣጫ መከተል ያስፈልጋል፡፡ የቲያትር ፌስቲቫሎች እንዲዘጋጁ፣ አማተር የቲያትር ሰዎች እውቅና የሚያገኙባቸው የሚበረታቱባቸው ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ መርዳት ይገባል፡፡ ቲያትር ቤቶች ለደንበኞቻቸው የሶስትና የአራት ቲያትሮች መመልከቻ ትኬቶችን በቅድሚያ የሚሸጡበትን አሰራር በመፍጠር የደንበኞችን መጉላላትና የቦታ ጥበትን ችግር እንዲያቃልሉ የሚያስችል አሰራር መከተል ያስፈልጋል፡፡

የቲያትር ደራሲዎች፣ አዘጋጆችና ተዋናዮች ለሞያቸው እድገት የሚበጅ ሀሳብ ለማፍለቅ፣ የጋራ ችግሮቻቸውን በጋራ ለመፍታትና የተቀናጀ አቅም እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚያስችል ነፃ ማህበር እንዲመሰርቱ መርዳት ይገባል፡፡

የሲኒማና የፊልም ጥበብ በሀገራችን ብዙም የተስፋፋ አይደለም፡፡ በተለይ ከኬብልና ከሳተላይት ቴሌቪዥን መስፋፋት፣ ከቪዲዮና ከኢንተርኔት መግነን ጋር በተያያዘ የሲኒማና የፊልም ጥበብ እንኳንስ እንደእኛ ገና ጠንካራ መሰረት ባልያዘበት ሀገር ቀርቶ ፊልም ራሳቸው በሚያመርቱና በዚህ ጥበብ ብዙ ገፍተዋል በሚባሉትም ሀገሮች ከባድ ፈተና አጋጥሞታል፡፡ በሀገራችን ሲኒማና ፊልም የማምረት ጥበብ ባለመስፋፋቱ በአዲስ አበባና በሌሎች የተወሰኑ ከተሞች በሚገኙ ሲኒማ ቤቶች ለአይታ የሚቀርቡት ፊልሞች ጊዜ ያለፈባቸው ናቸው፡፡ ብዙዎቹን ፊልሞች ሕዝቡ በቴሌቪዥንና በቪዲዮ ለማየት የሚችልበት እድል በመፈጠሩ ወደሲኒማ ቤቶች ለመጉረፍ የሚጓጓበት ሁኔታ እየቀነሰ በመምጣቱ የሲኒማ ቤቶች የረባ ገቢ ማስገኘት አልቻሉም፡፡ በዚህ መስክ እድገት እንዲመጣ ከተፈለገ ፊልም የማምረት ፍላጎት ያላቸውን ዜጎች በመንግስትና በግል ኩባንያዎች እንዲታገዙ በማድረግ የዶክሜንታሪና የፊቸር ፊልሞችን ጎን ለጎን በሀገር ውስጥ እንዲያዘጋጁ መርዳት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አሁን አገልግሎት የሚሰጡትን ሲኒማ ቤቶች ለብዙ ጊዜ የቆዩና ታይተው የተሰላቹትን የውጭ ፊልሞች በማምጣት ፋንታ አዳዲሶችን እንዲያስገቡና እንዲያሳዩ፣ ተደጋግመው ቢታዩም እንኳ ቶሎ የማይሰለቹትን እየመረጡ እንዲያስገቡ የሚያስችል አቅም የሚገነቡበትን ሁኔታ መፈጠር ይገባል፡፡ በሲኒማ ቤቶች ዙሪያ የካፊቴሪያ፣ የምግብ፣ የሱቅ ወዘተ. አገልግሎቶች አብረው የሚኖሩበትን ሁኔታ በመፍጠር የኢኮኖሚ አቅማቸው እንዲጠናከር ማደረግ ይገባል፡፡

በተቻለ መጠን በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በቋሚነት የሚካሄድ የፊልም ፌስቲቫል በሀገር ውስጥ በማዘጋጀትና በውጭ በሚዘጋጁትም ተሳትፎ በማድረግ ወደዘርፉ የሚገቡትን ሰዎች ጥረት እውቅና እንዲያገኝ በተለያየ መንገድ መደገፍ ያስፈልጋል፡፡